# ምዕራፍ ፯

## በኢትዮጵያዊ የተዋህዶ ሰውነት፥ የኹለት ባሕርያት ክሥተት፥ ጽኑ አደገኛነት።

በደብዳቤዎ ውስጥ፡ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡትን ሰባቱን ቃል ኪዳናትና የመንግሥታት ማኅበርን ቃል ኪዳን እንዳናመሳስላቸው" ብለው የጻፉት ሐረግ አለ። ይህ፡ እንግዴህ፡ የራስዎ የግል አስተሳሰብዎ ነው። ይኹን እንጂ፡ ይህንኑ፡ የእርስዎን የግል አስተሳሰብ፡ አርእስት ኾኖ ከምንነጋገርበት፡ ከዚህ ከያዝነው ከታላቁ የቅዱሱ ኪዳን ጉዳይ ጋር በማገናዘብ ሲመለከቱት፡ ርዮሰት ኾኖ ይገኛል። ምክንያቱም፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱ ላይ ያለውን መሠረታዊ አቋም ስለሚፃረርበትና ለቅዱሱ ኪዳን በመሐላ የገባውን ግዳጅ ስለሚቃረንበት ነው።

### የምዕራባውያን ሥርዓተ መንግሥት።

የዚህ አስተሳሰብዎ ነገር፡ በግለሰብ ደረጃ ሲጤን፡ ራሱን፡ በነጠላ፡ "እኔ" ብሎ የሚጠራውን፡ አንድን ሰው፡ ከኹለት የሚከፍል ሲኾን፥ በአገር ደረጃ ሲያጤኑት ደግሞ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እምነት፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ ሦስቱን ቤቶቿን፡ ማለትም፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን፡ በተዋህዶ ምሥጢር፡ እንደነፍስ፥ ሥጋና መንፈስ፡ አንድ አካል አድርጋ የኖረችውን፡ አንዲት ኢትዮጵያን፡ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት በሚል፡ ቀድሞ፡ ከዕብራውያን፥ ዛሬ ደግሞ ከምዕራባውያን ፈሊጥ በተገኘ ስያሜ፡ ከኹለት መለየት ይኾናል። በዚህ አቋምዎ፡ ለኢትዮጵያ ባዕድ ለኾነውና ሥጋውያን የኾኑት ምዕራባውያን፡ Democracy (ዲሞክራሲ ወይም "ሕዝባዊ አገዛዝ") ለሚሉት የሥነ መንግሥት ፍልስፍና (political theory)፡ እርስዎ፡ ምርኮኛና ፍጹም ተባባሪ መኾንዎን ማስመስከርዎ ነው።

### የዕብራውያን ሥርዓተ መንግሥት።

ይህ፡ የዓለማውያን አሕዛብና የሥጋውያን ባዕዳን ባህል፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ረቂቅ መሣሪያነት፡ በሰብአዊ ብልሃትና ዘዴ፡ ሠርጎ ገብቶ፡ ኢትዮጵያውያንን ያጥለቀለቃቸው፡ ዛሬ ብቻ ሳይሆን፡ ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት፡ በኪዳኑ አሪት አማካይነት፡ ወደኢትዮጵያ የገባው፡ የዕብራውያን እምነትና ሥርዓት፡ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር እንዲዋሃድ በተደረገበት ጊዜም፡ ነበር። ነገር ግን፡ ያ፡ በተመሳሳይ መልክና ይዞታ፡ ተከሥቶ የነበረው ሙከራ፡ እንደእስከዛሬው ኹሉ፡ ሳይሳካለት ቀርቷል። ይህንንም፡ በሚከተለው አጭር ቃል አስረዳለሁ።

አዎን! "የአብርሃም ልጆች ነን" ወይም፡ በተለይ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምድር ላይ ከተገለጠ ወዲህ፡ ባኹኑ ጊዜ ጭምር፡ "አይሁድ" ወይም "እስራኤል" ሳይኾኑ "ነን" የሚሉት ዕብራውያን፡ በሙሴ አማካይነት፡ ከኢትዮጵያውያን የተቀበሉትን፡ ከላይ የተጠቀሰውን፡ የመልከ ጼዴቅን የቃል ኪዳን ሥርዓት ትተውና በነቢዩ በሳሙኤል ዘመን፡ "እኛ፡ እንደአሕዛብ ልማድ፡ በሰው እንጂ፡ በእግዚአብሔር ሥርዓት አንተዳደርም!" ብለው በፈጣሪያቸው ላይ ሲያምፁ፡ ወዲያው፡ በሰብአዊ ፍልስፍናቸው፡ የዛሬውን የመሰለ፡ የራሳቸውን ሥርዓት መፍጠር፡ ግድ ኾነባቸው:: ይኸውም፡ ፈጣሪ አንድ አድርጎ የሠራውን፡ የአንዱን ሰው ሕያው ሰውነት፡ ነፍስና ሥጋ በሚባሉ፡ ባሕርያቱና አካላቱ፡ ከኹለት እንደመከፈል በሚቆጠር የመግደል ወንጀል፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ የኾነውን ኹሉ አጣምራ የያዘችውን ክፍል፡ በነፍስ አካል መስለው፡ "ቤተ ክህነት" ብለው በመጥራት፥ ምድራዊና ምግባራዊ የኾነውን ኹሉ አጣምሮ የሚሠራውን ክፍል ደግሞ፡ በሥጋ አካል መስለው፡ "ቤተ መንግሥት" ብለው በመሠየም፡ አንዲት የኾነችውን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ ከኹለት መክፈላቸው ነው::

ከዚህ የተነሣ፡ ነፍስ የተለየችው ሥጋ ምውት እንደሚኾን ኹሉ፡ እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት ይልቅ፡ የሰብአዊ መንግሥትን ሥርዓት በመምረጣቸው፡ እንዲሁ፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት የተለዩ ኾነው፡ በዚሁ፡ እነርሱው በፈለጉት ሥርዓት ከነገሠባቸው፡ ከሳዖል ጀምረው፡ እስከዛሬ ድረስ፡ እነሆ፡ እርስ በርሳቸው በመከፋፈልና በመተላለቅ ይኖራሉ::

ይህንንም ኹኔታ፡ ኢትዮጵያውያን፡ *"በአማን እሳት ውእቱ፡ ዘኢይክሉ ለኪፎቶ እሳታውያን፡ እለ ነደ እሳት እሙንቱ፡ ኪሩቤል ወሱራፌል"* የሚለውን፡ የቅዳሴ ማርያምን የምስጋና ቃል፡ በአንድምታ ሐተታ በሚተረጉሙበት ጊዜ፡ "ታሪክ" ብለው በሚጠቅሱት ማብራሪያ ላይ ገልጸውታል:: ይኸውም፡ የዕብራውያን ንጉሣቸው ዖዝያን፡ ቤተ መንግሥቱን በመወከል፥ ሊቀ ካህናታቸው አዛርያስ ደግሞ፡ ቤተ ክህነቱን በመወከል፡ በኹለቱ ባለሥልጣናት መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ፀብ የሚመለከተው ነው:: ቃሉም እንዲህ ይላል፦ "ንጉሡ፡ ሊቀ ካህናቱን፡ 'ምነው፡ ከእኔ ልብሰ መንግሥት ይልቅ፡ ያንተ ልብሰ ተክህኖ ይበልጣል?' ሲለው፥ ሊቀ ካህናቱ፡ 'መጽሐፉ፡ "ካህናትህ፡ እውነትን ይለብሳሉ እንጂ!" ይለኛል' ብሎ ይመልስለታል:: ሊቀ ካህናቱ፡ የንጉሡን ፍርድ ስለሚገሥሥበት፡ 'ምነው ፍርዴን ትገሠሥብኛለህ?' ይለዋል፤ 'ከመንግሥት ይልቅ ክህነት ይበልጣል' ብሎ ይመልስለታል:: እንዲህ አድርጎ፡ ሊቀ ካህናቱ፡ ቤተ መንግሥትን እያረካከሰ፥ ቤተ ክህነትንም እያነጋገሠ፡ ከመጻሕፍት በመጠቃቀስ ቢያውከው፡ በዚያም፡ በዚያም ቢሉ፡ ንጉሡ ቀንቶበት፡ 'ከቤተ መንግሥትማ፡ ቤተ ክህነት ከበለጠ፡ እኔስ፡ ባባቴ፡ ከቤተ መንግሥት ብወለድ፡ በእናቴ፡ ከቤተ ክህነት እወለድ የለምን?' ብሎ፡ ንጉሡ፡ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶና ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ፡ ወደቤተ መቅደስ ገባ::" ንጉሡ፡ በዚህ ድፍረቱ እንደተቀሠፈ በማስረዳት፡ ታሪኩ ያበቃል::

## የኢትዮጵያውያን ሥርዓተ መንግሥት::

ከዕብራውያን የቀደመው: የእኛ: የኢትዮጵያውያን ሥርዓት ግን: ከላይ እንደተገለጸው: ከዚህ የተለየ ነው:: ይኸውም: ጥንት: በመልከ ጼዴቅ፥ ኋላም: በመካከለኛው ዘመን: በክርስቲያናውያን ተጓዦች ዘንድ: "ቄሱ ንጉሥ" (Prester Jan ፕሬስተር ጃን) ይባሉ እንደነበሩት: እንደነቅዱስ ላሊበላ: አጼው: እንደማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ: ራሱ ሥልጣነ ክህነት ያለው፥ ያም ባይኾን: በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻ: በአንዲት ሴት ተወስኖና ቅዱስ ቊርባንን እየተቀበለ: እንደካህን የሚኖር ስለኾነ: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ይህ ችግር የተፈጠረበት ጊዜ የለም::

የኢትዮጵያውያን ሥርዓት ግልጽ ነው:- ይህንንም ለመረዳት: በዛሬው ዘመን እጅግ ተጋንኖ ስለሚለፈፍለት: Democracy (ዲሞክራሲ) ወይም "ሕዝባዊ አገዛዝ" ስለሚባለው የሥነ መንግሥት ፈሊጥ: በቅድሚያ: ሊታወቅ የሚገባው: ዓቢይ ቁም ነገር አለ፤ ይኸውም: ሥርዓቱ: ጥንቱኑ የተገኘው: ከኢትዮጵያውያን መኾኑ ነው:: ነገር ግን: ኹለቱ ሥርዓቶች: ኹለት መሠረታውያን ልዩነቶች አሏቸው::

በመጀመሪያ ደረጃ: ኢትዮጵያዊው ሥርዓት: ተመሥርቶ የታነጸው: በእግዚአብሔር አምልኮ ላይ ሲኾን: መንግሥቱም የምትመራው: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ነው:: በባዕዳኑ ሥርዓት ላይ የተመሠረተው "ሕዝባዊ አገዛዝ" ግን: የቆመው: በሃይማኖት አልባነት ሲኾን: አገዛዙ የሚመራው: በሰዎች ሥጋዊ ፍልስፍና ነው::

ኹለተኛ: በኢትዮጵያዊው ሥርዓት: የእግዚአብሔር የኾነችውን መንግሥት: ግንዷ ኾኖ: ያቆማትና የሚጠብቃት፥ የሚያካኺዳትና የሚያስተዳድራት: ቤተ ሕዝቡ ሲኾን: እርሱም: በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ሙሉ አባልነትና ፍጹም ተሳትፎ: ህልውና አግኝቶ: ከፈጣሪው: በተፈጥሮና በጸጋ በተሰጠው ባሕርያዊ ሥልጣንና መለኮታዊ ሥርዓት: የተግባሩና የአገልግሎቱ ቅርንጫፎች የኾኑትን: ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን: በነጻ ምርጫ: ከራሱ እያሠረፀ በማደራጀት: ይሠራል:: በባዕዳኑ ሥርዓት የሚመራው "ሕዝባዊ አገዛዝ" ግን: ሰዎች: ለራሳቸው ዓላማ ማስፈጸሚያ እንዲኾናቸው: በሥጋዊ አእምሮአቸው አጥንተው: የሚያወጡትን: የራሳቸውን ሕግ: ሕዝቡ: ፈቃደኛ ሲኾን: በሰላም ተቀብሎ፥ "እምቢ!" ካለ ደግሞ: በኃይል በማስገደድ: በዓለማዊው ዘዴ ብቻ: በሥራ ላይ እንዲያውለው የሚያደርግ ነው::

በዚህ መልክ: በኢትዮጵያ ጸንታ የኖረችው: የእግዚአብሔር መንግሥት: አጼው፥ (ሴት ከኾነች ደግሞ: ንግሥቲቱ): የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ዋና ተጠሪ እንደመኾኑ: ርእሰ ብሔርና ሊቀ ሀገር ኾኖ: የኹሉ በላይና ጠቅላይ ነው፤ ከእርሱ በታች ኾነው: ወደላይ: እርሱን የሚረዱት፥ የሚጠብቁትና የሚቆጣጠሩት፥ ወደታች ደግሞ: አስተዳደሩን: የሚመሩ፥ አገልግሎቱን: የሚያከናውኑና ሥርዓቱን: የሚያስፈጽሙ: ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት የተባሉት አቋሞች: በእኩልነት ደረጃ: በአጼው አካል: አንድ ግንድ፥ በሦስቱ ቤቶች ሊቃነ መናብርት አካላትም: ሦስት ቅርንጫፎች ኾነው: ተግባራቸውን ያካኺዳሉ::

እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን መሥርቶ፥ በመካከሉ፡ በመልከ ጼዴቅ አጽንቶ፥ በመጨረሻ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም፡ በዘውድ ደምድሞ የከለለውን፡ ይህን የኢትዮጵያውያን ዘለዓለማዊ ሥርዓተ መንግሥት፡ ማንም ፍጡር ሊያፈርሰው ቀርቶ፡ ሊለውጠውና ሊያሻሽለው እንኳ አይቻለውም።

በአሁኑ ጊዜ፡ ከብዙዎቹ መካከል፡ አንዳንዶቹን፡ ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፡ ቀደም ብለው፡ በምሥራቁ ክፍለ ዓለም፡ ጃፓን፥ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም ደግሞ፡ ታላቋ ብሪታንያ፡ ይህን ሥርዓተ መንግሥት፡ ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ወርሰው፥ ከሃይማኖታቸው ጋር አስማምተውና ለዘመናዊው ሥልጣኔ አብቅተው፡ እነሆ ሲሠሩበት እንመለከታለን።

## ኢትዮጵያ፡
## የአጼ ኃይለ ሥላሴን ታማኝነት
## ስትፋረድ!

ለመግቢያ ያህል፡ ይህን ከገለጽኩ፡ በአርእስተ ነገሩ ላይ የሚከተለውን ማብራሪያ እሰጣለሁ።

ይህ በእርስዎ የግል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተው መላምት፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ ለእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ ጨርሶ፡ ባዕድ የኾነ፡ እንግዳ ደራሽ ፍልስፍና ነው። አጼ ኃይለ ሥላሴ የፈጠሩትም ትውልድ፡ የዚህ ባዕድ ፍልስፍና አጋር ከመኾኑ ጋር፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ በክህደትና በዓመፅ ለማርከስ በሚካኼደው ትግል ውስጥ ካለው ጽኑ ኅብረት የተነሣ፡ ከእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ተገልሏል።

እኛም፡ በባላጋራችን በዲያብሎስ፡ ተታልለንና ተማርከን እንዳንጠመድበትና እንዳንወድቅበት፥ ነገር ግን ነቅተን በመመልከት፡ እንድንርቀው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዝቅ ብሎ በተጠቀሰው ቃሉ ያስጠነቀቀን፡ የታወቀው የጠላት ማሰናከያ ጕድጓዱ ይኸው ነው።

እንግዲህ፡ እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ያለውልውል፡ በፍጹም ፍቅርና ታማኝነት ሊያገለግለው በፈቃዱ ከመረጠውና መለኮታዊ ጌታው ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር ጋር የተካየደው ቃል ኪዳን፡ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም፡ ቅዱሱ ኪዳን ነው። ሌላ የለም። ለዚህም ሃይማኖታዊ እምነት፡ መሠረቱ፡ ከዚህ በታች የተጠቀሰው፡ እንዲህ የሚለው፡ የጌታ ቃል ነው፦

*"ለኹለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም። ወይም አንዱን ይጠላል፤ ኹለተኛውንም ይወድዳል። ወይም ለአንዱ ይታዘዛል፤ ኹለንተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።"*[፲፩]

ስለዚህ፡ እርስዎ ከሚከተሉት፡ የሥነ መንግሥት ፍልስፍና የመነጨው፡ ከላይ የተመለከተው ቅራኔ፡ በኢትዮጵያዊውና ኢትዮጵያዊ ባልኾነው ግለሰብ፡ ማለትም፡ በእኔና በእርስዎ መካከል ላለው አለመግባባትና አለመስማማት፡ ዋናው መነሻ ምክንያት ኾኖ ይገኛል ። በሌላ አገላለጽ፡ እኔ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ያለኝ ግንዛቤና በኢትዮጵያዊነቴ፡ እርሱን በሚመለከት፡ ልፈጽመው የሚገባኝ ግዳጅ፡ ከእርስዎ ግንዛቤና ግዳጅ ጋር ጨርሶ የማይጣጣም፡ ተጻራሪ ነው ማለት ይኾናል።

አጼ ኃይለ ሥላሴም እኮ፡ እርስዎ የሚደግፉትን፡ ይህንኑ ሰብአዊ የሥነ መንግሥት ፍልስፍና፡ ባለመታደል፡ "ለኢትዮጵያ ይበጃታል" ብለው አጽድቀው፡ በሥራ ላይ እንዲውል ሲያደርጉ፡ በትውልድ ክልላቸው በሐረርጌ፡ ገና በልጅነት ዕድሜያቸው ሣሉ፡ በካቶሊካውያን መምህራኖቻቸው ሞግዚትነት ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ፡ የምዕራባውያን ሥልጣኔ ምርኮኛ የነበሩ መኾናቸውን አረጋግጠው መስክረዋል:: ስለዚህ፡ በዚሁ ፍልስፍና ላይ የተመሠረተውን፡ ይህንኑ ሥልጣኔ፡ በዘመናቸው የነበረው፡ በተለይ ወጣቱ ትውልድ፡ እንዲቀበለውና በተግባር ላይ እንዲያውለው፡ በነበራቸው የማይገሠሥ ሥልጣን በመጠቀም፡ ተፅዕኖ ለማድረግ መቻላቸው ሊያስደንቅ ከቶ አይችልም:: ይልቁንም፡ ይህ አድራጎታቸው፡ በጣልያን ወረራ ምክንያት፡ ከኼዱበት ስደት፡ በአሸናፊው አንበሳ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊነት፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሰው፡ በዙፋኑ ከተቀመጡ በኋላ በሠሩዋቸው ሥራዎች፡ ጎልቶ ይታያል:: ምክንያቱም፡ ያ ጊዜ፡ እርሳቸው፡ በአጼነት በሚመሩዋትና ሃ'ስቱን ቤቶች አዋህዳ በያዘችው የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው አገራቸው፡ ሲሠራበት የኖረውና የተለመደው፡ የሲሦ ድርሻ ቁጥጥር ሥርዓት ቀርቶ፡ ሥልጣናቸው ያለገደብ፡ ፈጽሞ ልቅ የነበረበት ዘመን በመኾኑ ነው::

ይህን ነገር፡ በበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው ገጽታ አለው፤ ይኸውም፡ በራሳቸው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የሕይወት ዘመን፡ በኢትዮጵያ ላይ፡ ለኹለት ጊዜያት የደረሱትን የዕልቂት ጥፋቶች፡ ላስከተለው ምክንያት፡ መንሥኤ ኾኖ የተገኘው ዋና ጠንቅ፡ በእነዚሁ ጊዜያት፡ አንድ ዓይነት የኾነ መልክን ይዞ የተገኘው፡ ይኸው፡ ባዕድ የኾነው የሥነ መንግሥት ፍልስፍና መኾኑ ነው:: ኹለቱ የዕልቂት ጥፋቶች የተባሉትም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ቀደም ብለው፡ በመጀመሪያ፡ ኤውሮጳዊና የካቶሊክ ስለኾነው ነገር ኹሉ፡ ካደረባቸው፡ ጽኑ የፍቅር ስሜት የተነሣ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. የደረሰው፡ የፋሺስት ጣልያን ወረራ ሲኾን፥ ኹለተኛውና የመጨረሻው ደግሞ፡ አሜሪካዊና የምዕራብ ስለኾነው ኹሉ፡ ከነበራቸው፡ የጋለ የቅንዓት ስሜት የተነሣ፡ ከኀርባ ዓመታት በኋላ፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ለመራራው ፍጻሜ የበቃው፡ እግዚአብሔር አልባው የጋርዮሹ (communist) አብዮት ነው::

ከዚህ አልፎ፡ እጅግ ራቅ ባሉት፡ ባለፉት ዘመናት፡ በኢትዮጵያ ላይ ደርሰው የነበሩትን ተመሳሳይ ድርጊቶችና ኹኔታዎች ማዘከሩ አላስፈለገም:: ለማጠቃለል ግን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን፥ ራሳቸውንና መንግሥታቸውን እንዲጠብቅ ያቋቋሙት፡ የክብር ዘበኛ ሠራዊት፡ መንግሥቱ ንዋይ በተባለው የጦር አበጋዙ ቀንደኛነት፡ በቅርቡ፡ ማለትም፡ በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ያካኼደውን፡ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ መጥቀሱ ይበቃል:: ሙከራው ቢከሽፍም፡ የብዙ ሰዎች ደም፡ በግፍ እንደፈሰሰበት ይታወሳል:: እግዚአብሔር፡ ለቃል ኪዳን ሕዝቡ፡ የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ይኾን ዘንድ አምጥቶ፡ ባጭሩ የመለሰው፡ ያ፡ አሠቃቂ ድርጊት፡ በማንም ዘንድ ተደማጭነትን ሳያገኝ ስለቀረ፡ እነሆ፡ አገሪቱና ሕዝቡ፡ ከመሪያቸው ከአጼ ኃይለ ሥላሴና መንግሥታቸው ጋር፡ ለፈራረሱበት፡ ለደርግ የጭካኔ አገዛዝ ሊዳረጉ በቁ!

በቅዱሱ ኪዳን በኩል ኾነው ሲመለከቱት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በኢትዮጵያዊነታቸውና የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ የኾነውን የቃል ኪዳን ሕዝብ በተጠሪነት የሚመሩ የኢየሱስ ክርስቶስ ባለአደራ እንደመኾናቸው መጠን፡ በአንድ ጊዜ፡ የኹለት ጌቶች አገልጋይ፥ እንዲሁም፡ በአንድ ጊዜ፡ የኹለት ቃል ኪዳናት፡ ተካያጅ ኾነው መገኘት ከቶ አይችሉም፤ አይገባቸውምም። በአንድ ወገን፡ ቅዱስ የኾነው፡ የመለኮታዊው ቃል ኪዳን ተዋዋይ ኾነው እያሉ፡ እንደገና፡ በሌላ ወገን፡ ዓለማውያን የኾኑ፡ የኹለት ተከታታይ ቃል ኪዳኖች ተገዢ እንዴት ሊኾኑ ይችላሉ? ኹለቱ ተከታታይ ቃል ኪዳኖች የተባሉትም፡ የሚከተሉት ናቸው፡- የመጀመሪያው፡ በብሪታንያና በፈረንሳይ ቁጥጥር ሥር ይካሄድ ከነበረውና ከፈረሰው የመንግሥታት ማኅበር ጋር፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡ አጼ ከኾኑ በኋላ ባሉት፡ በቀደሙት ዓመታት፡ የተዋዋሉት ሲኾን፥ ኹለተኛው ደግሞ፡ ከስደት ኑሮ፡ በድል አድራጊነት፡ ወደዙፋናቸው ከተመለሱ በኋላ፡ ከጽንሰቱ አንሥቶ፡ በአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ ከሚመራው፡ ከዛሬው የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ጋር የተካየዱት።

ታዲያ፡ ለመለኮታዊው ጌታ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለኹለቱ ሰብአውያን የመንግሥታት ተቋሞች አመራር፡ እንዴት፡ በአንድ ጊዜ፡ አገልጋይና ታዛዥ መኾን ይችላሉ? ቅዱሱን ቅብዓት፡ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተቀብተው፡ ዘውዱን በጫኑ ጊዜ እኮ፡ ከሌሎቹ፡ ከምድራውያኑ ኹሉ የላቀውን፡ መለኮታዊ ቃል ኪዳን "አከብራለሁ!"፥ ከሌሎቹ ዓለማውያን ከኾኑት ኹሉ፡ በልዕልናው የሚበልጠውን፡ ሰማያዊ ጌታም "አገለግላለሁ!" ብለው፡ የታማኝነት ቃለ መሐላቸውን፡ አስቀድመው በሃይማኖታዊ መንፈስ ሰጥተዋል!

ከኹሉ የባሰው በደል ደግሞ እኮ፡ ከመለኮታዊው ቃል ኪዳን ይልቅ፡ ለእነዚያ፡ ለዓለማውያኑ ቃል ኪዳኖች፡ ከፍተኛውን ቅድሚያ መስጠታቸው፥ በእነርሱም ላይ ፍጹሙን እምነታቸውን መጣላቸው ነበር! ከዚህ የተነሣ፡ የኋላ ኋላ፡ ለራሳቸውም ኾነ ለኢትዮጵያ፡ ታላቅ ጉዳትን ያስከተለውን መራራ ፍሬ ሰበሰቡ። ለዚህም ጽኑ የኃላፊነት ጉድለት የተከፈለው ዋጋ፡ እጅግ ያሳዝናል! እርሱም፡ ሊታመን በማይቻልና በሚያስደነግጥ ኹናቴ፡ ከሃምሳ ዓመታት በላይ የደከሙበት ጠቅላላ ሥራቸው፡ በሙሉ መውደሙ ነው። ያንንም፡ ኹላችንም፡ የዓይን ምስክሮች ኾነን ተመልክተነዋል።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ራሳቸውን፡ ለኹለቱ ሰብአውያን ቃል ኪዳናት፡ በተከታታይና በገሃድ ባስገዙ ጊዜ፡ እኒህ ድርጊቶቻቸው፡ "እታዘዘዋለሁ! አገለግለዋለሁ!" ብለው፡ በገዛ ፈቃዳቸውና በቅዱሱ ኪዳን ቃለ መሐላ የተቀበሉትን፡ አማናዊና ታዋቂ የኾነውን መለኮታዊ ጌታቸውን፡ እግዚአብሔርን እንደመካድ አስቆጠራቸው! ከዚህ የተነሣ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የክህደትና የርኵሰት በደል የተፈጸመ መኾኑ ተረጋገጠ። ይህም፡ በመጀመሪያ፡- ማይጨው ላይ፡ በሙሶሎኒ የጣልያን ፋሺስታዊ ሠራዊት ድል መመታትን፥ በመጨረሻም፡- አዲስ አበባ ላይ፡ በእግዚአብሔር አልባው፡ የጋርዮሹ አብዮት፡ የድምሳሴ ውድቀትን አስከተለባቸው።

# ኢትዮጵያ፡
# የምዕራባውያንን ክርስቲያንነት
# ስትፋረድ!

አንድ ላይ በወገኑት፡ በኤውሮጳና በአሜሪካ አህጉር የሚመራው፡ የምዕራባውያን ክርስትና፡ እስካሁን በመቃተት፡ እጅግ ተሠቃይቷል፤ ወደፊት ባሉት ዓመታትም፡ ይህንኑ፡ የመቃተት ሥቃዩን ይቀጥላል። ይኸውም፡ መለኮታዊው ፍርድ፡ ጽዋው ሞልቶ፡ በመጨረሻ፡ *የማይቀረውን የቅጣት ዋጋ፡ ለተወሰነባቸው፡ እንደገና እስከሚከፍልበት* ጊዜ ድረስ ይኾናል። ልክ ዛሬ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ ደርሶበት እንደሚታየውና ያለፈው የዓለም ሕዝብ፡ በኹለተኛው የዓለም ጦርነት ደርሶበት እንደነበረው ማለት ነው። መለኮታዊውም ፍርድ፡ የእነሁ የምዕራባውያኑ፡ የገንዘብ፥ የጥበብና የኃይል አውታራቸው ተዘርግቶ፡ ሰብአዊ የሥነ መንግሥት ፍልስፍናቸው በሰፈነበት የዓለም አካባቢ፡ *ከሚደርሰው በደልና ግፍ የተነሣ፡* የሚመጣው ነው።

ምዕራባውያን፥ በይበልጥ ጎልቶ እንደሚታየውም፡ ክርስቲያኑ ዓለም የሚባለው፡ ኤውሮጳና የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ፡ ሥር ከሰደደውና ሊታረቅ ከማይቻለው፡ የፀረ ኢትዮጵያዊነት አቋማቸው ጋር፡ ይህን፡ ራሳቸው የፈጠሩትን ፍልስፍናቸውን፡ ዛሬ፡ ከመቼውም ጊዜ በተጠናከረ ኃይል፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሕዝቧ ፍላጎትና ፈቃድ ውጪ በኾነ ይዞታ፡ በኢትዮጵያ ላይ ለመጫንና በውስጧ ለማስፋፋት፡ በተፅዕኖ የሚያደርጉትን፡ *የሥነ መንግሥት፥ የሥነ ብዕልና የርእዮተ ዓለም ግፊት፡* በኀዘኔታ እመለከታለሁ። የዚህ ዘመቻ አዘጋጆች፡ በሚገባ አስበውበትና በተባበረ ጉልበት ሊያካኺዱት አቅደው ከተነሡበት ከዚህ ተግባራቸው፡ አሁን ደግሞ፡ የሚሰበስቡት ምርት፡ ምን ዓይነት እንደሚኾን ለማየት፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ እንደተለመደው፡ በሃይማኖት ተስፋ ይጠባበቃሉ።

ለመኾኑ፡ በትክክለኛ አእምሮ ሲያስቡት፡ "እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነኝ" ብሎ የሚያምንና ይህንኑ በቃሉ የሚያረጋግጥ፡ ማለትም፡ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር፡ ቃል ኪዳን የተጋባ፡ አንድ ሰው፡ የምዕራብ ክርስቲያኖች፡ በተለመደ ሕይወታቸው ማድረግ እንደቻሉት ኹሉ፡ ራሱን፡ በኹለት ገጸ ባሕርያት በመግለጽ፡ እንዴት፡ በኹለት መንገዶች ሊሠራ ይችላል? ይህም፡ ባጭር አገላለጽ፡ በምግባሩ፡ እንደመልአክ መኾን የሚጠበቅበት፡ "እኔ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ" የሚል፡ አንድ ግለሰብ፡ በአንዲት አፍታ ውስጥ፡ ወዲያው በቅጽበት፡ ራሱን ለውጦ፡ የዲያብሎስም አገልጋይ በመኾን፡ እንደሰይጣን ለመሥራት የሚችልበት ኹኔታ ነው።

ይህን የእስስት ባሕርይ ወይም የማስመሰል ጠባይ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ፡ እንኳንስ በተግባር ሊያውለው፡ በአእምሮውም ሊያስበው አይኾንለትም፤ ምክንያቱም፡ በእርሱ ዘንድ፡ ይህን የመሰለው ምግባር፡ በአምላኩ፡ በእግዚአብሔርና በተፈጥሮ ወገኑ፡ በሰው ላይ፡ እንደተፈጸመ፡ የክህደትና የርኵሰት ኃጢአት አድርጎ ስለሚቆጥረው ነው።

አዎን! የሰዎች እርቃናዊ ተፈጥሮ፡ መንፈስን ሳይጨምር፡ ነፍስና ሥጋ በተባሉት፡ ኹለት አካላትና ባሕርያት የቆመ፡ ክዕበት (ኹለትነት) ያለው መኾኑ፡ እርግጥ ነው:: ዳሩ ግን፡ ይህ፡ የክዕበት ሰብአዊ ተፈጥሮ፡ ማለትም፡ ይህ ኹለትነት እኮ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕታዊ ቤዛነት በተገኘው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ ለሰው ዘር የተሰጠውን፡ ሦስተኛውን መንፈሳዊ አካልና ባሕርይ በለበሰባት ቀን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ድል ተነሥቶና ተሸሮ፡ በሃይማኖት ለአንድነት በቅቷል:: ይህም ብቅዓት የተገኘው፡ እንዲህ፡ በአንዱ የሰውነት አካል ውስጥ፡ ባልተቋረጠ ተፃራሪነት፡ እርስ በርሳቸው ሲቀዋወሙ በኖሩት፡ በነፍስና በሥጋ ትግል ምክንያት፡ ኹለትነት የነበረው ሰብአዊ ባሕርይ፡ በጥምቀት፥ በንስሐና በቅዱስ ቁርባን ምሥጢራትና ሥርዓታት አማካይነት በተከናወነው፡ የመንፈስ ቅዱስ አዋሃጅነት፡ ከዘለዓለማዊው ሰላምና ዕረፍት በመድረሱ ነው::

ክርስቲያን ነን የሚሉት ምዕራባውያን፥ ከእነርሱ የተነሣም፡ የምዕራቡን የሥነ መንግሥት ፍልስፍናና ፈሊጥ የተቀበለ፡ የማናቸውም ብሔር፥ ወገንና ሃይማኖት ተከታይ የኾነ፡ ማንኛውም ግለሰብ ጭምር፡ አደገኛ የኾነው፡ የዚህ የኹለትነት ባሕርይ ጠንቅ፡ ቀላል ሰለባዎች ኾነው ሊወድቁ እንደሚችሉ፡ በግልጽ ይታያል:: ይህም፡ *"በአንድ ጊዜ፡ ኹለት ጌቶችን፡* ማለትም፡ እግዚአብሔርንና ሰው ሠራሽ የኾኑትን ነገሮች፡ ማለትም፡ እግዚአብሔርንና መንግሥታዊ ፈሊጥን፥ ወይም እግዚአብሔርንና ሥነ እውቀትን፥ ወይም እግዚአብሔርንና ገንዘብን፥ ወይም እግዚአብሔርንና ሥልጣንን፥ ወይም እግዚአብሔርንና ኃይልን ማገልገል እችላለሁ!" የሚል አቋምን ይዞ መገኘት ማለት ነው::

ስለዚህ፡ ዘረኝነትን የሚጨምረው፡ ጥላቻና የእርስ በርስ ግጭት፥ ሌላውም የበደል ዓይነት ኹሉ፡ ነቀርሳ ከኾነው ጠንቁ ጋር፡ በምዕራቡ ዓለምና እንዲሁም፡ ቀደም ብሎ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በነበረው፥ ባሁኑ ጊዜም፡ በምዕራባውያን የሥልጣን ክልል ውስጥ በሚገኙት፡ ኢትዮጵያን በመሰሉት አገሮች ውስጥ፡ እንዲህ እያየለ የኼደውና ዕድገቱ የቀጠለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን መገንዘብ ይገባል::

እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ግን፡ ከኹሉ የቀደመና የራሳቸው የኾነ፥ በነጻ ሕዝባዊ ምርጫም ላይ የተመሠረተ የአስተዳደር ሥርዓተ መንግሥት ስላላቸው፡ በእነርሱ ዘንድ፡ ይህ የባዕዳን ፍልስፍና፡ በፍሬያማ ተግባር ላይ ሊውል የማይችል መላምት ብቻ ሳይኾን፡ እንደሰይጣናዊም የሚቆጠር ነው፤ እንዲያውም፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ "መርገም ነው" ተብሎ ይወገዛል::

## ኢትዮጵያ፡
## የአጼ ኃይለ ሥላሴን አመራር
## ስትፋረድ!

"ሃይማኖት የግል፥ አገር የጋራ!" በሚል መፈክር፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በይፋ ያስታወቁት፡ ድንገተኛና ማዕበላዊ፥ መሠረታዊም የኾነ፡ የአመራር ለውጥ፡ እርሾውና ምንጩ፡ ይኸው፡ የምዕራባውያኑ፡ የሥነ መንግሥት ፍልስፍና መኾኑ አይካድም::

ይህ ደግሞ: የመልከ ጼዴቅ ልጆች በመኾናቸው: ጥንት: ከምዕራባውያን ቀርቶ: ከምሥራቃውያን በፊት ጀምረው: በእግዚአብሔር መንግሥትነት: ቤተ ሕዝባቸውን፥ ቤተ ክህነታቸውንና ቤተ ምልክናቸውን አዋህደው: ሲተዳደሩ ለኖሩት ኢትዮጵያውያን: ባዕድና እንግዳ ነገር ኾኖ የተገኘ: "ሥር ነቀል" ለውጥ ነው:: ይኸው ድርጊት: ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ: በቤተ ክርስቲያን ተቀብተው፥ *"ምአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* ከተባለው: ከንጉሠ ነገሥታቸው: ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉትን ዘውድ ተቀዳጅተውና "አጼ" ተብለው: በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ በተቀመጡባት ዕለት "እጠብቀዋለሁ! አጸናዋለሁም!" ብለው: በሃይማኖታዊ ሥርዓትና መሐላ: ለቅዱሱ ኪዳን የሰጡትን: ቃል ኪዳን በማፍረስ: ከዚህ አቋማቸው ተለይተው: ባዕዳን ወደ ኾኑት አዝማሚያዎች የማዘንበላቸው ነገር: በይፋ ከተከሠቱባቸው የክህደት ድርጊቶቻቸው መካከል: የመጀመሪያው ኾነ!

አጼ ኃይለ ሥላሴ: ይህን: የሥነ መንግሥታዊ አመራር ለውጥ ያካኼዱት: ያለምክንያት አልነበረም:: ያም: እርስ በርሳቸው: የተለያየ እምነትና ዓላማ ያላቸው ኾነው፥ ነገር ግን: በልቅ አኗኗር ደጋፊነታቸው: ማለትም: መረን ለተለቀቀው: ለአሕዛብ የአኗኗር ልማድ: የተባበረ አቋም ያላቸውን: ያገር ውስጥ ነዋሪዎችንና የውጭ ባዕዳንን ለማስደሰት፥ ለማረጋጋትና ለማበረታታት ነበር:: ይሁን እንጂ: ይህ እርምጃቸው: ከላይ እንደተመለከተው: ቅዱሱን ኪዳን በክብር ለመጠበቅና በፍቅር ለማንከባከብ የገቡትን: መሠረታውያን ግዴታዎቻቸውን: በተፃራሪ መልክ: በስፋትና በጥልቀት ነክቶባቸው ተገኘ::

አዎን! ጥንት ከፍጥረት አንሥቶ: በኢትዮጵያ ውስጥና በኢትዮጵያውያን መካከል: ማነኛውም ግለሰብ: ወይም ኅብረተሰብ: የራሱን ሃይማኖታዊ አምልኮ: ያለችግር ለማካኼድ የሚያስችለውን ሙሉ ነጻነት ተነፍጎ ወይም መብቱን አጥቶ አያውቅም:: ይህ ነጻነትና መብት: በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት: በልብ እንጂ: በወረቀት ሰሌዳ ላይ ባልተጻፈው: በመለኮታዊው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ታትሞና ተረጋግጦ: ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለኾነ: በማንም: ሥጋዊ ኾነ መንፈሳዊ ፍጡር: ሊገሠሥ ከቶ አይቻልም:: የዚህ እውነታ ትክክለኛነትና እርግጠኛነት: በኢትዮጵያ ሕያው ዜና መዋዕል ብቻ ሳይኾን: በምሁራኑ የሰዎችም ታሪክ ሳይቀር ሲመሰከርበት የኖረ፥ ዛሬም እየተመሰከረበት ያለና እየቀጠለ የኼደ መኾኑ ይታወቃል:: ይኹን እንጂ: ተጠብቆ ሊኖር የሚገባው: ይህ መለኮታዊ ሥርዓት እያለ: እንደሥርዓቱ: ሦስቱም የእግዚአብሔር መንግሥት ዓበይት ቤቶች: ማለትም: ቤተ ሕዝቡ፥ ቤተ ክህነቱና ቤተ ምልክናው: በአንድነት ሳይስማሙበት: በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኩል: በብቸኝነት የተሰጠው: ያ: ከላይ የተጠቀሰው: ያንድ ወገን: መንግሥታዊ መመሪያ: ቀደም ብሎ እንደተወሳው: እርሳቸው: "አጼ" ተብለው የተቀቡበትንና ዘውድ የጫኑበትን፥ ጥንታዊዉንና "ሥር በቀል" የኾነውን: የአገሪቱን የቃል ኪዳን ሃይማኖት የሚያናውጽ እንጂ: ሊጠብቀውና ሊያጠናክረው ከማያስችል: አሳሳቢና አደገኛ ኹኔታ ላይ እንዲወድቅ አደረገው::

ያ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በአገር ደረጃ ያወጁት፡ መንግሥታዊ መመሪያ፡ በከፈተው አዲስ አግጣጫ ምክንያት፡ ሊደርስ የሚችለውን፡ ጊዜያዊ፥ የአጭርና የረዥም ዘመን ጉዳት፡ አብዛኛው የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ የተገነዘበው አይመስልም ነበር፡፡ ምክንያቱም፡ "አጼ ኃይለ ሥላሴና መንግሥታቸው፡ ለቃል ኪዳን አምላካቸውና ለቅዱሱ ኪዳን ያላቸውን ታማኝነት አጽንተው ይቀጥላሉ" ብሎ፡ ያለአንዳች ጥርጣሬ ያምን ስለነበር ነው፡፡ እውነታው ግን፡ ይህ አልነበረም፡፡ ለዚህም፡ ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ዘርፎች፡ አንዱ በኾነችው፡ በቤተ ክህነቱ በኩል የታየውን ኹኔታ በምሳሌነት እጠቅሰዋለሁ፡፡

## የአመራሩ ቀውስ፡
## በቤተ ክህነት ላይ፡ ያስከተለው ችግር፡፡

እኔ፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ኾኜ እስከተመደብኩበት፡ እስከ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ድረስ፡ የቤተ ክህነት ሰዎች፡ ማለትም፡ በመላው ኢትዮጵያ የሚያገለግሉት፡ ካህናት፥ መምህራኑና ሊቃውንቱ፥ የአዲስ አበባና የየሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤቶች፣ ሠራተኞች፥ ራሴ ጭምር፡ ኹሉም፡ ያስቡት የነበረው፡ ራሳቸውን፡ እንደመንግሥት ሠራተኛ አድርገው ነበረ፡፡ ቀደም ብለው እንዲያውቁት የተደረገ፡ አንዳችም ነገር፡ ወይም ፍንጭ የሚኾን ምልክት እንኳ ስላልነበረ፡ ከዚህ የተለየ አቋም መኖሩን፡ ጨርሰው አያውቁም፡፡ ይኖራልም ብለው፡ ጥቂትም፡ ጥርጣሬ አልነበራቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት፡ በሥራ አመዳደብ፥በደመወዝ አከፋፈልም ኾነ፡ በጡረታ አወጣጥ ሥርዓት፡ በመንግሥቱ ደንብ መሠረት የሚፈጸምላቸው ይመስላቸው ነበር፡፡

በተሰጠኝ ኀላፊነት፡ በዚህ ረገድ፡ ሥራው የሚመራበትን ደንብ በምጠይቅበት ጊዜ፡ የሚፈለጉት ደንቦች ኹሉ ባለመገኘታቸው፡ ስለዚሁ ጉዳይ ለመረዳት፡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው፡ የቤተ ምልክናው (የመንግሥት) መሥሪያ ቤቶች ጋር፡ ባደረግሁት መጻጻፍ፡ ቤተ ክህነት፡ በሕግ፡ ከመንግሥት ሠራተኛ ማስተዳደሪያና ከጡረታ አስተዳደር አዋጆች ውጪ መኾኗን የሚያስታውቅ የመርዶ ደብዳቤ ደረሰ፡፡ ይህም ደብዳቤ፡ በቤተ ክህነቱ ዘንድ ታላቅ ድንጋጤንና ኃዘንን ፈጠረ! ለተጨማሪ ማብራሪያ ለተጻፈው ጥያቄ፡ የተገኘው ምላሽ፡ ቤተ ክህነት፡ ያላት ዕድል፡ እንደሌሎቹ የግል ድርጅቶች፡ የራሷን ደንብ አዘጋጅታ፡ በዚህ በኩል ያለባትን ኃላፊነት ከመወጣት በቀር፡ በእነርሱ በኩል ምንም የሚያደርጉት ነገር አለመኖሩን የሚገልጽ ነበር፡፡

ለችግሩ መፍትሔ የሚኾን፡ ሌላ አማራጭ ባለመገኘቱ፡ ቤተ ክህነት፡ ከእግዚአብሔር የተሰጣትን፡ ጥንታዊ መብቷን የነፈጋትና ከአንድነት አካሏ ለመገንጠል በመሞከር፡ "ከእኔ ጋር ክፍል የለሽም" ብሎ፡ በሥውር የበየነባት፡ ያ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ በዚህ ድርጊቱ፡ በመለኮታዊው ፍርድ ተይዞ፡ ለውድቀት እስከበቃበት፡ እስከአብዮቱ ፍንዳታ ድረስ፡ የራሷን ደንቦች አርቅቃ፡ ይፋ ለማውጣት እየተዘጋጀች እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡

ከዚህም በላይ፡ በሦስቱ፡ የመለኮታዊቷ መንግሥት ቤቶች ውስጥ ተመድበው፡ የየበኩላቸውን አገልግሎት፡ በያሉበት በመስጠት ላይ ይገኙ የነበሩት፡ እንያ፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ እንግዴህ፡ ባዕዳን ሃይማኖቶች፡ በዚያ፡ የአዋጅ መመሪያ መሠረት፡ በአገሪቱ ውስጥና በሕዝቡ መካከል፡ እምነታቸውንና ዓላማቸውን፡ እንዲህ፡ እንደልባቸው እንዲያሠራጩና እንዲያስፋፉ፡ ይህን ያህል፡ መረን የተለቀቀ ነጻነትን ከተቀዳጁ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ደግሞ፡ "የቅዱሱ ኪዳን ባለአደራ የኾነችው የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ይህን፡ አዲስ ኹኔታ ለመቋቋም ትችል ዘንድ፡ አስፈላጊውንና ተገቢውን ተመጣጣኝ ዝግጅት፡ በቅድሚያ ያከናውንላታል" ብለው አምነው ነበር፡፡ እምነታቸውም፡ "ለባዕዳኑ ከተሰጠው ነጻነት፡ በበለጠ መጠን፥ ያ ካልኾነ ደግሞ፡ ከዚያ ጋር፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ ተወዳዳሪና ሚዛናዊ በኾነ መጠን፡ ጥረት ይደረግበታል ተብሎ የታቀደ፡ የቅድሚያ ዝግጅት ይኖራል" የሚል ነበር፤ በዚህ ዝግጅት መሠረት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በየዘርፉ ያሉባትን፡ የኃላፊነት ተግባሮች፡ በትክክልና በሚበቃ ለማካኼድ ከሚያበቃት የገንዘብ ወጪ፥ የሠለጠነ የሰው ኃይልና የአገልግሎት መሣሪያ ይዞታ ጋር፡ የካህናቷን የእውቀትና የችሎታ መጠን ከፍ ማድረግ፥ እንዲሁም፡ ለጥንታዊ አቋሟ፡ ዘመናዊ መልክን፥ ለዕርግና (ለኖረ) ባህሏም፡ የተሐድሶ ዕድገትን በሚሰጥ መልክ እንደሚከናወን ተማምነው ነበር፡፡

ዳሩ ግን፡ ተፈጽሞ የተገኘው፡ እጅግ ያዘኑበት፡ ተቃራኒው እንጂ፡ ይህ፡ የጠበቁት አልነበረም፡፡ ይኸውም፡ በቅድሚያ ያስተዋሉት፡ በቃል ኪዳን አለኝታነቱ፡ እምነታቸውን ጥለውበት በነበረው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ አመራር፡ ተከደውና ለጠላት አልፈው ተሰጥተው፡ ማለትም፡ እንደአሮጌ ዕቃ፡ ወዲያ ተወርውረው፡ ራሳቸውን ማግኘታቸውን ነበረ፤ ቀጥሎ፡ እያደርና እየቆየ፡ በተለያየ ማስመሰያ መልክ፡ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረግ በነበረው፡ ምሥጢራዊ ስልትና ሥርዓታዊ ዘዴ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕያው ውርሳቸው መሠረት፡ ቀስ በቀስ እየተቦረቦረና እየተናደ መሄዱን ማስተዋላቸው ነበር፡፡

በመጨረሻ፡ ይህ ድርጊት፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ በኩል፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተፈጸመ የክህደትና የርኵሰት ኃጢአት መኾኑን ሲያረጋግጡ፡ እነሆ፡ የመለኮታዊው የፍርድ ጊዜ መቃረቡን አወቁ!

እዚህ ላይ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በማናለብኝነት ድፍረት ስለፈጸሙት የክህደትና የርኵሰት ኃጢአት፡ አንዳንድ ጉልህ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይኸውም፡ የምዕራባውያንን ሥልጣኔ ወደኢትዮጵያ በማስገባትና በማስፋፋት፥ የባዕዳን የኾነውን፡ የሥነ መንግሥት ፍልስፍናቸውንም ጭምር፡ በተፅዕኖ፡ በተግባር ላይ በማዋል ረገድ፡ በእነርሱ ዘንድ፡ "ጀግና" ያሰኛቸውን አገልግሎት፡ ለእነርሱ ለማበርከት ሲሉ፡ ለቅዱሱ ኪዳን በመሐላ የገቡትን ግዴታዎቻቸውን ሳያከብሩ መቅረታቸው ነው፡፡ ከእነዚህ ማስረጃዎች መካከል፡ እስቲ፡ ከቅርቦቹ ተነሥቼ፡ ወደኋላ እየኼድኩ፡ ጥቂቶቹን ብቻ ልጥቀስ!

## ኢትዮጵያ፡
## የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱሳውያንን
## ስትፋረድ!

ለዚህ ሰፊ የዕቅድ ተግባራቸው ፍሬያማነት፡ የመጨረሻው የድል አክሊል ምልክት ኾኖ የሚቀርበው፡ የሥራ ውጤታቸው፡ በኢትዮጵያ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ፡ በስማቸው የተቋቋመው፡ በአጠቃላይ ኹለንተናውና ባሕርዩ፡ ፈጽሞ ምዕራባዊ የኾነው፥ ዘሩ፡ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መሠረት ላይ ተጥሎ፡ የኋላ ኋላ፡ በተከታታይ ዕድገቱ፡ ለተሟላ ብሔራዊ መካነ አእምሮነት (universityhood ዩኒቨርሲቲነት) የበቃው፡ ቀዳሚው ከፍተኛ የእውቀት ተቋም (college ኮሌጅ) ነው፤ እርሱም፡ "የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መካነ አእምሮ" ይባል የነበረው፡ የዛሬው፡ "የአዲስ አበባ መካነ አእምሮ" ነው።

ይህን የመሰለውን፡ ከፍተኛ የእውቀት ተቋም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ገና በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን ካቋቋሙትና የመጀመሪያው ዘር ከተጣለበት፡ ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ጀምሮ፡ በትምህርት አሰጣጡና በአስተዳደር አመራሩ ረገድ፡ ጠቅላላውን ኃላፊነት ይዞ እንዲሠራ፡ ሙሉው ሥልጣን የተሰጠው፡ የኢየሱሳውያን (Jesuits ጄዙዊትስ) ማኅበር የሚባለው፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ ዋና የሥራ ማካኼጃና ማከናወኛ ዘርፍ የኾነው ድርጅት ሲኾን፡ የትምህርት ቤቱንም ኾነ የተቋሙን ዓላማ፡ በመምህርነትም ኾነ በሠራተኛነት፡ ተግባራዊ የሚያደርጉት፡ የዚሁ ማኅበር አባሎች የኾኑት ካቶሊካውያን ካህናት ነበሩ።

በዚህ፡ "የኢትዮጵያ" ተብሎ፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለተቋቋመው፡ "ትምህርት ቤት"፥ "የትምህርት ተቋም" ወይም "መካነ አእምሮ"፡ ለሃይማኖታዊው አገልግሎትና ለመንፈሳዊው እረኝነት፡ እንደሌሎቹ፡ የባዕዳኑ ተመሳሳይ ተቋማት፡ አንድ ኢትዮጵያዊ ኖላዊ (ጠባቂ) ካህን (chaplain ቻፕሊን) እንኳ አልተመደበም፤ ለዚሁ ተግባር የምትውል፡ አንዲት ኢትዮጵያዊት ቤተ መቅደስም (chapel ቻፕል) እንኳ፡ ተለይታ አልተዘጋጀችም።

በዚህ ረገድ፡ የተፈጸመው ድርጊትና የታየው ኹኔታ ኹሉ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ እንቆቅልሽ ኾኖ እንደቀጠለ ይገኛል። ይኸውም፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር"፡ ማለትም፡ "እግዚአብሔር መርጦ የሾመው" ራሱ፡ ኢትዮጵያዊው አጼ፡ በዙፋናዊው ሥልጣን ላይ እያለ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን እንዲጠቅምና ለእርሷ አገልግሎት እንዲውል ተብሎ የተቋቋመው፡ ይህን የመሰለው ማስተማሪያ ድርጅት፡ በመጀመሪያ፡ በሚቋቋምበት ጊዜ፡ በአገሪቱ የትምህርት አሰጣጥ በኩል፡ የመለኮታዊቷ መንግሥት፡ ተጠሪና ኃላፊ ኾና የኖረችው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ከጽንሰ ሐሳቡ ጀምሮ፡ እስከሥርዓተ ትምህርቱ፥ መርሐ ግብሩና የሥራ ክንውኑ ድረስ፡ ሊኖራት ከሚገባው፡ ከሙሉው የተካፋይነት መብቷ እንድትገለል መደረጉ፥ ኹለተኛም፡ ለድርጅቱ ህልውና፡ እጅግ አስፈላጊ፥ ለኢትዮጵያዊነቱም መለያና መታወቂያ የኾኑትን፡ እኒያን ቀላል የአገልግሎት መሰናዶዎች እንኳ እንዳያገኝ መከልከሉ ናቸው።

በእኔ በኩል፡ በመለኮታዊው ፍርድ የተወሰነው የቁጣ ማዕበል፡ በምንም መንገድ፡ ሊገታ የማይችል መኾኑን፡ ኋላ ልገነዘብ ቻልሁ እንጂ፡ ያጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር፡ ሊወድቅ ወደተቃረበባት፡ ወደመጨረሻዪቱ ጊዜ፡ ማለትም፡ ለቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት አገልግሎት፡ ተጠርቼ በነበረበት ወቅት፡ ወደ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ግድም፡ በዚሁ መካነ አእምሮ አጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘውና ቀድሞ፡ "ገነተ ልዑል" ይባል የነበረው፡ የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን፡ ለመካነ አእምሮው ቤተ መቅደስነት እንዲውል፥ ለካህንነቱም፡ አባ መዓዛ ይባሉ የነበሩት መነኵስ (ኋላ፡ በደርግ አገዛዝ ሥር፡ በጵጵስና ሢመት፡ አባ አትናቴዎስ የተባሉት) እንዲመደቡ፡ አሳቡን በቅድሚያ፡ በጊዜው፡ የመካነ አእምሮው ሙሴ (President) ለነበሩት፡ ለሊቀ ምሁር (Dr.) አክሊሉ ሀብቴ አካፈልኋቸው፤ ያም ወራት፡ የመካነ አእምሮው ተማሪ ኹሉ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ በዓመፅ የተነሣሣበት ጊዜ ስለነበረ፡ አሳቡን፡ እርሳቸውም ኾኑ የበላዮቻችን፡ ያለማመንታት ፈጥነው ስለተስማሙበት፡ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ።

ዳሩ ግን፡ ምን ያደርጋል! ተገድቦ የቆየውና እስከአፉ፡ ጢም ብሎ፡ ሞልቶ የነበረው፡ የዓመፁና የቁጣው ማዕበል፡ ለካ፥ በዚያን ጊዜ፡ ተርፎ መፍሰስ ጀምሮ ኖሮ፡ ከጥቂት ወራት በኋላ፡ ያ፡ በቅርብ የተደከመበት ውጥን ዝግጅት፡ ገና በእንጭጭነቱ፡ በቅጣቱ ማዕበል ተጥለቅልቆ፡ ፍሬ አልባ ኾነ! ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ጀምረው፡ በካቶሊካውያኑ ኢየሱሳውያን ካህናት ተኰትኵተው ያደጉትና ለDoctorate (ዶክቶሬት) የትምህርት ማዕርግ፥ ከዚያም፡ በእነርሱ ተመሥርቶ ለታነጸው መካነ አእምሮ ሙሴነት (Presidency ፕሬዚዴንትነት) የበቁት Dr. (ዶክቶር) አክሊሉ ሀብቴ፡ በደርግ አገዛዝ ሥር፡ የባህል ምሉክ (Ministre) ኾነው ተሹመው ወዳገለገሉበት መሥሪያ ቤት ሲዛወሩ፡ የቀረነው ደግሞ፡ ወደደርግ የእሥርና የሞት ጽዋ ተላክን።

## ኢትዮጵያ፡
## ፀረ ማርያሞችን ስትፋረድ!

ቅዱሱ ኪዳን፡ በአገሪቱ ላይና በሕዝቡ ዘንድ፡ ተጠብቆ መቀጠሉን በማረጋገጥ ረገድ፡ የባለአደራነት ኃላፊነትና ግዴታ ያላት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ በጉዳዩ ውስጥ፡ ሕጋዊው አግባብና ተሣትፎ ሳይኖራት፥ የስምምነት ቃሏንም፡ በአግባቡ ሳትሰጥ፡ World Lutheran Federation (ወርልድ ሉተራን ፌዴሬሽን) ለተባለ፡ ዓለም ዐቀፍ፡ ፀረ ማርያም (Protestant ፕሮቴስታንት) አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት፡ "ብሥራተ ወንጌል" በሚል ስያሜ፡ አዲስ አበባ ላይ፡ ኃይለኛ የኾነ፡ አንድ፡ የነፋስ ድምፅ (radio) ማስተላለፊያ ጣቢያን እንዲያቋቁም መፈቀዱ፡ ሌላው ማስረጃ ነው። ከዚህ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ እንደመካነ አእምሮው ኹሉ፡ ይህም ዓለም-አቀፍ ድርጅት፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ላይ፡ ያን የመሰለውን፡ የወረራና የማጥፋት ዘመቻን፡ እጅግ ባየለና በተራቀቀ ይዞታ፡ በገሃድ ሊያካኺድ ባደረገው የዕቅድና የተግባር መሰናዶው፡ እንዲያ ሊወላዳና ሊቀናው የቻለው፡ በጊዜው የነበሩት፡ የቤተ ክህነት መሪዎች፡ እጨጌ ባስልዮስና እንደራሴያቸው አባ ቴዎፍሎስ፡ ሌሎቹም ጳጳሳት፡ የነበራቸውን፡ ከግዴለሽነትና ከቸልተኛነት፥ ከዝምተኛነትና ከአኰራፊነት የማያልፈውን፡ ደካማ አቋማቸውን፡ በአገር ውስጥ ወኪሎቹ አማካይነት ስለተማመነ እንደነበረ፡ ከዚህ የሚከተለው፡ የጉዳዩ ኺደት በግልጽ ያሳያል።

እንዳጋጣሚ: ይህ ድርጊት እንደተፈጸመ ወዲያው: ከታኅሣሥ: ፶፫ ዓ. ም. የእነ መንግሥቱ ንዋይ ግርግርና እልቂት በኋላ: ጠቅላላው የአገሪቱ የውድቀት አዝማሚያ ኹኔታ አሳስቦኝ: በራሴ ጠያቂነትና ፈቃደኛነት: በቤተ ክህነት ውስጥ: ለትምህርትና ስብከት፥ ለማስታወቂያና ድርሰት ክፍሎች የኃላፊነት አገልግሎት ተጠርቼ: ሥራ የጀመርሁበት ጊዜ ስለነበረ፥ ያ: የነፋስ ድምፅ ማስተላለፊያ ጣቢያ እንዲቋቋም: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ደረጃ የተሰጠው ፈቃድ አላገባብ መኾኑን በማመልከት: ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ አስፈላጊ መኾኑን: መጀመሪያ: በጊዜው: የቤተ ክህነቱ መሪ ለነበሩት: ለእጨጌ ባስልዮስና ለእንደራሴያቸው: ለአባ ቴዎፍሎስ አሳሰብሁ:: ይህን ማሳሰቢያ: እነርሱ ሲቀበሉት: ጉዳዩ: በጽሑፍ ማስታወሻ ተዘጋጅቶ: በቀጥታ ለአጼው ቀረበላቸው፤ እርሳቸውም: ኋላ የሚያደርጉትን ያውቁታልና: ለጊዜው ውጥረቱን ለማርገብ ሲሉ: ግድ ኾኖባቸው: የቀረበው አሳብ: በልዩ ከፍተኛ ምርፋቅ እንዲጠና አዘዙ:: የዚያም: ምርፋቅ ጸሓፊ: እኔው እንድኾን ተፈቅዶ: ጥናቱ ተጀመረ::

ከቤተ ክህነት የቀረበው ይህ ማሳሰቢያ: "ጉዳዩ: እንደገና መታየት አለበት" ለሚለው ጥያቄ: መሠረት ያደረገው ነጥብ: በቅዱሱ ኪዳን: የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው: በኢትዮጵያ ምድርና ሕዝቧ ላይ: ይህን የመሰለው: የባዕድ ሃይማኖት መስበኪያ ጣቢያ ሲቋቋም: "ባለአደራዋና ተጠያቂዋ: የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: ባላት: የኃላፊነት ድርሻዋ: መስማማት አለባት" የሚለውን ቀዳሚ ምክንያት ብቻ አልነበረም፤ ሌላ ዋና ምክንያትም ነበር:: ይኸውም: አንደኛ: የኢትዮጵያ ቤተ ክህነትና ያ: የነፋስ ድምፁን ጣቢያ የሚያቋቁመው: የዓለም ሉተራውያን ድርጅት: ኹለቱም: መሥራቾች ኾነው ያቋቋሙት: ዋና መሥሪያ ቤቱ: ጄኔቫ የኾነው: World Council of Churches (ወርልድ ካውንስል አፍ ቸርችስ) የሚባለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት አባሎች ስለኾኑ፥ ኹለተኛ: በ፲፱፻፵፰ ዓ. ም. በኔዘርላንድ ከተማ: በአምስተርዳም: በአባሎቹ ስምምነት የጸደቀው: የምክር ቤቱም ዓላማ: አባሎቹ: እየተባበሩ: በምድር ላይ: በኢየሱስ ክርስቶስና በእናቱ ድንግል ማርያም: ገዝፋ የተገለጠችውን: የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲያስፋፉ በመኾኑ: ስለማስተላለፊያው ጣቢያ መቋቋም የሚደረገው ውል: ሕጋዊ ሊኾን የሚችለው: ኹለቱም ወገኖች: በቅድሚያ ተነጋግረው የተስማሙበትን ረቂቅ: በአግባቡና በመስመሩ: ለሚመለከተው የመንግሥቱ አስፈጻሚ ዘርፍ: ማለት ለቤተ ምልክናው ሲያቀርቡ ነው" የሚል አቋምን የያዘው ምክንያት ነበር::

ከዚህ ጋር: ቤተ ክህነት: ቀደም ብላ: ሳታውቀውና ሳትስማማበት: "በውል የተሰጠው ፈቃድ: ሕጋዊ አይደለም" ያሰኘው ሌላው ምክንያት: የውሉ ዝግጅት የተካኼደውና የተከናወነው: "አባቱ ዳኛ! ልጁ ቀማኛ!" እንደሚባለው: በዚያን ጊዜ: ባንድ ወገን: የዚያ: የዓለም ሉተራውያን ድርጅት: የሃይማኖቱ ተከታይ አባል፥ በኢትዮጵያም: የሃይማኖቱ ተጠሪና መሪ ሲኾኑ፥ በሌላው ወገን ደግሞ: በኢትዮጵያ መንግሥት ስም: ተዋዋይ በነበሩት: የደብዳቤ፥ የስልክና የነፋስ መልእክት ምሉክ (Posts Telepone and Telegraph Ministre የፖስታ፥ ቴሌፎንና ቴሌግራፍ ሚኒስትር) በነበሩት: አቶ አማኑኤል አብርሃም በተባሉት ሰው አማካይነት መኾኑ እንደነበረ: እዚህ ላይ ማስታወሱ አግባብ ይኾናል::

ይኹን እንጂ፡ በዚህ መሠረት የተጠናቀረው የቤተ ክህነት ማሳሰቢያ መነሻ ኾኖ፡ የነፋስ ድምፁ ማስተላለፊያ ጣቢያ እንዲቋቋም የተሰጠው የፈቃዱ መልክና ይዘት የሚሻሻልበት መንገድ ይገኝለት እንደኾነ "ያጥና!" ተብሎ፡ በከፍተኛ የአባሎች ደረጃ የተሠየመው፡ ምርፋቅ፡ ተግባሩን ፈጽሞ፡ በጽሑፍ ያቀረበው የውሳኔ አሳብ፡ ምንም ዓይነት ምላሽ ወይም ተፈጻሚነት ሳያገኝ ቀርቶ፡ በመዝገብ ቤት ታሽጎበት ተቀመጠ:: እኔም፡ ወደዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ድርጅት ተዛውሬ እንድሠራ ተደርጎ፡ በዚያ እያገለገልሁ ሣለሁ፡ እንደገና ለአገልግሎት ተጠርቼ፡ ወደቤተ ክህነት በተመለስሁበት ጊዜ፡ ይህንኑ ጉዳይ የሚመለከተውን፡ በቤተ ክህነት የነበረውን የውሳኔውን አሳብ ቅጂ፡ ከመዝገብ ቤት ብጠይቅ፡ አለመኖሩ ተነገረኝ::

በመካከሉ፡ መንግሥታዊው ፈቃድ የተሰጠው፡ አዲሱ የባዕዳኑ፡ የነፋስ ድምፅ ጣቢያ፡ ሥራውን እያካኼደ ሣለ፡ በውሉ መሠረት፡ ከ፳፬ቱ የማስተላለፊያ ሰዓቶቹ ውስጥ፡ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ የተሰጣትን፡ የ፴ ደቂቃ ጊዜ፡ ቤተ ክህነት ተቀብላ እንድትሠራበት፡ ትእዛዝ ተላለፈ፤ ቤተ ክህነትም፡ ያንን ትእዛዝ ባለመቀበል፡ በዚያ ፋንታ፡ በኢትዮጵያ (በአዲስ አበባ) የነፋስ ድምፅ ጣቢያ፡ ለአገር ውስጥ አድማጮቿ፡ በዚያን ወቅት ታስተላልፍ የነበረውን ዝግጅቷን፡ "ለጊዜው ይበቃኛል" በማለት ቀጠለች::

ቤተ ክህነት፡ በዚህ መልክ፡ "አልቀበልም" ያለችውን፡ የ፴ (ሰላሣ) ደቂቃ ስጦታ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ልዩ ጽሕፈት ቤት (Cabinet = ካቢኔ) ውስጥ፡ የመንፈሳዊዉን ሥራ የሚያካኺደው ክፍል፡ ያለቤተ ክህነቱ ስምምነትና ፈቃድ፡ ያው፡ በታወቀው የማናለብኝነት ድፍረት ተረከቦ፡ በእርሱ አማካይነት፡ የሚፈለገው ትምህርትና ስብከት፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም፡ በቀጥታ፡ ይተላለፍ ጀመር! ለዚህም ተግባር፡ ቀንደኛ መሣሪያ ኾነው የተመደቡት፡ በአጼው ልዩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ፡ የመንፈሳዊዉ ክፍል ኃላፊና የአዲስ አበባ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ "ገዳም" (ወይም Cathedral ካቴድራል)፡ ሊቀ ሥልጣናት የነበሩት፥ በዚያን ጊዜ ስማቸው፡ አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ይባሉ የነበሩት መነኲስ ነበሩ:: (Cathedral ካቴድራል ስለሚለው ባዕድ ቃል፡ የተሰጠውን ሐተታ በሚቀጥለው ንዑስ አርእስት ሥር ይመለከቷል::)

በአጼው ልዩ ጽሕፈት ቤት፡ የመንፈሳዊዉ ክፍል አማካይነትና ኃላፊነት፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም፡ በዚያ፡ የባዕዳን ነፋስ ድምፅ ጣቢያ፡ ሲተላለፍ የቆየው፡ ሃይማኖታዊው ትምህርትና መንፈሳዊው ስብከት፡ በዚህ ኹኔታ አልቀጠለም:: ትምህርቱና ስብከቱ ብቻ ሳይኾን፡ ዓለም አቀፉ የነፋስ ድምፅ ማስተላለፊያ ጣቢያ ጭምር፡ በተገላቢጦሽ፡ "እግዚአብሔር የለም" ለሚል የክህደት ርእዮተ ዓለም ማሠራጫ በመኾን፡ ጠቅላላ አገልግሎቱ ተቋርጦ፡ ለመቼውም ጊዜ እንዲቆም ኾነ እንጂ! ይህም፡ ያ ጣቢያ፡ የኢትዮጵያ ሊቀ ካህናትና ንጉሠ ነገሥት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለቅድስት እናቱ፡ ለድንግል ማርያምና በእርሷ ኪዳነ ምሕረትነት፡ በኢትዮጵያ አጽንቶ ላኖረው፡ ለተቀደሰው ቃል ኪዳኑ ማጥቂያ ይኾን ዘንድ፡ በምሥጢርና በሴራ በተዘጋጀው፡ በዚህ ጣቢያ ላይ፡ እንደሌላው ኹሉ፡ በመለኮታዊ ዳኝነቱ የሰጠው ፍርድ፡ በተፈጸመበት ድርጊት፡ ገሃድ ኾኖ ታይቷል::

ነገሩ: እንዲህ መኾኑ ተረጋግጦ ሊታወቅ የቻለው: እግዚአብሔር: ይህን ፍርዱን ያስፈጸመው: ስሙ: "መንግሥቱ: የማርያም ኃይል ነው" የሚል ትርጉም ያለውን: አንድ የተናቀ ተራ ሰው አስነሥቶና መቀመጫውን: በታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ዓፀደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አድርጎ: ጸጋውን: ከአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ነሥቶ: ቊጣውን በገለጠበት በደርግ ዘመን በመኾኑ ነው::

ከእርሱ ዳኝነት የሚያመልጥ ማንም ፍጡር: ወይም ምንም ነገር የለምና! ኢትዮጵያም: ከዚያን ጊዜ ወዲህ: የእግዚአብሔር ስም: በነፋስ ድምፅም ኾነ: በነፋስ ሥዕል አማካይነት: ፈጽሞ የማይጠራባት አገር ኾና ቀረች! እርሱ የቀጠረው ቀን እስኪመጣ ድረስ!

## ኢትዮጵያ:<br>አስተምራ ያሳደገቻቸውን ልጆቿን<br>ስትፋረድ!

እኒያ: ለዚያ: ዓለም-አቀፍ የነፋስ ድምፅ ማስተላለፊያ ጣቢያ: የሴራ አገልግሎት መሣሪያ የነበሩት: ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የሚባሉት መነኩስ: "እውነተኛው ንጉሥ" የሚል: አማናዊ ትርጉም ያለው በመኾኑ: ሊጠሩበት በማይገባ፥ *ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በተሰጠው "መልከ ጼዴቅ" በሚለው ስም:* በዚያው: አሥሮ በፈታቸው ደርግና በአገዛዙ ዘመን: የጵጵስና ሹመትን ተቀበሉ! ዕድላቸውም: ከሾማቸው ደርግ ህልውና ጋር ተሣሥሮ ኖሮ: የእርሱ የጭካኔ ዘመን አብቅቶ: ከሥልጣን ሲወገድ: እርሳቸውም: "እጠብቀዋለሁ! እሞትለታለሁ!" ብለው: ከመለኮታዊው ንጉሥና ንግሥት እናቱ: ሌላው ቢቀር: በምንኵስና ቆባቸው: ቃል ኪዳን የተቀበሉትን የእረኝነት አደራቸውን ጥለው፥ ራሳቸውን "ለማዳን" ወደተማመኑበት: ወደባዕዳን አህጉር: ሸሽተው ሄዱ!

የሚያስገርመውና በእጅጉ የሚያሳዝነው፥ "ይኾናል!" ተብሎ የማይታሰበውም: እርሳቸው ይመሩት በነበረው: በዚያ የአጼው ልዩ ጽሕፈት ቤት: መንፈሳዊ ክፍል ሥር ይካኼዱ በነበሩ ተቋማት ውስጥ ይሠሩና ይማሩ የነበሩት፥ በዚሁ ክፍል አማካይነትም: ለከፍተኛ ትምህርት እየተባለ: ወደእግዚአብሔር የለሾቹ የምሥራቅ አገሮች: እየተፈቀደላቸው: ይላኩ የነበሩት: የቤተ ክህነት ተማሪዎችና ምሁራን: ኋላ: ለዚሁ: ለሃይማኖተ ቢሱ: የደርግ: የዓመፅና የክህደት መንግሥት ዋና አገልጋዮች ኾነው መገኘታቸው ነው:: ከእነዚህ መካከል: እግዚአብሔር-አልባ በኾነው: በኪዩባ የኮሚዩኒስት መንግሥት ዘንድ: የመጀመሪያው የደርግ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ኾነው የተሾሙትን: አቶ አእምሮ ወንድማገኘሁ የተባሉትን፥ እንዲሁም: በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እየተመደቡ ከመሥራታቸው ጋር: በቃለ ዐዋዲ ወጥቶ ይሠራበት የነበረውን: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን የሰበካ ጉባዔ ዓርማና ደንብ: ለደርግ በሚስማማው ዓርማና ደንብ በመለወጥ: በቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን: የደርግ ተጠሪ መሣሪያ በመኾን ያገለገሉትን: አቶ (ኋላ: ሊቀ ማእምራን) አበባው ይግዛውን: በምሳሌነት መጥቀሱ ይበቃል::

እንግዲህ፡ አቶ አእምሮ ወንድማገኘሁና አቶ አበባው ይግዛው፡ የቤተ ክህነት ትምህርት የተማሩና ከቅድስት ሥላሴ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የተመረቁ ደቀ መዛሙርት ይኹኑ እንጂ፡ ዓይነተኞዎቹ አፅራረ ሃይማኖት (communists ኮሚዩኒስቶች) ነበሩ ማለት ነው! በዚህም፡ ኢትዮጵያ፡ በቤተ ምልክናዋ አማካይነት ብቻ ሳይኾን፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ ቀደም ብሎም፡ በቤተ ክህነቷ አማካይነት ጭምር፡ እንዴት ከውስጥ ትገዘገዝ እንደነበረ፡ መለኮታዊው ኃይል፡ ደባውን መገላለጡን እንመለከታለን። ይህንም እውነታ፡ በኹለቱም ሰዎች የቀደመ ድርጊት፡ በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል።

እኔ፡ ቀደም ብዬ፡ በ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. የቤተ ክህነቱ፡ የትምህርት፥ የስብከት፥ የድርሰትና የማስታወቂያ ሥራ መሪ ሣለሁ፡ በጊዜው የነበሩት፡ እጨጌው፡ ብፁዕ አባ ባስልዮስ፥ እንደራሴያቸውም፡ አባ ቴዎፍሎስ፥ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ደግሞ፡ አቶ ልሣኑ ሀብተ ወልድ ይባሉ ነበር። እኒሁ የበላዮቼ ተስማምተውና ፈቅደው፡ በእነርሱ ትእዛዝና ደብዳቤ፡ ለጉዞዬ የሚያስፈልገው መሰናዶ ተዘጋጅቶልኝ፡ ለሥራና ለስብሰባ ወደአሜሪካ አገር ተልኬ፡ በዚያ እያለሁ፡ በአዲስ አበባ የነበረው የአሜሪካ የማስታወቂያ መሥሪያ ቤት፡ ስለጉብኝቴ፡ በተከታታይ፡ ጽሑፍ መግለጫን ያወጣ ኖሮ፡ አቶ አእምሮ ወንድማገኘሁ፡ እኔ በሌለሁበት፡ በድርሰቱና በማስታወቂያው ቦታ ተቀጥረው፡ ስለእኔ ኃላፊነትና ማንነት፥ ስለተልእኮዬም፡ የአሜሪካኑ የማስታወቂያ መሥሪያ ቤት የሰጠውን መግለጫ በማስተባበል፡ በአዲስ ዘመን ጦማረ ሕዝብ (gazetta ጋዜጣ) ሰፊ ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ተደረገ። እኔም፡ ከተልእኮዬ እንደተመለስኩ፡ ለማመን እስኪያቅተኝ ድረስ የተጠራጠርኩትን፡ ይህን ድርጊት፡ በዓይኔ አንብቤ ካረጋገጥኩ በኋላ፡ ተገቢውን የመልስ ማብራሪያ ለ"አዲስ ዘመን" በመስጠት፡ ስሕተቱ እንዲስተካከልና ጉዳዩ እንዲዘጋ አደረግሁ። አቶ አእምሮም፡ የተቀጠሩት፡ ለዚሁ ተልእኮ፡ ማለትም፡ በእኔ ላይ ያን የተቃውሞ ጽሑፍ ለማስተላለፍ ብቻ ይመስል፡ ከእኔ ጋር መሥራቱን ባለመፈለግ፡ በአገልግሎቱ ሳይዘልቁበት፡ ሥራውን ትተውት፡ ወደዓለማዊው ተግባረ ሥጋ ተመለሱ።

ወደቤተ ክህነት የመጣሁት፡ በኢትዮጵያዊነት ተልእኮዬ ለማገልገል እንጂ፡ ለነገርና ለንትርክ ባለመኾኑ፡ ድርጊቱ፡ እኔን በማሳዘን፡ አገልግሎቴ እንዲጨናገፍ ለማድረግ መኾኑን ስለተረዳሁት፡ ጉዳዩን፡ ከሚመለከታቸው ዘንድ፡ በአቤቱታ መልክ ሳይኾን፡ በማሳወቅ ደረጃ ብቻ በማድረስ፡ ሥራዬን ቀጠልኩ። በዚያን ጊዜ፡ ተፃራሪ እንጂ፡ ደጋፊ በሌለበት አካባቢ ያተኮርኩት፡ የቤተ ክህነት ትምህርት ጨርሶ እንዳይጠፋ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በነበረበት ኹኔታ ተጠናክሮ እየቀጠለ፡ ወደፊት፡ በዘመናዊ መልክ ተደራጅቶ ሊስፋፋ የሚችልበትን ጥናት በማካሄዱና እስከዚያው፡ ትምህርቱም፡ ስብከቱም፡ በቃል፥ በድርሰት፥ በሕዝባዊው ጦማርና በነፋስ ድምፅ አማካይነት እንዲተላለፍ በማድረጉ ላይ ነበር። በተለይም፡ በኢትዮጵያ ነፋስ ድምፅ (Radio ራዲዮ)፡ አማካይነት ለሚተላለፈው መልእክት፡ ለየቀኑ ሥርጭት፡ በከፍተኛ ጥረት ያስፈቀድነው ጊዜ፡ ፲፭ ደቂቃ ብቻ ቢኾንም፡ በዚህ ረገድ ለተከናወነው ሥራ፡ ነፋስ ድምፁ፡ ታላቁን አስተዋጽዖ አበርክቷል።

ጥቂት ወራት እንዳለፉ፡ ለተመሳሳይ የቤተ ክህነት ተልእኮ፡ ወደሕንድ አገር እንድጓዝ ታዝዤ ከኼድኩ በኋላ፡ በዚያ፡ የተላክሁበትን ግዳጅ ፈጽሜ በተመለስኩ ጊዜ፡ የገጠመኝ አቀባበል ግን፡ ከቀደመው የባሰ አሳዛኝ ኾኖ አገኘሁት፤ ይኸውም፡ እንዳለፈው ጊዜ፡ ሥራዬ፡ በከፊል፡ ለሌላ የተሰጠበትና በሕዝብ ፊት፡ በይፋ የተዋጣሁበት አልነበረም፤ ጨርሶ፡ ከሥራዬ የተሰናበትኩበት መስተንግዶ ነበረ እንጂ። እንደማናቸውም ጊዜ፡ የጉዞዬ መሰናዶ፡ በነበሩት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ አማካይነት ተዘጋጅቶልኝና ተሰናብቼ የሄድኩ መኾኔ እየታወቀ፡ "ሥራውን ትቶ ወዴት እንደሄደ ስላልታወቀ፡ ወደፊት፡ ሌላ ኀላፊ በቦታው እስኪተካበት ድረስ፡ የቤተ ክህነቱ ዋና ጸሓፊ፡ ሥራውን በተጠባባቂነት እንዲያካኺድ" በሚል መልክ፡ አንድ ደብዳቤ፡ ወዲያው እንደኼድኩ፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ጽሑፍ ኪዳን (firma ፊርማ)፡ ለሚመለከታቸው ኹሉ ተላልፎ፥ ለእኔ የተዘጋጀልኝንም ቅጂ፡ እኔ፡ ወደአገሬና ወደሥራዬ ስመለስ አገኘሁት።

በዚህ ጊዜ፡ ጉዳዩን ከእጨጌውና ከእንደራሴው ከማድረስ በቀር፡ ሌላ ዕድል ስላልነበረኝ፡ አቀረብኩላቸው። እነርሱም ድርጊቱን ያላወቁ መኾናቸውን ከገለጹልኝና ደብዳቤው፡ በደብዳቤ እንዲሻር ካደረጉ በኋላ፡ አሁንም፡ ሥራዬን ቀጠልኩ። ይኹን እንጂ፡ የበላዮቼ፡ እነርሱ ባሉበት፡ ይህን የመሰለው፡ ሥርዓት-አልባና ይሉኝታ ቢስ የኾነ የማጥቃት በደል፡ በግልጽ የሚፈጸም ከኾነ፡ በዚያ ቦታ መቆየቱ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ አስፈላጊ መስሎ የማይታየኝ ኾነ! የቤተ ምልክናው (የመንግሥት) ተሿሚ በኾነው፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ብቻ፡ በእኔ የሥራ መደብ ላይ፡ በዚያ መልክ፡ በቀጥታና በተከታታይ የተላለፉት፡ እነዚያ ውሳኔዎች፡ የዚያ፡ የዓለም-አቀፉ ነፋስ ድምፅ ማስተላለፊያ ጣቢያ ውዝግብ ውጤቶች መኾናቸውንም የተገነዘብኩት ብዙ ቆይቼ ነበር፤ እንደዛሬው ኹሉ፡ በዚያን፡ የወጣትነት ዕድሜና የቅንዓት አገልግሎት ጊዜም፡ በቅንነትና በትጋት ከመሥራት በቀር፡ በተለይ፡ በቤተ ክህነት አካባቢ፡ በበላዮችም ኾነ በሥራ ባልደረቦች ዘንድ፡ ያን የመሰለ የተንኰልና የመሠሪነት ክፉ መንፈስ "ይኖራል!" ብዬ በፍጹም አልጠረጠርም ነበርና።

በዚህ ጊዜ፡ ፈጣሪዬ፡ መሥራት ወደምችልበት ቦታ የምዛወርበትን መንገድ አዘጋጀልኝ። ይኸውም፡ በቤተ ክህነት የትምህርት ክፍል ሥራ መሪነቴ፡ የታዕካ ነገሥት በዓታ ገዳምን የያዘው፡ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ድርጅት፡ የባለአደራው ምርፋቅ (Board ቦርድ) አባል ስለነበርኩ፡ በአባልነቴ የነበረኝን ንቁ ተሳትፎና የማቀርባቸውን የዕቅድ አሳቦች በመመልከት ይመስለኛል፡ ምርፋቁ፡ ለድርጅቱ ንብረት አስተዳዳሪነትና ሥራ አስፈጻሚነት ኀላፊነት አጭቶኝ ኖሮ፡ ጉዳዩን፡ ለአጼው አቅርቦ፡ ወደዚያ አገልግሎት ተዛውሬ እንድሠራ ተደረገ።

በዚያም፡ ኹለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፡ ቤተ ክርስቲያኑ፥ ትምህርት ቤቱ፥ ጡረታ ቤቱና ጽሕፈት ቤቱ፡ በተቻለ መጠን እንዲሟሉ ከመሞከር ጋር፡ በየክፍላተ አገሩ ያሉት፡ የመታሰቢያ ቤቱ የገጠር ሰበካዎች፡ ጥቅማቸውን ብቻ መሰብሰብ ሳይኾን፡ ተገቢውን ግልጋሎት እንዲያገኙ ለማድረግ፡ በቅድሚያ፡ እነርሱን እየተዘዋወሩ በመጎብኘት፥ በአዲስ አበባ ያሉትንም ቦታዎች፡ ርስትነታቸው እየተረጋገጠ፡ በቢጋር (Carta ካርታ) ተነሥተው፡ የባለቤትነት ማስረጃን፡ ከማዘጋጃ ቤት በመረከብና "ዘውዲቱ" የተባለውን ሕንፃ፡ በመኻል አራዳ በማሠራት፡ ዓቅም የፈቀደውን አገልግሎት ለማበርከት ተችሏል።

ለቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅነት፡ አቶ ሠይፉ ሚካኤል የተባሉትን ካቶሊካዊ ሳይቀር፡ ሸዋ የነበረው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ በእርሳቸው ቦታ፡ ከላይ ስማቸውና ግብራቸው የተገለጸውን፡ አቶ ልሳኑ ሀብተ ወልድን የመሰሉትን ሰዎች፡ ለቤተ ክህነት ዕድገት፡ ቁልፍ በኾነው፡ በዚያ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ላይ ለምን ያስቀምጣቸው እንደነበረ ለመረዳት፡ በተለይ ለዚህ መጽሐፍ አንባቢ የሚያዳግት አይኾንም።

በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ዋናው፡ በንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም፥ ምክትልነቱም፡ በኹለቱ፡ በአባ (ኋላ ንቡረ እድ) ገብረ ሥላሴና በአቶ መኰንን ዘውዴ ተይዞ የነበረውን፡ የቤተ ክህነቱን ጠቅላላ የሥራ አስኪያሃጅነት ኃላፊነት፡ እኔ ብቻዬን፡ አጠቃልዬ ስረከብ፡ በተለይ በዚያ ቀውጢ ጊዜ፡ ሥራው፡ ለአንድ ሰው፡ እጅግ ከባድና ሰፊ እንደሚኾን መገንዘብ፡ ለማንም አያዳግትም። ስለዚህ፡ "ለሥራው ይረዳሉ፥ ፈቃደኛም ይኾናሉ" ብዬ በማሰብ፡ ወደቤተ ክህነት እንዲመጡ ብዙዎችን ጠየቅሁ፤ እነርሱ ግን፡ ሥራውን ለመቀበል ፍላጎት የሌላቸው ኾነው አገኘኋቸው።

ቤተ ክህነት፡ በዚያን ጊዜ በነበረው፡ በተለይ በዘመናዊ ትምህርት በታነፀው ትውልድ ዘንድ፡ እጅግ የተናቀች ብቻ ሳትኾን፡ የተጠላችም ነበረች። እንኳንስ ሌላው፥ ራሷ፡ በአገር ውስጥም ኾነ፡ ወደውጭ ልካ ያስተማረቻቸው፡ ልጆቿ ሳይቀሩ፡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከተመረቁ በኋላ፡ መቀጠር የሚፈልጉትና የሚመደቡት፡ ከፍተኛ ደመወዝ በሚገኝበትና የላቀ ክብር በሚሰጠው፡ በቤተ ምልክናው (በመንግሥት) መሥሪያ ቤቶች፥ ወይም፡ በንግድና በውጭ ድርጅቶች ውስጥ ባለው የሥራ ቦታ ላይ እንጂ፡ በቤተ ክህነት ስላልኾነ፡ በሥራ ለመመደብ ቀርቶ፡ ለምክር እንኳ ሲጠሩ፡ ወደቤተ ክህነት ለመቅረብ የሚከብዳቸው፡ ብዙዎች እንዳነበሩ፡ በድፍረት መናገር ይቻላል። በዚያን ጊዜ፡ በቤተ ክህነት በኩል፡ "ይህ ጎድሏል! ይህ ተሳስቷል! ይህ ሊደረግ ይገባል!" እያሉ፡ በቀዳሚነት የሚተቹና የሚነቅፉ፡ እነዚሁ እንደነበሩም ይታወሳል። ዳሩ ግን፡ ያን ጉድለት፡ እንዲያሟላላቸው፥ ያነንም ስሕተት፡ እንዲያስተካክልላቸው የሚጠብቁት፡ ማንን እንደኾነ ለማወቅ ያዳግታል! ባዕዱን፡ ከውጭ? ወይስ፡ መልአክን፡ ከሰማይ?

ለዚህም፡ Dr. (ዶክተር = ሊቀ ምሁር) ጌታቸው ኃይሌ የተባሉትን ሰው፡ ከአያሌዎቹ ዘመናውያን፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት መካከል፡ በቀንደኛ ምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። እኚህ Dr. ጌታቸው፡ ከእኔ በፊት፡ ለቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅነት፡ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ታጭተው፥ ሹመታቸው፡ በአጼው ስለጸደቀ፡ በአዋጅ ተነገሮ፡ ማለትም፡ በዜና ማሠራጫዎችና በሕዝብ መገናኛዎች ከተላለፈ በኋላ፡ እርሳቸው ግን፡ ይህን የአገልግሎት ጥሪ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይኾኑ በመቅረታቸው፡ ጥሪው፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ የባሕር ማዶ ትምህርትና ማዕርግ ወደሌለኝ፡ ወደእኔ፡ ወደአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ በተላለፈ ጊዜ፡ መቀበሌን፡ እዚህ ላይ ማዘከር፡ አግባብ ይመስለኛል።

ቤተ ክህነት፡ ወደውጭ አገር ድረስ ልካ ያስተማረቻቸውና እርሷን ለማገልገል፡ "እምቢ!" ያሉት፡ እኒያ Dr. (ዶክተር) ጌታቸው ኃይሌ፡ ኋላ፡ እግዚአብሔር አልባው ደርግ፡ በትረ መንግሥቱን ጨብጦ፡ ሰይጣናዊ አውታሮቹን በመላ ኢትዮጵያ በዘረጋባቸው፡ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት፡ ለግፍ አገዛዙ እንዲያመቸው ባቋቋማቸው በብሔራዊ ሸንጎና በቤተ ክህነት የተሐድሶ ጉባዔ ውስጥ አባል ኾነው ለማገልገል ፈቃደኛ ኾኑ!

ይኹን እንጂ፡ በዚያ አገልግሎታቸው ላይ እያሉ፡ በእርሳቸውና በደርግ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት፡ ያ የተወጠነው ሰብአዊ ዓላማ፡ ብዙም ዕድሜ ሳይኖረው፡ በአጭር ተቀጨ! ደርግ፡ ለሞታቸው፡ በእርሳቸው ላይ የሠነዘረው ሠይፍ፡ በተአምር ተቀይደና የአካል ጉዳትን ብቻ በማስከተል ተወሰኖ፡ እነሆ ዛሬ፡ ሕይወታቸው ተርፎ፡ በአንድ የአሜሪካ መካነ አእምሮ ውስጥ ይኖራሉ፤ በዚያም፡ ዝግጅታቸው፡ ቀደም ብሎ፡ በእኔ የአገልግሎት ዘመን፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ትብብር የተጠናቀቀውንና በረቂቅ የሥዕል ሰፋድል (microfilm) የተቀረጹትን የኢትዮጵያን ጥንታውያን ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በየስማቸውና በየዓይነታቸው በመመዝገብ፥ በእነርሱም ላይ ዝርዝር ጥናት በማድረግ ይሠራሉ።

እኔም፡ እርሳቸው "አልቀበልም!" ብለው የተዉትን፡ ያን ኃላፊነት በተረከብኩበት ጊዜ፡ ከላይ በገለጽኳቸው ችግሮች የተነሣ፡ የገባሁበትን ግዳጅ ለመወጣት፡ ሌላ ማማረጫ ስላልነበረኝ፡ በቤተ ክህነቱ ውስጥ፡ ቀደም ብለው ከነበሩት በቀር፡ በቅርብ የማውቃቸውን፥ በዚያ በኩልም የማይሳካልኝ ቢኾን፡ ሌሎችን፡ ከየመሥሪያ ቤቶቻቸው፡ በልመናና በጊዜያዊ የዝውውር ፈቃድ፡ በኃላፊነቱ ድርሻ እንዲሳተፉ እየጋበዝሁ፡ ሥራውን እንዲቀበሉ እስከማድረግ መድረሴ ይታወሰኛል። ከእነዚህ መካከል፡ ፈቃደኞች ባለመኾናቸው የቀሩትን ትቼ፡ ፈቃደኞች ኾነው ጥሪውን የተቀበሉትን፡ ጥቂቶቹን ብቻ ብጠቅሳቸው፡ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት፡ መምሬ (ኋላ፡ መጋቤ ካህናት) ዘውዴ ወልደ ማርያም፥ ከትምህርት ምልክና፡ ቄስ (ኋላ ሊቀ ካህናት) ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ፥ ከእርሻ ምልክና፡ አቶ (ኋላ አለቃ) ሴም ከበደ፥ ከግል ሥራ፡ አቶ ገና ደስታ፥ ከአዲስ አበባ ውኃ ፍሳሽ መሥሪያ ቤት፡ አቶ ኤልያስ ሠይፈ፥ ከቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መካነ አእምሮ፡ አቶ (ኋላ፡ ሊቀ ማእምራን) አበባው ይግዛው፡ ወደቤተ ክህነት ተዛውረው፡ አገልግሎት መስጠት የጀመሩት ይገኙባቸዋል።

በዚህ ረገድ የተደረገውም ጥረት ቢኾን፡ "በተደላደለ መልኩ ተሳክቷል፤ የሚፈለገውንም ፍሬ አስገኝቷል" ሊባል እንዳልተቻለ፡ ከፈቃደኞቹ መካከል፡ በአንደኛው፡ በአቶ አበባው ይግዛው በኩል፡ ወዲያው ተከታትሎ የተፈጸመውን ያልታሰበ ድርጊት፡ በምሳሌነት መመልከቱ ይበቃል። አቶ አበባው ይግዛው፡ በአገር ውስጥ፡ በዘመናዊ ሥርዓት ይሰጥ የነበረውን፡ መንፈሳዊውን ትምህርት ጨርሰው፡ ለከፍተኛ ትምህርት ተልከው ከቆዩባት፡ ከዚያን ጊዜዋ የኮሚዩኒስት ሩማንያ ተመልሰው፡ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (የዛሬው የአዲስ አበባ) መካነ አእምሮ (University) ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ተመድበው ይሠሩ ነበረ፤ በዚያን ዘመን፡ የመካነ አእምሮው ሙሴ (President) ከነበሩት፡ ከDr. (ዶክተር) አክሊሉ ሀብቴ ጋር በመመካከር፡ በእርሳቸው ተፅዕኖና ድጋፍ ጭምር፡ አቶ አበባው፡ ያውም፡ በጊዜያዊነትና በዝውውር መልክ ብቻ፡ ወደቤተ ክህነት መጥተው፡ በመምሪያ ኃላፊነት ደረጃ ለመሥራት ተስማሙልኝ። እዚያም፡ በሙያቸው የሚያገለግሉበትን የመምሪያ ኃላፊነት ይዘው፡ ለጥቂት ወራት ከሠሩ በኋላ፡ "ወደነበርኩበት መካነ አእምሮ ሥራዬ መመለስ አለብኝ!" ብለው፡ ድንገተኛ ጥያቄ አቀረቡልኝ፤ እንዲቀዩ ቢለመኑም፡ የማይቻል ኾነ፤ እንዲያውም፡ በመካነ አእምሮው ውስጥ የነበራቸው የሥራ መደብና ለወደፊት የሚጠብቃቸው ዕድል እንደሚበላሽባቸው በምሬት ላቀረቡት ጥያቄ፡ ራሳቸው የመካነ አእምሮው ሙሴ፡ ምንም ችግር እንደማይኖር ቢያረጋግጡላቸውም፡ ለመቆየት ፈቃደኛ ሳይኾኑ ቀሩ።

በመጨረሻ፡ በምንም መልኩ "በቂ ነው" ተብሎ ሊነገር በማይቻለው ምክንያት፡ እንደፍላጎታቸውና ጥያቄያቸው፡ ወደነበሩበት ሥራ መመለሳቸውን፡ በቅሬታ አስታውሰዋለሁ:: የኋላ ኋላም፡ በገሃድ ፈጽመውት በታየው ድርጊታቸው፡ "ለካ! ያ ኹሉ መቅበጥበጥና "አብዮታዊ" እምቢታ፡ ጊዜውን ይጠብቅ ለነበረው፡ ለእግዚአብሔር የለሹ ደርግ፡ የተዘጋጁበትን የጋርዮሽ (ኮሚዩኒስታዊ) አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉበትን መንገድ ለማመቻቸት ኖርዋልና!" ብዬ በአንክሮ አስተዋልሁት::

እኔ፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅነት፡ ወደቤተ ክህነት ከመምጣቴ በፊት፡ የቤተ ክህነት፡ የልማት ባለአደራ ምርፋቅ (Commission ኮሚሽን) ዋና ጸሓፊና ሥራ መሪ ኾነው ተመድበው ሲያገለግሉ የቆዩት፡ አቶ ጌታነህ በጋለ፥ እንዲሁም፡ ስማቸው፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሱት ሌሎቹ የቤተ ክህነት የክፍል ኀላፊዎች ጭምር፡ ኹሉም፡ የደርግ አገልጋዮች ኾነው መገኘታቸውን ሳስበው ይገርመኛል! በተለይም፡ ስማቸው፡ በመጨረሻ የተጠቀሱት፡ አቶ ጌታነህ፡ በደርግ እሥር ቤት ውስጥ፡ ለወራት ታግተው ከቆዩ በኋላ፡ ከእሥር ተፈትተው፡ በኢየሩሳሌም፡ የዚያው የደርግ መንግሥት ተጠሪ እስከመኾን በደረሰ ሥልጣንና ማዕርግ፡ ዋና አገልጋይ መኾናቸው ያስደንቀኛል:: ይህም ማለት፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ "አገልጋይ ነኝ" ሲል ቆይቶ፥ በዚያም፡ "የመስቀሉን መከራ ተቀብያለሁ" ሊል ይችል የነበረው፡ ያው አንዱ ሰው፡ ራሱን፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጦ፡ የዲያብሎስ አገልጋይ ሊኾን የመቻሉ ነገር ነው፤ "እግዚአብሔር የለም!" የሚለው፡ የደርግ የጋርዮሹ (communist የኮሚዩኒስቱ) መንግሥት አገልጋይ መኾን፡ በቀጥታና በገሃድ፡ የዲያብሎስ አገልጋይ መኾን ነውና::

## ኢትዮጵያ፡ ስለገዳምና "ካቴድራል" ስለሚለው ስያሜ ስትፋረድ!

ከላይ፡ ቀደም ብሎ፡ በአጋጣሚ፡ የተነሣውን፡ የአዲስ አበባውን መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በሚመለከት፡ በተለይ፡ "ገዳም" ወይም Cathedral (ካቴድራል) ስለሚለው ስሙ ብቻ፡ ከዚህ የሚከተለውን ሐተታ ሰጥቶ ማለፍ ግድ ይኾናል::

በእውነተኞች ኢትዮጵያውያን ሕጋውያን ካህናት ተቈርቋሪ፡ በ"ደብር" ደረጃ፡ ይገለገል ለነበረውና ኋላ፡ በአዲስ ዘመናዊ ሕንፃ ለተስፋፋው፡ ለቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፡ "መንበረ ጸባዖት" የሚለው፡ የጥንቱ የማዕርግ ስያሜው ይበቃው ነበር:: ከጊዜ በኋላ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ ቈርቋሪዎቹ ሕጋውያን ካህናት ተከልክለው፥ ማለትም፡ በጥንታዊው ቤተ መቅደስ ብቻ እንዲወሰኑ ተደርጎ፡ መነኮሳት ብቻ የሚቀድሱበት "ገዳም" ኾኗል ተባለ! ይህም አልበቃ ብሎ፡ ካቶሊካውያንና ግሪኮች በሚጠቀሙበት፥ ኢትዮጵያዊም ባልኾነ፡ Cathedral (ካቴድራል) በሚለው፡ የሌላ ሃይማኖት መለያና መታወቂያ በኾነ ስም እንዲጠራ ተደረገ!

Cathedral (ካቴድራል) የሚለው ቃል፡ በቃልነቱ፡ የሚጎዳ ነገር ኖሮበት አይደለም! ነገር ግን፡ አለቦታው፡ ምን ያደርጋል? ለምን አስፈለገ? ቃላት ሳናጣ!? በተለይ፡ በዚህ ቤተ መቅደስ ላይ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊዘነቅ የተፈለገበት ምክንያት፡ ከቶ ምን ዓላማ ቢኖር ነው?

ቃሉ፡ ላቲን ነው፤ ታዲያ፥ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ላቲን ምናችን ነው? ትርጉሙም፡ ለባዕዳኑ ሃይማኖት፡ Cathedra (ካቴድራ) "ወንበር" ከሚለው፡ ጥሬ ዘር የወጣ ኾኖ፡ Cathedral (ካቴድራል) የሚለው፡ "ወንበራዊ"፡ ወይም "መንበራዊ"፡ ወይም "የጳጳስ ወንበር"፡ ወይም "መንበረ ጳጳስ"፡ ወይም "የጳጳስ ወንበር ያለበት ቤተ መቅደስ" ማለት ነው።

ይህ ዓይነቱ ስያሜ፡ ይህን ለመሰለው ኢትዮጵያዊ ደብር፡ "ይገባዋል" ብሎ ተቀብሎ ማጽደቅ፡ ኢትዮጵያውያን፡ Orthodox (ኦርቶዶክስ) የሚለውን ባዕድ ቃል በመቀበላቸው፡ እየደረሰባቸው እንዳለው ጠንቀኛ ችግር ኹሉ፡ ደብሩንም፡ ኢትዮጵያዊ የሚያሰኘውን፡ ተዋህዶነቱን ማሳጣት ስለሚኾን፡ እጅግ ይከብዳል፤ ይህን ስም በመስጠታቸው፡ በኃላፊነት ተጠያቂዎች ከኾኑት ግለሰቦችና በእነርሱ መሣሪያነት፡ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ከተነሣሡት ባዕዳንም ጋር፡ ራስን፡ እንደማስተባበር ያስቆጥራል። ሕጋውያኑ ካህናት፡ ይህንኑ ደብር ቈርቍረው በማሳደግ፡ ዕድሜአቸውን ሙሉ፡ በሕይወታቸው የከፈሉትን፡ ንጹሕ የአገልግሎት መሥዋዕትነት፡ ከንቱ ማድረግም ይኾናል። ከእኒያ፡ ቈርቋሪዎች ሕጋውያን ካህናት መካከል፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን፡ የደብሩን ጽላት፡ ከተጉለት ይዘው መጥተው፡ ከመቃኞው ጀምረው፡ ከነልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው፡ በከፍተኛ ኃላፊነት ሲያገለግሉት የኖሩትን፥ ኋላም፡ ለአዲሱ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ይኾን ዘንድ፡ መኖሪያ ቦታቸውን ሳይቀር እስከመልቀቅ በደረሰ ፍቅርና ታማኝነት፡ ለደብሩ ደህንነት የተጋደሉትን፡ የትልቁ መምሬ ወልደ ኢየሱስ የልጅ ልጅ፡ የእመት ወለተ ኪሮስ ፍልፍሌን ባለቤት፡ መምሬ አምኃ ሥላሴን የመሰሉትን ካህን፡ በቀዳሚ ምሳሌነት መጥቀሱ ይበቃል። ይኹን እንጂ፡ ዛሬ፡ የክህነት ፈለጋቸውን የተከተሉት፡ ሕጋውያን የልጅ ልጆቻቸው፡ "ደብሩ፡ ገዳም ኾኗልና፡ መነኰሳት ስላልኾናችሁ፡ ቤተ መቅደስ ገብታችሁ፡ መቀደስም፥ ሌላውንም፡ ክህነታዊ አገልግሎት መስጠት አትችሉም!" ተብለው፡ መታገዳቸውንና መከልከላቸውን፡ በኀዘን ተቀብለውት ይኖራሉ።

ከዚህ፡ Cathedral (ካቴድራል) ከሚለው፡ የባዕዳን ቃል ይልቅ፡ "መንበረ ጸባዖት" ከሚለው ጋር የሚኼድ ስያሜ ካስፈለገ፡ ወትሮም ኾነ ዛሬ፡ "ርእሰ አድባራት" ወይም፡ በገዳምነቱ ይቀጥል ከተባለ፡ "ርእሰ ገዳማት" የሚለውን የማዕርግ ስም መስጠቱ፡ በበቃም ነበር። ቀድሞውንም ቢኾን፡ ታማኝ የእግዚአብሔር ተጠሪና ተቆርቋሪ የሃይማኖት ተመልካች ኢትዮጵያዊ ጠፍቶ ነው እንጂ፡ የሥላሴ መንበር የተዘረጋበት መኾኑን በሚገልጸው፡ "መንበረ ጸባዖት" በሚለው፡ በባለቤቱ በግእዝ ስያሜ ላይ፡ ወይም እርሱ ተነሥቶ፡ በምትኩ የጳጳስ መንበር የተቀመጠበት መኾኑን፡ በይፋ የሚያስታውቀው፡ "ካቴድራል" የሚለው፡ የባዕዳን ቃል ተዘንቆ እንዲሠለጥን ለማድረግ የሚደፍር ሰው፡ እንዴት ሊኖር ይችል ነበር? አዎን! ዘመኑ፡ እንደትንቢቱ ቃል፡ ጳጳሳት፡ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ፡ የራሳቸው ክብር፡ በካህናቱም ኾነ በሕዝቡ፥ በባለሥልጣኖችም ፊት በልጦ እንዲታይ፥ እንደእግዚአብሔር ወይም ከዚያ በላይ ሊመለኩ የሚፈልጉበት ጊዜ ስለኾነ፡ ድርጊቱ ላያስደንቅ ይችላል። ከዚህም ጋር፡ በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው አኗኗር፡ ኢትዮጵያዊ የኾነውን ኹሉ፡ የመናቅና የመጥላት በሽታ የጸናበት፥ ከዚህም የተነሣ፡ ራስን ለባዕዳን የማስገዛት ባሕርይ የሰፈነበት ዘመን በመኾኑ፡ ባሁኑ ጊዜ፡ ይህን የመሰለው አድራጎት፡ ቤተ ክህነቱን ጨምሮ፡ በኢትዮጵያዊው ትውልድ ዘንድ፡ በስፋት እየተካኼደ መታየቱ፡ ከቶ አያስደንቅም።

ደግሞስ: ይኸው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን: በደብርነቱ እያደገና በአገልግሎቱ እየተስፋፋ እንዲሄድ በማድረግ ፋንታ: ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጪ ካልኾነ በቀር: በኢትዮጵያውያን ሥርዓት: "ገዳም" በከተማ ውስጥ ማቋቋም የማይፈቀድ መኾኑ እየታወቀ: ለምን ወደገዳምነት እንዲቀየር ተደረገ? ይህስ ለምን አስፈለገ?

ራሱ: የግእዙ ቃል ትርጉም እንደሚያስረዳው: "ገዳም" ማለት: "ዱር÷ ጫካ÷ በረሃ÷ ምድረ በዳ÷ ከሃገር ወይም ከከተማ ወይም ከመንደር እንኳ ሳይቀር: የራቀ: አራዊት የሚኖሩበት÷ በደለኛ ሸሽቶ የሚጠጋበትና ደውሉ የሚማጠንበት ቤተ ክርስቲያን ያለበት: የባሕታውያንና የመነኮሳት ሠፈር" ማለት ነው:: በአገራችን: እንደደብረ ሊባኖስ÷ እንደዝቋላ÷ እንደደብረ ዳሞ÷ እንደዋልድባ÷ በውጭም: በምድረ ከነዓን: እንደገዳመ ቆሮንቶስ÷ በግብፅም: እንደገዳመ አስቄጥስ ማለት ነው:: በዚያ የሚኖሩትም: "ገዳማውያን" ይባላሉ፤ በነጠላ: "ገዳማዊ" ማለት: "የገዳም ሰው÷ በረኸኛ÷ መነኰሴ ወይም ባሕታዊ" ማለት ነው::

እንግዲህ: ኢትዮጵያውያን: በቤተ ክህነታቸው አቋምና ሥርዓት÷ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም እንደደነገገው: ቤተ መቅደሳቸውን: በመንደር ሲኾን: "ገጠር"÷ በከተማ ሲኾን: "ደብር"÷ በበረሃ ሲኾን: "ገዳም" ብለው እያቋቋሙ: በጋብቻ ቃል ኪዳን ተወስነው: ሕይወታቸውን: በፈቃዳቸው: ለፈጣሪያቸው አገልግሎት የሰጡትን ካህናት: በገጠር ቤተ መቅደሶችና በከተማ አድባራት በመመደብ÷ በድንግልና÷ በብሕትውና ወይም በምንኵስና ቃል ኪዳን ተወስነው: ሕይወታቸውን: በፈቃዳቸው: ለፈጣሪያቸው አገልግሎት የሰጡት ደግሞ: ራሳቸውን: በበረሃ ገዳማት እየወሰኑ÷ በእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ተቋማት ውስጥ የሚመደቡትም ኹሉ: ይህን ሥርዓት: እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አክብረውና ጠብቀው ኖረዋል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን: ከጥንት ጀምሮ: በሥርዓተ ጋብቻ ላይ ተመሥርቶ የኖረውን: የኢትዮጵያውያንን የሊቀ ካህናትነት መንበር: የኋላኋላ ደምስሶ በተተካው: በግብፃውያን የምንኵስና ሥርዓት: የቤተ ክህነቱን ሥልጣን የጨበጡት ጳጳሳት: ራሳቸው መነኩሳት በመኾናቸው: በእነርሱ ደጋፊነት ጭምር: በዚሁ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣን ዘመን: እነሆ: ይህ: ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በድፍረት ተጥሶና ተሽሮ ይታያል:: ይህም ትርኢት: ገዳማውያን የኾኑት መነኩሳት: ራሳቸውን: ወደከተማ ካህናትነት ለውጠው: ያገር ውስጥ ከተሞችን ብቻ ሳይኾን: የውጭ አህጉር ከተሞችን ጭምር በማጥለቀለቃቸው: በተገላቢጦሽ: የከተማ አድባራትን: ወደገዳምነት÷ የበረሃ ገዳማትንም: ወደከተማ ደብርነት የቀየሩዋቸው መኾናቸው ተረጋግጦ የሚታይበትና የዛሬዎቹ የቤተ ክህነት መሪዎች: በተለመደው: የማናለብኝነት ድፍረት: በዚህ ረገድ እንዲቀጥል የገፉበት ድርጊት ነው:: ይህንንም ድርጊት: በጊዜያችን: በእውን ሲፈጸም በሚታየው ኹኔታ: ገዝፎ እንመለከተዋለን፤ ይኸውም: እኒያ ሕጋውያን ካህናት: መሥዋዕት ኾነው በቈረቈሩዋቸውና በደከሙባቸው÷ ባገልግሎታቸውና በሹመታቸውም ባስከበሩዋቸው: በአዲስ አበባና በሌሎቹ ከተሞች ውስጥ ባሉ አድባራት: እነርሱ እየተገለሉ: በቦታቸው: ለደመወዝ እየተባለ: በእልቅናና በአስተዳዳሪነት መሾም ብቻ ሳይኾን: በተራው ሰሞነኛነት ሳይቀር የሚመደቡት መነኩሳት ብቻ በመኾናቸው ነው:: ለነገሩማ: ለዕለት ጉርስና ለዓመት ልብስ ከሚቀርብላቸው በቀር: ደመወዝና ንብረት: ለመነኩሳትና ለጳጳሳት ምናቸው ነው? ሲመነኰሱ: "ንቀን ትተነዋል!" ያሉት አልነበረምን?

ሕጋውያኑ ካህናት፡ ስለከፈሉት መሥዋዕትነት ከሚያስረዱት፡ ከብዙዎቹ ኹኔታዎች መካከል፡ ራሴ የማውቀውን፡ አንዱን ብቻ፡ እዚህ ላይ በምሳሌነት አቀርበዋለሁ። ይህም፡ ቄሰ ገበዝ ወልደ ኢየሱስ አምኃ የተባሉት፡ ስማቸው፡ ከላይ በተጠቀሰው፡ በአንዱ፡ የመምሬ አምኃ ሥላሴ ልጅ ላይ የደረሰውን፡ የሚመለከት ነው። አባታቸው፡ ለመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ደብር መቋቋምና ህልውና እንዳደረጉት ኹሉ፡ እኝህም ካህን፡ የአዲስ አበባን መካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን፡ ከመቈርቈሩ ጀምሮ፡ ደብር ለመኾን እስከበቃበት ዘመን ድረስ፥ ከዚያም በኋላ፡ ዕድሜያቸውን ሙሉ፡ በቄሰ ግብዝና ሥልጣን አገልግለውታል።

በዚያ የኃላፊነት አገልግሎታቸው ላይ ሣሉ፡ ፋሺስት ጣልያን፡ ኢትዮጵያን በግፍ ወርሮ፡ አዲስ አበባ ገባ፤ ወዲያው፡ ከወራሪው ጦር አዛዦች መካከል፡ ለከተማዋ ደቡብ ክፍል አላፊ የኾነው፡ አንዱ ዋና አዛዥ፡ የዚህኑ የቅዱስ ቂርቆስን ደብር ቤተ መቅደስ፡ ለጦር መሣሪያው ግምጃ ቤትነት፥ ዓፀደ ቤተ ክርስቲያኑንም፡ ለሠራዊቱ ምሽግነት፡ እጅግ ተስማሚ ኾኖ አግኝቶት ኖሮ፡ አንድ ቀን፡ ከቀትር በኋላ ባለው ጊዜ፡ እዚያው፡ እቤተ ክርስቲያኑ ድረስ መጥቶ፡ ቄሰ ገበዝ ወልደ ኢየሱስን አስጠራቸውና፡ ቤተ መቅደሱን እንዲከፍቱ አዘዛቸው፤ እርሳቸው ግን፡ በዚያን ሰዓት፡ ማንም ሰው፡ ወደቤተ መቅደስ ለመግባት የማይችል መኾኑን ገለጹለት። እርሱም፡ ባልጠበቀው ኹኔታ ትእዛዙ ሳይፈጸም በመቅረቱ፡ ተቆጥቶና ተበሳጭቶ፡ ሽጒጡን መዘዘና በግንባራቸው ላይ አነጣጥሮ፡ "ክፈት ነው የምልህ!" ብሎ፡ በታወቀው የዕብሪተኞች አባዜ ጮኸባቸው። እርሳቸው ግን፡ አስተርጓሚውና ሌሎቹ ሓማሴኖች፥ ነጮቹም የፋሺስት ወታደሮች እስኪገረሙ ድረስ፡ ከነገሩት ቃል ውጪ ምንም ማድረግ የማይችሉ መኾናቸውን አረጋገጡለት። በዚያን ጊዜ፡ አስተርጓሚው፡ "ሰውዬው፡ ግልፍተኛ ነውና፡ ተኩሶ እንዳይጨርስዎ፡ እባክዎ፡ 'እሺ!' ብለው ይክፈቱ!" በሚል የጭንቀት ንግግር ቢማፀናቸውም፡ ያን ቸል ብለው፡ "እንኳን፡ አንተ፡ እኔም ብኾን፡ በዚህ ሰዓት፡ ወደቤተ መቅደስ መግባት አይፈቀድልኝም በለው!" ሲሉ አሁንም፡ በረጋ መንፈስና በትሕትና፡ መልስ ሰጡት።

ቄሰ ገበዝ፡ የገድል ሕይወታቸውን ፈጽመውና የሞታቸውን ጽዋ ተቀብለው የሚያርፉባት ዕለት፡ ገና አልደረሰች ኖራ፡ ያ ግፈኛ ጠላት፡ በእርሳቸው ላይ የደገነውን፡ የጦር መሣሪያውን፡ በተአምራዊ ኃይል፡ ከእርሳቸው ግንባር፡ ድንገት መለስ አድርጎ፡ ወደተቆለፈው፡ የቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ፡ ተንደርድሮ ኼዶ፡ ያንን በራፍ፡ በዚያ ቅልጥም ሙሉ ጫማው፡ በኃለ ቁጣና ንዴት ቢጠልዘው፡ ብርግድ አለ! ወደቅድስቱም ዘው ብሎ ገብቶ፡ የመቅደሱን በር፡ በአረማዊ ድፍረቱና ርኵሰቱ፡ እንደዚያው፡ በጫማው ቢረግጠው ተከፈተለት! ወዲያው፡ የመቅደሱን መጋረጃ ገልጦ፡ ወደውስጥ ሊገባ፡ እግሩን ብድግ ሲያደርግ፡ ድንገት፡ ከፊቱ አንዳች የገፈተረው ነገር ያለ ይመስል፡ ወደኋላው ምልስ አለ! እንደገና ሞከረ! ነገር ግን እንደዚያው ኾነበት! መግባት ጨርሶ አቃታው! በዚህ ጊዜ፡ በድንጋጤ፥ በመሸበርና በፍርሃት መንፈስ፡ ዘወር ብሎ፡ እውጭ፡ በኃዘን ቆመው፡ ይመለከቱት ወደነበሩት ቄሰ ገበዝ መጥቶ፡ ሽጒጡን በዛቻ እያወዛወዘና ወደመቅደሱ እያመለከተ፡ "አንተ! ምንድር ነው እዚያ ውስጥ ያስቀመጥከው? እንደዚያ እየተፋጀ የሚገፈትረው? ንገረኝ! ንገረኝ ነው የምልህ፡ ይህን ጥይት ሳላዳፍንብህ?" ብሎ፡ ከቀድሞው በባሰ ኹኔታ አባረቀባቸው።

እርሳቸው ግን: በዚያው: በቀደመው የረጋና የትሕትና አቋማቸው እንደጸኑ ኾነው: "አልሰማ አልኸኝ እንጂ: ቅድም እኮ ነግሬህ ነበር! እኛ ኢትዮጵያውያን እኮ: እንደእናንተ አይደለንም! እኛ: 'በእውነትና በመንፈስ' የምናመልከው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር፥ በቅዱሳን መላእክቱ ታጅቦ: በመንፈስ ቅዱስ: በዚያ ቤተ መቅደስ ውስጥ አለ! 'በዚህ ሰዓትና በዚህ ኹኔታ: ስንኳን አንተ: እኔም ብኾን: ልገባ አይቻለኝም!' ያልኩህ ስለዚህ ነው፤" አሉት::

ያም የፋሺስት ጦር አዛዥ: በመለኮታዊው ኃይል የደረሰበት አስደንጋጭ በትርና ይህ: ከቄስ ገበዙ የሰማው ሃይማኖታዊ ምላሽ፥ በዚያም ላይ: የተናጋሪው: ያልተቃወሰ እርጋታና ትሕትና ተጨምሮ: በግፍ የተመላና በዕብሪት የሰከረ መንፈሱን ወደስክነት መልሶት ኖሮ: ያ ኹሉ ድንፋታ ቀርቶ: ሽጉጡን ወደአፎቱ እየከተተ: በለሰለሰ ቃል: "በል! በነገው ቀን: ከጧቱ ልክ በሦስት ሰዓት: አራዳ ካለው ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ድረስ እንድትመጣ! እንዳትቀር!" ብሏቸው: ሙሉ ስሙን ከነማዕርጉ ሰጥቷቸው ተመለሰ::

ቄሰ ገበዝ: እጅግ ማልደው ተነሥተውና ትንሹን ልጃቸውን አስከትለው: ከዚያች ከተቀጠሩባት ሰዓት ቀደም ብለው: እተባለው መሥሪያ ቤት ደረሱ፤ እዚያም: ማንን እንደሚፈልጉ ተጠይቀው ካስታወቁ በኋላ: "ይቆዩ!" ተብለው ሲጠባበቁ: ሰዓታት አለፉ፤ ቀትር ኾኖ: የምሳ ጊዜም ተላልፎባቸው: የሠርኩ ሰዓት ተቃረበ! አባትና ልጅ: "ነገሩ ምን ይኾን?" እያሉ በማመንታትና ከማናቸውም ጉዳት እንደሚያድናቸው ወደሚተማመኑበት አምላካቸው እየጸለዩ ሣሉ: ተጠርተው: ወደዋናው ሹም ጽሕፈት ቤት ገቡ፤ እዚያም: ሹሙ ተቀብሎ: በመገረም: ቄሰ ገበዝ: ስለመጡበት ምክንያት በዝርዝር እንዲያስረዱት ጠየቃቸው:: እርሳቸውም: በትናንትናው ቀን: በቤተ ክርስቲያን የኾነውን ኹሉ ነገሩት፤ ስለዚሁ ጉዳይ: ቀደም ብሎ አግኝቶት የነበረው መረጃና የእርሳቸው ቃል አንድ መኾኑን ሲያረጋግጥ: "የአንተ አምላክ: ኃይለኛ ነው! ያ እንደዚያ ያደረገው የጦር አዛዥ: 'እከሌ' ትናንት: ለዘመቻ ታዝዞ: ማታውኑ: ጦሩን እየመራ: በባቡር ወደድሬዳዋ ሲጓዝ: ሌሊት: አደጋ ደርሶበት ሞቷል! አንተ ግን: ትእዛዙን አክብረህ: በቀጠሮህ እዚህ በመገኘትህ: የሚገባህን ፈጽመሃል:: ወደፊትም: በቤተ ክርስቲያንህ ላይ ምንም ችግር አይደርስምና: አምልኳችሁን: ያለሥጋት ልትፈጽሙ ትችላላችሁ!" ብሎ: በአክብሮትና በፈገግታ ሰላምታ ሰጥቶ አሰናበታቸው::

እኒያ: ሕጋውያን ካህናት: የቈረቈሩዋቸውን አድባራት: ይህን በመሰለ ሰማዕትነትና መሥዋዕትነት: እንዲህ አድርገው ያቆዩዋቸው ሲኾን: ዛሬ: የእነርሱን ክህነታዊ ፈለግ ተከትለው የሚገኙት ልጆቻቸው: በ"ገዳምነት" ምክንያት: ከመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ደብር: ከአገልግሎት እንዲለዩ ሲደረግ: በቅዱስ ቂርቆስ ደብር ላይ ደግሞ: አንድ መነኩስ እንዲሾምበት ተደርጎ: የዚህ መጽሐፋዊ መልእክት አዘጋጅና የቄሰ ገበዙ: የልጅ ልጅ የኾነው ካህን: "እኒያ አባቶቼ የተጋደሉላት: ንጽሕትና ርትዕት የኾነችው የተዋህዶ ሃይማኖት: ቃል ኪዳኗን አትሽርም! አትለወጥም!" በማለቱ ብቻ: ወደተወለደባትና ወዳገለገለባት ቤተ መቅደስ እንዳይገባ: በእጬጌ ጳውሎስና በጳጳሳቶቻቸው ተከለከለ::

በዚህ አንጻር: ከትግራይ ገዳማቸው ወጥተው: በዚሁ ደብር ሲያገለግሉ በቆዩ: በአንድ መነኩስ ሕይወት የኾነውን መመልከት ነው::

እኝህ መነኰሴ፡ ስለታመሙ፡ ከሕክምና፡ ወደደብረ ሊባኖስ ገዳም፡ ለጠበል ተወስደው፡ መረዳት እንደጀመሩ፡ "ይህን፡ የገዳም ዳቤና ንፍሮ፡ ሰውነቴ፡ ሊቀበለው አልቻለም፤ የለመድሁትን፡ ጮማና whisky (ውስኪ) እየተመገብሁ፡ እዚያው አዲስ አበባ ብሞት ይሻለኛልና፡ እባካችሁ ወደዚያ መልሱኝ!" ብለው፡ ፈቃዳቸው ተፈጽሞላቸው፡ ብዙም ሳይቆዩ ዐርፈዋል።

እንግዲህ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የቀኖና ሥርዓታቸውን አክብረውና ጠብቀው መኖር ስላለባቸው፡ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ደብር፡ "ርእሰ አድባራት" ተብሎ፡ በደብርነቱ ሊቀጥል፥ በዚያም ኾነ፡ በሌሎቹ የከተማ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያን፡ ተመድበው የሚገኙት መነኰሳትም ኹሉ፡ ወደየገዳማቸው ሊመለሱ፥ ወይም ወደየሚፈልጉበት ገዳም ሊደለደሉ፥ የሚቆዩ ቢኖሩም እየታየ፡ እንደሥርዓቱ ሊፈጸም ይገባል።

## ኢትዮጵያ፡
## ባዕዳን የሃይማኖት ልኡካንን ስትፋረድ!

የአጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር፡ ባዕዳንን፡ የሃይማኖት ሰባኪዎች (missionaries = ሚሲዮናውያንን) በሚመለከት፡ ሙሉ ሥልጣን ያለው ኾኖ፡ ማናቸውንም ጉዳይ የሚከታተል፡ አንድ የተልእኮ ሕዋስን (Committee) በነጋሪት ጦማረ ሕዝብ (gazette = ጋዜጣ) ደንብ፡ አቋቁሞ እንደነበረ ይታወሳል። የሕዋሱ አባሎች ብዛትና ሥልጣን፡ በዚያ ደንብ ውስጥ በተጠቀሱት፡ አግባብ ባላቸው፡ በመንግሥቱ ምልክናዎች ቁጥርና በከፍተኛ ደረጃ እንዲኾን ሲወሰን፡ ስለአባሎቹ የሃይማኖት ዓይነት ግን፡ የተጠቀሰ፡ አንዳችም ነገር አልነበረም። ስለዚህ፡ በሕዋሱ ውስጥ፡ መሥሪያ ቤቶቻቸውን ወክለው ይገኙ ከነበሩት ተጠሪዎች ባለሥልጣኖች መካከል፡ የልዩ ልዩ ባዕድ ሃይማኖት ተከታዮች፥ ይልቁንም፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ላይ እጅግ የጸና የተቃውሞ አቋም እንዳላቸው በግልጽ ይታወቁ የነበሩት እንኳ ሳይቀሩ፡ አባሎች ኾነው ይመደቡ እንደነበረ ይታወቃል። ይህ ሲኾን፡ በጉዳዩ ተጠያቂነትና መብት ያላት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ብቻ፡ ኾን ተብሎና በይፋ፡ ከአባልነቱ እንድትገለል ተደረገ።

የሃይማኖት ልኡካኑ፡ የታቀደ ዓላማቸው፡ ከግቡ ይደርስላቸው ዘንድ፡ የተግባሮቻቸውን አካኼድ፡ የተቃናና የተመቻቸ በማድረግ ረገድ፡ የሚከናወንላቸውን ዝግጅት እንኳ፡ ለዚህ ሴራ፡ ሰለባ ኾና የቀረበችው፡ ጭቁኒቱና ብሔራዊቷ ቤተ ክርስቲያን፡ እንድታውቀው እንኳ አይሞከርም ነበር። ይኸውም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ፡ የሚኖርበትን አካባቢ ሳይቀር፡ "ይህኛው፡ ዝግ ወረዳ ነው"፥ "ይህ ግልጽ ወረዳ ነው" ብሎ እስከመወሰን በሚደርሰው፡ ለዚያ ሕዋስ፡ በአዋጅ ተሰጥቶት በነበረው ልቅ ሥልጣን ውስጥ፡ ቤተ ክህነት እንድትካፈል አለመደረጉ ነው። ይህ የተቃወሰ አድላዊ ደንብ እንዲሻሻል፡ ጥናት ይደረግ ዘንድ፡ ቤተ ክህነት በየጊዜው፡ ለቤተ ምልክናው ያቀረበችው ጥያቄ፡ ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል። በዚህ ኹሉ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ የባሕርይ ገንዘቧ በመኾኑ፡ ሊገሠሥ የማይቻለውን መለኮታዊ መብቷን የሚነካ፡ ታላቅ የድፍረት በደል ተፈጽሞባታል።

ከላይ በተጠቀሰው፡ የነጋሪት ጦማረ ሕዝብ፡ በወጣው ደንብ መሠረት፡ በኹሉም ዓይነት የሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ ለሚገኙና "ሰባኪዎች ነን" ለሚሉ ባዕዳን ልኡካን፡ ያለተገቢ ምርጫና ማጣራት፡ ወደኢትዮጵያ እንዲመጡ ተጋብዘዋል፤ እንዲገቡም ተፈቅዶላቸዋል።

ከገቡም በኋላ፡ ግልጽ ያደረጉትንና በምሥጢር የያዙትን ሃይማኖቶቻቸውን፡ በአገሪቱ ውስጥ፡ እንዲያሠራጩና ሥውር ተግባራቸውን እንዲያካኺዱ፡ ሙሉ ነጻነትና ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል::

እኒህ ልኡካን፡ የስብከትና የማስተማር ሥራቸውን አስፋፍተው ማካኼድ ያለባቸው፡ "ግልጽ ወረዳ" ተብሎና ተለይቶ በተሰጣቸው ክልል ውስጥ ብቻ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ በይበልጥ፡ ያለ፥ የሌላቸውን ኃይል፡ በሙሉ አጠቃልለውና ከሌላው መልሰው፡ የሚረባረቡት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ በሚኖርባቸው፡ "ዝግ ወረዳዎች" በተባሉት ክልሎች ውስጥ ነበር:: ይህም አሠራር ይካኼድ የነበረው፡ በዚያ፡ በተጠቀሰው ደንብ መሠረት፡ ታስቦበትና ታቅዶ፥ መንግሥትም እያወቀ፡ እንዳላወቀ በመምሰል እንደነበረ፡ እነሆ፡ ውጤቱ ገሃድ አድርጎታል:: "ግልጽ ወረዳ" የሚባለው፡ ባዕዳን የሃይማኖት ሰባኪዎች፡ በውስጡ ገብተው፡ የመስበክና የማስተማር ተግባራቸውን ማካኼድ የሚችሉበት ሲኾን፥ "ዝግ ወረዳ" የሚባለው ደግሞ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ የሚኖርባቸው በመኾኑ፡ ያንን ተግባራቸውን ማካኼድ የማይችሉበት ነበር::

በዚህም፡ ኢትዮጵያን ለመጉዳት ሲባል፡ ኾን ተብሎ ይካኼድ የነበረው፡ የዚህ የሃይማኖት ዘመቻ፡ ብቸኛ ዓላማው፡ በተግባር ተገለጠ! የወኪሎቹም ተልእኮ ከፍጻሜ ደርሶ ታየ! "የተተኰሰው ጥይት፡ ዒላማውን መታ!" እንደማለት ኾነ:: ይኸውም፡ እነዚያ ልኡካን፡ "ግልጽ" ወደተባለው ወረዳ ኼደው፡ ደኑን መንጥረውና አቅንተው ከመሥራት ይልቅ፡ ያለብዙ ድካም፥ በአጭር ጊዜ፡ የተትረፈረፈ ምርት ወደሚሰበስቡበት፥ በክርስትናው ሃይማኖት፡ የለሰለሰ እርሻ ወደኾነላቸው፥ ለጥፋት ተልእኳቸውም፡ ዋና ዒላማቸው አድርገውት ወደመጡበት፡ በተለይ፡ "ዝግ" ወደተባለው ወረዳ ውስጥ በቀላሉ ገብተው፡ በሚከፋፍለው የስብከት ትምህርታቸውና ሃይማኖትን በሚያስለውጥ ምግባራቸው፡ ቤተ ሕዝቡ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ያለው የሃይማኖት ጽናት እንዲላላና የአንድነቱ ኃይል እንዲዳከም ማድረግ ረገድ ነው::

ለዚህም፡ አያሌ ማስረጃዎችን ማቅረብ ሲቻል፡ ከእነዚህ፥ በተለይም ከቅርቦቹ ይልቅ፡ ቀደም ካሉት፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣን ዓመታት ከተፈጸሙት መካከል፡ አንዱ፡ ለምሳሌ ያህል፡ እዚህ ላይ፡ ባጭር ተጠቅሷል::

## ኢትዮጵያ፡ ስለእውነተኛ ልጇ፡ ስለአለቃ ዘካርያስ ስትፋረድ!

### የሺህ ዘኾርያ ማንነት::

በአንድ ወገን፡ ፊት በግራኝ አሕመድ፥ ኋላም፡ በደርቡሾች ወረራ ምክንያት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ፡ እስልምናን፡ በግድ እንዲቀበል በተደረገበት ጊዜ፡ በዚያ ምክንያት፡ ወደእስልምና ከገቡት አያት ቅድመ አያቶቻቸው ከተገኙት፡ "ጅብሪል" ከተባሉት አባታቸው፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የክርስቲያን ቄስ ልጅ ከነበሩትና ኋላ "በፍታ" ከተባሉት እናታቸው፡ በላስታ አውራጃ፥ ቡግና ወረዳ፥ ጣርና በተባለው ቀበሌ[፲፭፻] የተወለዱ፡ አንድ ብርቅ የሃይማኖት ሰው ነበሩ::

በእስልምና ስማቸው: ሼሀ ዘኸርያ ይባላሉ:: የተወለዱት: በ፲፰፻፶፫ ዓመተ ምሕረት ሲኾን: በጣም የታወቁት: በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን ነበር:: አስደናቂ ዜና ሕይወታቸውና ዝክረ ነገራቸው: በአጭር ሓተታ: እንደሚከተለው ቀርቧል::

ዘኸርያ: በእስልምና እምነት መወለዳቸውና ማደጋቸው ብቻ ሳይኾን: ይህንኑ ሃይማኖት በሚገባ ተምረው: "ሼሀ" ለሚለው ማዕርግ በቅተውበታል:: ይኹን እንጂ: የጥንተ ክርስቲያንነታቸው ሥር መሠረት: አልለቅ ስላላቸው: በዚያ የእስልምና ሃይማኖታቸው: መንፈሳቸው ረክቶና የሕሊና ዕረፍትን አግኝተው: በሰላም ሊኖሩ ስላልቻሉ: እውነተኛውን ሃይማኖትና አምልኮ ይገልጥላቸው ዘንድ: በእስልምናም፥ በክርስትናም ወደሚመለከው: ወደአንዱ ፈጣሪ: ወደእግዚአብሔር ለማመልከት: ሱባዔ ገቡ! እግዚአብሔርም: በእውነት የሚለምኑትን የሚሰማ: እውነተኛ አምላክ በመኾኑ: የአንድነቱንና የሦስትነቱን ምሥጢር፥ በመንፈስ ቅዱስ ግብር: ከድንግል ማርያም የተወለደው: የእግዚአብሔር ቃል: ኢየሱስ ክርስቶስ: እርሱ ብቻ የዓለም መድኅን መኾኑንም የሚያሳውቀውን ምሥጢረ ሥጋዌዉን ገልጠላቸው: በዚያው በመንፈስ ቅዱስ ተመልተው: ከሱባዔያቸው ወጡ!

## የሼሀ ዘኸርያ ተልእኮ::

ከዚህ በኋላ: የእስልምና ሃይማኖታቸውን ሳይለውጡ: አላገባብ በልማድ የተጨመሩትን ብቻ አጋልጠው በማውጣት: በዚያው በቁርዓኑ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን: እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማሩ: አያሌ እስላማውያን ወገኖቻቸውን: ወደጥንቱ: የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸው መለሱ! የተመለሱትም: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየተጠመቁ: ክርስቲያን፥ ዐማራ፥ ኢትዮጵያውያን ኾኑ!

በዚህ የአምላክ ድርጊት የተበሳጩ: በዋግ፥ በላስታ፥ በበጌምድር፥ በትግሬና በወሎ ያሉ የእስልምና ተጠሪዎች: ከፉኛ ቢቃወሟቸውና በየአካባቢያቸው ለሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች: አቤቱታ እያሰሙ፥ እየከሰሱም: በየተራ፥ በየግዛቱ፥ በይግባኝም: ለዳኝነት ቢያስቀርቧቸው: ነገሩ: አንድ ጊዜ: ከእግዚአብሔር የመጣ በመኾኑ: በመንፈስ ቅዱስ የተመሉትን: እኝህን ሰው: ማንም: በምንም መንገድ ሊቋቋማቸው የማይቻለው ኾነ!

## የሼሀ ዘኸርያ ገድል::

በመጨረሻ: ከሳሾቻቸው: በጊዜው: የአገሪቱ ጠቅላይ ዳኛ ወደነበሩት: ወደዳግማዊ አጼ ምኒልክ የይግባኝ አቤቱታቸውን ስላቀረቡ: ራሳቸው: አጼው: በዙፋናቸው በተቀመጡበት: በአዲስ አበባ ታላቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ: ችሎት ተደርጎ: በዚያ ሸንጎ ላይ: በኢትዮጵያ የሚገኙ: "የእስልምና ሃይማኖት ሊቃቻችን ናቸው" ያሏቸውን ይዘው: ከሳሾቻቸው ላሰሙባቸው ክስ: ሼሀ ዘኸርያ በሰጡት መልስ: እንደተለመደው: ከሳሾቻቸውን ረቷቸው!

ከሳሾቻቸው ግን፡ "በእኛ የእውቀት ማነስ ምክንያት፡ ሃይማኖትን ያህል ነገር፡ እንዴት 'ተረትተንበታል' እንባለን! ከእኛ የበለጠ፡ የሃይማኖቱ እውቀት ያላቸው ስላሉ፡ እነርሱንና በውጭ ካሉትም አስመጥተን ክርክራችንን ለመቀጠል ይፈቀድልን!" የሚል አቤቱታ አቀረቡ። ችሎቱ፡ በመጨረሻው የይግባኝ ደረጃ፡ በቀረበለት ጉዳይ ላይ፡ የመደምደሚያውን የፍርድ ውሳኔ ከመስጠት በቀር፡ አቤቱታቸውን ተቀብሎ፡ ጉዳዩን፡ ለሌላ ቀጠሮ የማስተላለፉ አሠራር፡ ከተለመደው ሥነ ሥርዓት ውጪ መኾኑ ቢታወቅም፡ በከሱ ሃይማኖትነት ምክንያት፡ ሸንጎው አስተያየት አድርጎ፥ ተከሳሹም፡ ቢቀጠር የሚስማሙ መኾናቸውን ስለገለጹ፡ በአጼው ፈቃድ፡ ከሳሾቹ፡ የጠየቁት የቀጠሮ ቀን ተሰጣቸው።

በቀጠሮው መሠረት፡ ከሳሾቹ፡ ዋቢዎቻቸው የኾኑትን፡ ሊቆቻቸውን ይዘው ቢቀርቡም፡ በዚህም፡ አጼው በተቀመጡበት፡ በኹለተኛው የዙፋን ችሎት ላይ፡ ሼህ ዘኸርያ፡ እንደገና ረቱ! ከሳሾቻቸው ግን፡ መረታታቸውን አሁንም ለመቀበል ፈቃደኞች ባለመኾናቸው፡ በችሎቱ ላይ የተገኙት፡ የከሳሾቹ ሊቆች፡ "በመላው ዓለም ከሚገኙት መካከል፡ ከእኛ የበለጠ እውቀት ያላቸውን፡ የሃይማኖት ምሁራን ይዘን ለመቅረብ እንድንችል፡ የአንድ ጊዜ ዕድል ይፈቀድልን!" ብለው አመለከቱ። ምንም እንኳ፡ በከሳሽነትና በተከሳሽነት ቆመው የሚሟገቱት፡ ኹለቱም ወገኖች፡ የዚያው የአንዱ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መኾናቸው ቢታወቅም፡ ከሳሾቹ፡ "እኛ እስላሞች በመኾናችንና የምንከራከረውም፡ ለእስልምና ሃይማኖታችን በመኾኑ፥ ተከሳሹ ግን፡ 'እውነተኛውና ትክክለኛው ሃይማኖት፡ እስልምና ሳይኾን፡ ክርስትና ነው' በማለት ስለሚከራከረን፡ እስካሁን የረታን፡ አጼውና ዳኞቹ፡ የክርስቲያን መንግሥት ባለሥልጣኖች ስለኾኑ ነው!" በሚል ምክንያት፡ "ፍርድ ጎደለብን! ተበደልን!" እንዳይሉ በማሰብ ይመስላል፡ እንዳለፈው ጊዜ፡ አሁንም አስተያየት ተደርጎላቸው፡ የመጨረሻው ቀጠሮ ለሦስተኛ ጊዜ ተሰጣቸው።

በዚህም፡ አጼ ምኒልክ በተቀመጡበት ችሎት ላይ፡ በከሳሾቹ አማካይነት፡ ከግብፅ፥ ከዓረብ፥ ከፋርስና ከሕንድ ሳይቀር፡ ተጠርተው የመጡት፡ እኒያ የእስልምና ሊቃውንት በተገኙበት፡ ተከሳሹ፡ ሼህ ዘኸርያ፡ አሁንም፡ ለሦስተኛ ጊዜ ረቱ! ያ፡ ለዚህ አገልግሎት መርጦ የጠራቸው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ለእነርሱና ለአሕዛብም ምስክር እንዲኾን፡ ስለእኔ ወደገዢዎች፥ ወደነገሥታትም ትወሰዳላችሁ! አሳልፈውም ሲሰጧችሁ፡ የምትናገሩት፡ በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና፡ እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ! በእናንተ የሚናገር፡ የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፡ የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁምና!"* ሲል የተናገረው ቃሉ፡[፻፷፮] በዚያን ጊዜ መፈጸሙ ተረጋገጠ።

## የሼህ ዘኸርያ የድል አክሊል።

እንዲህ ኾኖ፡ ተከሳሹ፡ ሼህ ዘኸርያ፡ በቀረበባቸው ክስ ኹሉ ስለረቱ፡ ትምህርታቸውን፡ ማንም ሳይቃወማቸው፡ በመላ ኢትዮጵያ፡ በነጻ ለማስተማር የተፈቀደላቸው መኾኑን በመግለጽ፡ አጼ ምኒልክ፡ የችሎቱን ውሳኔ፡ ለጉባዔው በይፋ አስታወቁ።

በዚህ ጊዜ፡ ከሳሾቹ እስላሞች፡ “ለረዥም ዘመን የቆየውን ልማዳችንን እንዴት እንተዋለን?” ቢሉ፡ “ልማድ ሃይማኖት አይኾንም!” የሚል ምላሽ ሰጥተዋቸው፡ ጉዳዩ በዚሁ ተዘጋ:: ውሳኔውንም የሚያስታውቅ፡ የአዋጅ ቃል፡ በታላቁ ማኅተም ታትሞ፡ ለሼህ ዘኸርያ ተሰጣቸው::


ሼህ ዘኸርያ፡ ይህን የአዋጅ ቃል ይዘው፡ ከወገኖቻቸው መካከል፡ ብዙዎችን፡ ከእስልምና ወደነባሩ ኢትዮጵያዊ ሃይማኖታቸው፡ ወደክርስትና ከመለሱ በኋላ፡ በመጨረሻ ራሳቸውም፡ በደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን፡ “ንዋየ ክርስቶስ” የሚለውን፡ ስመ ክርስትና ተቀብለው፡ ተጠመቁ! የተጠመቁትም፡ በመንፈስ ቅዱስ ታዝዞ፡ ከአኵስም በመጣ፡ ሐናንያ በተባለ፡ ባሕታዊ ካህን እጅ ነበር:: የእግዚአብሔር ልጅነታቸውንና እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታቸውንም፡ ቅብዓ ሜሮኑን በመቀባትና ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል፡ ለመጨረሻ ጊዜ አጸኑት! ዐተሙት! ከዚያች፡ ሃይማኖታዊት የንግሥ ቀናቸው ጀምረው፡ “አለቃ ዘካርያስ” በሚለው መጠሪያ ስማቸው፡ የታወቁ ኢትዮጵያዊ ኾነው ኖሩ::

አጼ ምኒልክ፡ ለሼህ ዘኸርያ፡ በዚሁ በበጌምድር ክፍለ ሀገር÷ በጋይንት አውራጃ÷ በነፋስ መውጫ ወረዳ÷ በታች ነገላ ቀበሌ በሰጧቸው ርስት ጕልታቸው ላይ፡ በሐዋርያት (አቦ) ስም፡ አንድ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው፡ የሐዋርያነት አገልግሎታቸውን፡ እየተዘዋወሩ ሲቀጥሉ ከቆዩ በኋላ፡ በዚሁ ርስተ ጕልታቸው ላይ እንዳሉ፡ በጥቂት ቀናት ሕመም፡ ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ተለይተው፡ አስከሬናቸው፡ በዚያው በአጸቋሙት፡ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተዘጋጀው መካነ መቃብራቸው ዐርፏል::

እርሳቸው ካረፉ በኋላም፡ “አለቃ እከሌ” እየተባሉ፡ ያንኑ፡ የሐዋርያነት አገልግሎታቸውን የቀጠሉት ደቀ መዛሙርቶቻቸው ባመለከቱት መሠረት፡ አመልካቾቹ፡ በዚያን ጊዜ፡ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በነበሩት፡ በንጉሥ ተፈሪ (ኋላ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ) አማካይነት፡ ከንግሥት ዘውዲቱ ዘንድ ቀርበው፡ አባታቸው አጼ ምኒልክ፡ ለአለቃ ዘካርያስ ሰጥተዋቸው የነበረውን የአዋጅ ቃል በማጽደቅ፡ ታላቁ ማኅተም ያረፈበትን ደብዳቤያቸውን ሊያገኙ ችለዋል::

## ኢትዮጵያ፡
## አድቬንቲስቶችን
## ስትፋረድ!

ቀድሞ፡ “ሼህ ዘኸርያ” ይባሉ የነበሩት÷ ኋላ ግን፡ “አለቃ ዘካርያስ” ሲባሉ የኖሩት፡ እኒያ ታላቅ፡ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ፡ ከእግዚአብሔር በተቀበሉት፡ በዚያ፡ ተልእኳቸው ምክንያት፡ በአንድ ወገን፡ በውስጥ፡ ከእስላሞች በኩል፡ በእርሳቸውና ኋላም በተከታዮቻቸው ላይ፡ ያልተቋረጠ ተቃውሞ ሲደርስባቸው፡ በሌላ ወገን ደግሞ፡ ከውጭ፡ “ክርስቲያን ነን” በሚሉ ባዕዳን በኩል፡ ባልታሰበ አግጣጫ፡ ጠላት ተነሣባቸው!



የደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን።

የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ግድም፡ በኢትዮጵያ ተወልደው የኖሩትና ሠርተው ያረፉት፡ ኢትዮጵያዊው የቀድሞው ሸኽ ዘኸርያ፥ የኋለኛው አለቃ ዘካርያስ፡ ወስመ ጥምቀቱ ንዋየ ክርስቶስ፡ ገና በእስልምና ሃይማኖት ሣሉ፡ እውነተኛውን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት በማስተማራቸውና በመስበካቸው፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ያሉ እስላሞች፡ በተቃውሞ ተነሣሥተውባቸው፡ እነዚሁ ተቃዋሚዎቻቸው፡ በወከሏቸው ሊቃውንቶቻቸው መሪነትና ዋቢነት፡ እስከአጼው ችሎት ድረስ፡ በባለሥልጣኖች ላይ፡ በየደረጃው እየተከሰሱና መልስ እንዲሰጡ እየተጠሩ በቀረቡባቸው አያሌ ጊዜያት፡ ከሳሾቻቸውን፡ በራሳቸው የቁርዓን ቃል፡ በተደጋጋሚ መርታታቸው፥ በዚህም ረገድ፡ በመጨረሻ የተበየነውን፡ የፍርድ ውሳኔ፡ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ፡ በታላቁ ማኅተም አጽድቀው፡ ተከሳሹ፡ የሐዋርያነት ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ የፈቀዱበት የዓዋጅ ቃልና ጽሑፍ፥ ልጃቸው ንግሥት ዘውዲቱም፡ ያንኑ የአባታቸውን ግብር በማጽናት፡ ሌላ የአዋጅ ቃልና ጽሑፍ የሰጧቸው መኾኑ፡ በዚህ መጽሐፍ ገጾች ፪፻፺፰-፫፻፩ ውስጥ ታትቷል። የእነዚያ ኹለት የዓዋጅ ቃላትና ጽሑፎች ብርሃናዊ ቅጂ፡ ይኸው ቀርቧል። በጽሑፎቹ ውስጥ የማይነበቡ፡ አንዳንድ ቃላት ቢኖሩ፡ ከወረቀቶቹ የዕድሜ ርዝመት የተነሣ መኾኑ እንዲታወቅ ይኹን!

ሞዓ አንበሳ፡ዘእምነገ
ደ፡ይሁዳ፡ሥዩም ት፡እ
ግዚአብሔር፡ንግሥት፡ነ
ገሥታት፡ዘውዲቱ፡ወለ
ቴ፡ለዳግማዊ፡ምኒልክ፡
ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢት
ዮጵያ፡ሐ፡ዘካርያስ፡
፲፫ኛ መት፡ጠሎ፡የተገሬ
ኝ፡የቀጉኝ፡የመቴትኝ፡
የጐንደርኝ፡የበጌምድ
ርን፡ኸስላም፡ሁሉ፡ያስቀ
ምር፡ነበርቀት ምሕርቱ
ም፡የቁራኑ፡ቃል፡ጠብ
ቂቀ ምነው፡በአዋልድ፡ቃ
ል፡እየሄዱ ቻሁ፡ትስታላ
ቸ ሁ ያልታዘዘውን፡ተሰ
ራላችሁ፡አያለ፡ነበረላች
ሁም ቸ፡ግን፡ዶክ ዝን፡አ
ጓለቅም፡ብለው፡የተገሬዎች፡
እዩ ሺ፡ገብሬ፡ሥላሴ፡ሳ
ይ፡ከሰሱት፡፡ሃይማኖታቸ
ኛ ን፡ለውጠዋል፡ሥራታ
ቸኝ ን፡እፍርስዋል፡ብለ
ውታእሱም፡የገዢ፡ቁራኖ
ቸውን፡ምስክር፡እያደረ
ገ፡እረታቸው፡፡የሳቴና፡
የካዱ፡እነሱ፡እንደሆኑ፡
ገለጠባቸውና፡የዋጋና፡
የላስታ፡እስላሞች፡በዚሁ፡
ታል፡እዋጋሹም፡ኋንጉል፡
ላይ፡ከሰሱት፡እርሱም፡
እንደሌቱ ኞች፡እረታቸ
ውየጐንደርና፡የበጌም
ድርም፡እራስ፡ጉግሳ፡ላይ፡
ከሰሱት፡ዘካርያስም፡እን
ደሬትኞች፡እረታቸውና
ቁራናቸውን፡ለቀው፡በል
ብ፡ወለድ፡ለሥጋቸው፡የ
ሚመቻቸውን፡እንደሰ
ሩ፡እስታወቀባቸው፡፡ከ
ዚህ፡በኋላ፡እነዚያ፡የረታ
ቸው፡ሁሉ፡ይግባኝ፡በኛን

ሠ፣ነገሥተ፡ፈተ፡ብለው [illegible]
ከሰሱ፡ተ፡ስለዚ [illegible]
ዘው፡ወደ፡መጠ፡በመ [illegible]
ሙያ፡ጊዜ፡በአደባባ፡[illegible]
ያለውን፡ዓረብና፡ቱርክ፡[illegible]
ሂኘዴና፡ጉራው፡ጊ፡አሳበ
ፉፉኤየዴነት፤ሁነው፡ፍር
ዱ፡ደሰሙን፡ብለው፡ለመ
ኑን፡እኛም፡በቀጠሮ፡አ
ጋጠምናቸው፡አቡኛና፡
ሊቃውንትን፡ወምበሮች
ንና፡ሽማግሌዎችን፡መ
ሰፍንቶንና፡መኳንንትን፡
ሰብስበን፡ከፋሽችም፡በራ
ታቸ፡ንጉሡቸው፡ክኅ
ዱ፡አሉም፡መለሰ፡የተካከ
ዴ፡በትን፡የቁራን፡ቃል፡ሁ
ለቱ፡በመረጡቸው፡መሾ
ሐፍ፡እዋቲዎች፡እደሰነበ
ብን፡እደስተረጉምን፡ለየነ
ውሉ፡እሩቶቸውን፡እደሰነበ
ብን፡እደስተረጉምናቸ
ው፡በገዛ፡ቃላቸውና፡በቁ
ራናቸው፡ምስክር፡በሶስት፡
ጉባዔ፡አረታቸው፡ከዚሁ፡

በኋላ፡ጀግኖች፡የወረዛመኑ፡
ተካለሂሬ፡ቃሉ፡ወረገዩ፡
የሰገተ፡ቤተ፡ወሉ፡እስኅም
ች፡ሁሉ፡ተሰብስበው፡መፕ
ተው፡ደኝነት፡ደስውን፡ዋት፡
ርቶ፡ያውሙ፡ሌኛ፡እኘዴት፡
ሃይማኖትን፡ያሁል፡ነገር፡
ዓኀረቃና፡ሳኘከራከር፡እኛ
ተዋለኝ፡ካሁን፡ተጅሞ፡የ
ተረቱ፡ያሏተማሩና፡ኢሉም፡
ያገወቱ፡ናቸው፡አሁኑ፡ግ
ን፡አውቀት፡ያገቸውኛ፡
ፉርቃን፡የሚተረጉሙትን፡
እምዋቶችን፡ብለው፡ቢለ
ምኑ፡ንጉሡ፡ጃኒቶችው፡ሁሉ፡
ሊቃውንትንና፡ወምበሮች
ን፡መኳንንትና፡መሳፍን
ትን፡ሰብስበን፡ዘካርያስን፡
አቅርበን፡አጋጠምናቸው፡
ሁለት፡ቀን፡ጉባዔ፡እድርገን፡
ዘካርያስም፡እኘደፈተኞች፡
አረታቸው፡እኛም፡እኘ
ዴህ፡እኘዴት፡ተሆኑ፡በቁ
ራናቸው፡ቃል፡ታገደሉች
ሁ፡የለም፡አሉተኛሬም፡

ብላችሁ፡ ነበረ፡ ተረታች
ሁበት፡ አልናቸው፡ እነሱ
ም፡ እንዲት፡ ፲፰፻፺፬ ዓመ
ት፡ የምርጫውን፡ ልማዳች
ን፡ ይቅር፡ አሉ፡ እኛም፡ ል
ማድ፡ ሕግ፡ አይሆንም፡ ስ
ንል፡ ይኼንን፡ አዋጅና፡ ፈ
ቃድ፡ ለሺህ፡ ዘካርያስና፡
እሱን፡ ለመሰሎት፡ ሁሉ፡
ሰጠን፡ ያዋጁም፡ ቃል፡ ይ
ኸ፡ ነው፡ ሺህ፡ ዘካርያስ፡
ከእስላሞች፡ ጋራ፡ በተክ
ሰሰበት፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በቁ
ራን፡ እረቱል፡ ስለዚህ፡ ካ
ሁን፡ ቀድሞ፡ በቁራኑ፡ ቃል፡
የሚያስረውን፡ እስላም፡
ሁሉ፡ በወደደው፡ አገር፡
እየሄዱ፡ እንዲ እስተምር፡
ፈቀድንለታል፡ አሁንም፡
ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ ሺህ፡ ዘካር
ያስን፡ ወይም፡ ደረሶችን፡
በሱም፡ ትምሕርት፡ የረገ
ትን፡ ሰዎች፡ ማንም፡ በሃይ
ማኖት፡ የተነሳ፡ አውካለ
ሁ፡ ቢል፡ ሁለተኛ፡ አይከሰ

ሱ፡ ሺህ፡ ዘካርያስ፡ በተከ
ሰበት፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ፈጽሞ፡
እረቷልና፡ የዚህ፡ የአዋጅ፡
ቃል፡ ቀጂ፡ በሺህ፡ ዘካርያስ
ና፡ በደረሶቹ፡ እጅ፡ በቤት፡
መንግሥትም፡ ይቀመጣል፡
ለዘለዓለምም፡ ምስክር፡
ይሆን፡ ዘንድ፡ እኛም፡ ይህ
ን፡ አዋጅ፡ ማስነገራችን፡
እስላም፡ ለስላም፡ ሁለተኛ፡
እንደይጣላ፡ ብለን፡ ነው፡
ግንቦት፡ ፳ ቀን፡ ፲፰፻፹፱ ዓ
መት፡ ምሕረት፡ አዲሳበባ፡
ከተማ፡ ተጻፈ
የሚሌ፡ የጃንሆይ፡ ያዬ፡
ምኒልክን፡ ማኅተም፡
ያለታ፡ ንዋየ፡ ክርስቶስ፡
ተማሮች፡ እምጥተው፡ የ
ጃንሆይ፡ ማኅተም፡ እን
ደይቀደድብን፡ ጎልባጩ
ን፡ ይስጡን፡ ብለው፡ ቢያ
ሳዩኝ፡ ጎልባጩን፡ በኔ፡ ማኅ
ተም፡ አተሚ፡ ሰጥቻቸዋለሁ፡
ጥር፡ ፳፱ ቀን፡ ፲፱፻፲፭ ዓመት፡
ምሕረት፡ አዲሳበባ፡ ከተማ፡ ተጻፈ





ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡
ሥዩመ እግዚአብሔር፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ። ይ–
ጆሠ፡ ዘካርድስ፡ ፲፫ ዓመት፡ ሙሉ፡ ለትግሬን፡ የዋግን፡ የወ
ቆትን፡ የጎንደርን፡ የቤገምድርን፡ እስላም ሁሉ ያስተ
ምር፡ ነበር። ትምህርቱም፡ የቁርአን ቃል፡ ጠብቆ፡ ምሩ፡
በእዋልድ ቃል፡ እየጻፈው፡ ተሰሚላችሁ፡ ያለ ታዘዉግ

ተሰራላችሁ፡ እያለ፡ ነበረ። ለእስላሞች ግን፡ ይህንን እንሰቀሳ ዛለው፡
የተጋሬዎች፡ አጼ ጀት፡ ገብረ፡ ሥላሴ፡ ላይ፡ ከሰሱት፡ ሃይማኖታቸውን፡ ለወጠ ሃል፡ ሠራታች
ንን፡ አፍርሶሃል፡ ብለው። እርሱም፡ ለገዛ፡ ዘራዩቸው፡ ን
ምስክር፡ እያደረገ፡ እረታቸው፡ የትቱና፡ የካዱ፡ እነሱ፡ እን
ደሆኑ፡ ገለጠባቸው።
ዓዋግና ያላስታ ፡ እስላሞች፡ በዚሁ ቃል፡ ከዋግሹም ጓንጉል፡ ላይ ከ
ሰሱት፡ እርሱም፡ እንደ፡ ሬተኞቹ እረታቸው።
የጎንደርና የቤገምድርም፡ ከራስ ጉግሣ፡ ላይ፡ እንደ ሠተኞቹ ከሰሱት
። ዘካርያስም፡ እረታቸው፡ ቁራያቸውን ገለቀው፡ በልብ፡ ወለድ ለሠጋቸው፡ የ
ሚለዉቸውን፡ አገዱ ስሩ፡ እስታወቀባቸው።
ከዚህ፡ በኋላ፡ እነዚያ፡ ለረታቸው፡ ሁሉ፡ ይግባኝ፡ በንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ፊት
ብለው፡ ከሰሱት፡ ስለዚህ፡ ተያዘው፡ ወደኛ፡ መጡ። በመጠየቂያ፡
በአዱስ፡ አበባ፡ ደለውን፡ አረብና ቀርኝ፡ ሕንዶች፡ ግራውን፡ አሳበሩ። እንዳ

ሁኔው፣ ፍርድ፣ ይሰጣኛ፣ ከለው፣ ለመኑን፣ እኛም፣ በቀጠሮ እንጠምዎቸ
ው፣ አበንዩ፣ ሊቃውንቶም፣ ወያሮችንና፣ ሽማግሌዎችን፣ መሳፍንትንም፣ መ
ኳንንትን ሰብስበኝ።
ዘሰጡቹም በሬታችን፣ ነገሬቸውን፣ አስገው፣ እርሱም፣ መልስ፣ ወጥትንክኑ
ልትንም፣ የቁሬን፣ ቃል፣ ሁለቱ፣ ባለንብረቶች በመፈጫቸው፣ መጽሐፍ፣ አዋቂ፤
እያለነበብኝ፣ እያለተረጉመኝ፣ አየነው፣ አራቶቻውን፣ እያለነበብን፣ እያለ

ሬጉምናቸው፣ ለገዢ፣ ቃላቸውና፣ ለቁ ሁናቸው፣ ምስክር ባለሰትጉባዔ፣ አረሃ
ቸው፤ ከዚህ፣ በኋላ፣ ደገሞ፣ የሠረዛ መሁ፣ ተከለዩሌ፣ ሃሎ፣ ወረቀ፣ የለባታ
ት፣ ወሎ፣ እስላሞቹ፣ ሁሉ፣ ተሰበሰ ው፣ መኖተው፣ ዱኝነቱ፣ ይሰጡኝና
ትክርትዐ፣ ያውጡልኝ፣ እንዲሁ፣ ሃይማኖቱን፣ ይህል፣ ነገር፣ ሳንሊትዩ፣
ሳንክራከር፣ እንተቀለን፣ ካሁን ቀደም፣ የተረቱት፣ ያልተመለሱትም፣ እሌ
ም፣ የማያውቁ፣ ባቸው፣ እሁንግን፣ እውቀት፣ ያላቸውንየ፣ ፋይዳን፣
የተረገሙትን፣ ለምትቀተዋል፣ ብለው፣ ቢለምኑን፣ እንዲሁ፣ ሠተኛው፣ ሁሉ
ሊቃውንቱንም፣ ወምበሮችን፣ መኳንንቱንም፣ መሳፍንቱን፣ ሰብስበን፣
ዘካርያስን፣ አቁርበን፣ እንጠምዎቸው፣ ፪ቀን፣ ተዋዔ አርገን፣ ዘካ
ርያስም፣ እንዲሁ ሠተኞቹ፣ አረታቸው፣ እኛም፣ እንግዲህ፣ እንዲሁ፣
ትሆኑ፣ በቁርዓኖችሁ፣ ቃል፣ ካላዳራችሁ፣ ወልም፣ አልተዳረም፣ ዘላኛ ሁ፣
ነበር፣ ተረቱችሁበት፣ እልዩቱ ው—
እነሱም፣ እንዲሁ፣ ሸሁ፣ ከ፻፵፬ ዘመን፣ የሞረው፣ ለማደኛ ነ፣

ይቅርታን፡ እኔ፡
ኢትዮጵያ፡ ልማድ፡ ሕግ፡ እግዚአብሔር፡ ሰንበል፡ ይህነኑ አቀጅና፡
ፈቃድ፡ ለሸህ፡ ዘካርያስና፡ እርሱ ፒ፡ ለመሰሶ፡ ሁሉ፡
ሰጠን፡ ፃቁጂም፡ ቃል፡ ይህ፡ ነው።
ሸህ፡ ዘዝና ይለ፡ ከሰለጭ ቹ፡ ጋር፡ በተከሰለበት፡ ነገር
ሁሉ ለቀረን እራቱ ለ፡ ለአዚህ፡ ካሁን፡ ቀድሞ፡ ባቀረን፡ ቃል፡ የሚገኙ ሬወ፡ ን፡ እል
ነው፡ ሁሉ፡ በወደደው፡ አገር፡ አየሰ፡ እንደ ይልተምር፡ ሬቀ ይገለታል።
እሁንም፡ ሸዘሬ፡ ደምር፡ ሸህ ዘካርያስን
ወይም፡ ደረሶቹን፡ በርሱም፡ ትምሕርት፡ የሬተትን፡
ሰዎች፡ ማንም፡ ቢሄይማኖት፡ የተነሣ፡ አውከለሁ፡ ቢሉ፡
ሁለተኛ፡ አይከሰሱ። ሸህ፡ ዘካርያስ፡ በተከለለበት፡ ነገ
ር፡ ሁሉ፡ ፈጽሞ፡ እረሱ ቷልና፡ ፱ሺህም፡ ይቀጡ፡ ቅጁ፡
በሸህ፡ ዘካርያስና፡ በደረሶቹ፡ እጅ፡ በቤተ፡ መንግሥትም፡
ይቀመጠሉ፡ ለዘለለም፡ ምልክር፡ ይሆን፡ ዘንድ። እኛ
ም፡ ይህን፡ አቀጅ፡ ማስነገራቹን፡ እለለም፡ ለለለም፡ ሁለተ
ኛ፡ እንዳይጠላ፡ ብለን፡ ነው። ግንቦት፡ ፳፡ ቀን፡ ፲፱፻፳
፱፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ተጻፈ።



የአለቃ ዘካርያስ የበኵር ልጅ፡ እማሆይ ወለተ እግዚአብሔር፡
ከልጃቸው፡ ከእማሆይ እህተ ማርያም (ድንስር) (ከታች ከመኻል)
እና ከወይዘሮ ዘሓቡ ዘካርያስ ልጆች፡
ከልጅ እርቁ አበበ (የበስተግራው)ና ከአባ አግማስ አበበ ጋር።

የኢትዮጵያውያን: ቅዱሱ ኪዳን ሕያው ታሪክ የማይረሳውን ታላቅ በደል የፈጸመባቸው: ያም ጠላት: Seventh Day Adventist (ሰቨንት ዴይ አድቬንቲስት): ማለትም: "የሰባተኛው ቀን አክባሪ" የተባለው: የአሜሪካ የሃይማኖት ድርጅት ሲኾን: የዚህ ድርጅት ልኡካን: (missionaries ሚሲዮናውያን) እና የአገር ውስጥ ተባባሪዎቻቸው: በአለቃ ዘካርያስ ገናና ስምና የተቀደሰ ሙያ ላይ የፈጸሙት ታላቅ በደል: ከዚህ በታች: ባጭር ቃል በሠፈረው: አማናዊ ድርጊታቸው ተገልጾ: ይነበባል።

አጼ ምኒልክ ስለሼህ ዘኸርያ ባስቻሏቸው: ሦስት ችሎቶች ላይ: በዚያን ጊዜ: ገና በልጅነት ዕድሜ የነበሩት ተፈሪ መኰንን (የኋለኛው አጼ ኃይለ ሥላሴ) እና እምሩ ኃይለ ሥላሴ (የኋለኛው ራስ) ተገኝተው እንደነበረ ታውቋል። ስለዚህ: አጼ ኃይለ ሥላሴ: የቀድሞውን ሼህ ዘኸርያና የኋለኛውን አለቃ ዘካርያስን: በአካለ ሥጋ ጭምር: ደህና አድርገው ያውቋቸው ነበረ፤ የዚህም ነገር እርግጠኛነት: ከራሳቸው: ከአጼ ኃይለ ሥላሴ አንደበት ተሰምቷል።

## የአድቬንቲስቶች ስሑት አገባብና መሠሪ ድርጊት።

አጼ ኃይለ ሥላሴ: የአጼነቱን ሥልጣን በያዙበት ዘመን: የአድቬንቲስት ሃይማኖት ልኡካን: በጣልያን ቅኝ አገዛዝ ሥር በነበረችው: በኤርትራ ዋና ከተማ: በአሥመራ ይገኙ ስለነበረ: እነዚሁ ልኡካንና እነርሱን የመሰሉት ኹሉ: ወደኢትዮጵያ ለመግባትና ለመውጣት የሚያስችላቸው: በሩ ተከፍቶላቸው ኖሮ: መጀመሪያ: የአለቃ ዘካርያስ: የተከታዮቻቸው ልጆች ከኾኑት መካከል፥ ቀጥለው: በእነርሱ አማካይነት: ከዋናዎቹ የአለቃ ዘካርያስ ደቀ መዛሙርቶች መካከል: ከአንዳንዶቹ ጋር: በየምክንያቱ: የምሥጢር ግንኙነት ማድረግ ጀመሩ፤ ከዚያ በኋላ: አድቬንቲስቶቹ: ያው: በታወቀውና በተለመደው ዘዴያቸው: ለመቀራረብና ለመወዳጀት: ባካኼዱት ጥረት: በመካከላቸው: የተለየ ፍቅር ተመሠረተ። በዚህን ጊዜ: ባዕዳኑ የሃይማኖት ሠርጎ ገቦች: ስለአለቃ ዘካርያስ ታሪክ: ከእኒህ ደቀ መዛሙርቶቻቸው: ዝርዝር መረጃን አገኙ።

ከዚያ የተነሣ: ያን: ያገኙትን መረጃ በጥልቀት አጥንተው: አለቃ ዘካርያስ: የተናገሩዋቸውን ቃላት ኹሉ: ለእነርሱ በሚጠቅማቸው መልክ እየተረጐሙ በማቅረብ፥ እንዲያውም: "ያ: አለቃ ዘካርያስ ያመኑበትና ያስተማሩት ሃይማኖት: ይህ እኛ: ዛሬ የምንነግራችሁ: የአድቬንቲስት ሃይማኖት ነው" እስከማለት ደረጃ በደረሰ መጠን: ሰብአዊ ቅጥፈትንና የዲያብሎስን ሐሰት የተመላ ስብከታቸውን በማጠናከር: በሃይማኖት: መርታት እንጂ: መረታት: ልማዳቸው ላልኾኑት: ለአለቃ ዘካርያስ: "ደቀ መዛሙርት ናቸው" ሊባሉ የማይገባቸውን: እነዚያን ተከታዮቻቸውን: ሊያሳምኗቸው በቁ።

አዎን! እነዚያ: ጥቂቶቹ የአለቃ ዘካርያስ ደቀ መዛሙርት: ከእስላምነት: ወደዐማራነት: ወይም ወደክርስቲያንነት: ማለትም: ወደኢትዮጵያዊነት የተመለሱ: አዲስ አማኞች እንደመኾናቸው: ምናልባት: "ስለቅዱሳት መጻሕፍት: ገና: በሚበቃ መጠን: ጠልቀው አላወቁም!" ይባል ይኾናል፤ እንዲያ ከኾነም: የአድቬንቲስቶቹን የጥቅስ አቀራረብና የማስረዳት ችሎታ: ለመቋቋምና ለመከራከር የሚያበቃ የእውቀት ደረጃ ሊኖራቸው እንደማይችል: ግልጽ ነው።

ታዲያ፡ ከዚያ ድክመት ጋር፡ ይባስ፡ *ሥጋዊው ስስትና ብልጭልጩ* ነገር፡ በተለይ ከፈረንጅ ሲመጣ፥ ደግሞም፡ በዚያን ጊዜ፡ ልዩ ኃይል ስላለው፡ ያ የፍትወት ምርኮኛነትና መታለል ተደማምሮ፡ ከሽንፈት፡ ያውም፡ ከሃይማኖት ሽንፈት አደረሳቸው።

## የድሉን አክሊል፡ ወደሽንፈት ደለል።

የጦር ፊታውራሪያቸው፡ አለቃ ዘካርያስ፡ በታላቅ አመታት ድል ያደረጉት፡ ያ መሠሪ፡ ተኵላ ጠላት፡ አሁን ደግሞ፡ በበግ ለምድ ተሠውሮና በሌላ ተመስሎ፥ መምጫ መንገዱንም ለውጦና አዘናግቶ፥ እንዳስለመደውም፡ በጨለማ፥ በምሥጢር፥ እንደሌባ፡ አጥር ጥሶ ገብቶ፡ እየነጠቀ ሊወስዳቸው ሲመጣ፡ እነርሱም፡ እንደጦር መሪያቸው፡ እንደአለቃ ዘካርያስ፡ ጠላትን እስከመጨረሻው፥ እስከሞት ድረስ ተቋቁመው በመመለስ ፋንታ፡ እየራሳቸውን፡ ለሃይማኖት ውድቀት በመዳረግ፡ እጃቸውን እየሰጡ ተማረኩለት። "የአለቃ ዘካርያስ ደቀ መዛሙርት" እስከመባልና ለየራሳቸውም፡ "አለቃ" የሚለውን ማዕርግ እስከመቀበል ከደረሱት መካከል፡ ለታማኝ ባለአደራነት ያልበቁትን፡ እነዚያን፡ ደካሞች፥ ድልሎችና የክህደት ምርኮኞች፡ ጠላት፡ ድል አድርጎ፡ የውርደት ሸማቸውን እንደተከናነቡ፡ ወደእርሱ ጎራ ወስዶ ቀላቀላቸው።

ለዚያ ሽንፈትና ምርኮኝነት፥ ለዚያ ውድቀትና ውርደት፡ ቀንደኞች መሪዎች ከነበሩት መካከል፡ ለምሳሌ ያህል፡ የአለቃ ኢሳይያስና የአለቃ ሞትባይኖር ስም በምሳሌነት ሊጠቀስ ይቻላል። ይህም ሲኾን፡ "አለቃ" ብሎ "አድቬንቲስት!" የማያሰኝ፥ "አለቃ" ተብሎ፡ "ለጠላት እጅ መስጠት!" የማያስኼድ መኾኑን በመጠቆም ነው። ከታማኞቹ መካከል ግን፡ ከአለቃ ዘካርያስ ልጆችና ባሎቻቸው ጋር፡ የእነአባ ገብረ እግዚአብሔርና የእነአለቃ ብርሌ ስም፡ በመልካም ሲወሳ ይኖራል።

አለቃ ዘካርያስን "ይተካሉ" የተባሉት ወንዶች የልጅ ልጆቻቸው፡ አብዛኞዎቹ፡ በፋሺስት ጣልያን እጅ፥ ከዚያ በፊትና ከዚያ በኋላም፡ በአገር ውስጥ በነበረው አለመረጋጋት፥ በድንገተኛ ደዌም፡ አንድ አንድ እያሉ ስላለቁ፥ በሕይወት የነበሩትም፡ ገና ለአቅመ አዳም ስላልደረሱ፥ ከደቀ መዛሙርቶቻቸውም መካከል፡ የእርሳቸውን መንበር ለመውረስ የበቃ ምሁር ባለመኖሩ፡ እኒህ ኹሉ ኹኔታዎች፡ አድቬንቲስቶቹን ስለረዷቸው፡ ከአለቃ ዘካርያስ ደቀ መዛሙርት መካከል፡ የተመረጡትን ሳይቀር፡ በአድቬንቲስት ሃይማኖት እያሳመኑና ኹለተኛ ጥምቀት እያጠመቁ፡ የእነርሱ ሃይማኖት አባሎችና አገልጋዮች አደረጓቸው።

በዚህ ጊዜ፡ *"በጠበበው ደጅ* (በተዋህዶ ሃይማኖት) *ግቡ! ወደጥፋት የሚወስደው* (የአድቬንቲስትና ሌላው እምነት)፡ *ደጁ፡ ሰፊ፥ መንገዱም፡ ትልቅ ነውና! ወደእርሱም የሚገቡ፡ ብዙዎች ናቸው። ወደ ሕይወት የሚወስደው፡ ደጁ፡ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና! የሚያገኙትም፡ ጥቂቶች ናቸው። የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ፥ በውስጣቸው ግን፡ ነጣቂዎች ተኵላዎች ከኾኑ ከሓሰተኞች የሃይማኖት መምህራን ተጠንቀቁ! ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ! ከእሾህ ወይን፥ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? …ማንም እንዳያስታችሁ፡ ተጠንቀቁ! ብዙዎች፡ 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ፡ በስሜ ይመጣሉና! ብዙዎችንም ያስታሉ።*

*"...ማንም: 'እነሆ: ክርስቶስ: ከዚህ አለ!' ወይም: 'ከዚያ አለ' ቢላችሁ አትመኑ! ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸውስ: የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ: ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ!" የሚለውን: የጌታቸውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል* እንዲጠብቁ: አለቃ ዘካርያስ: ለደቀ መዝሙሮቻቸው: ከአደራ ጋር[፷፬] ሰጥተዋቸው የነበረው ማስጠንቀቂያ: መረሳቱና አለመጠበቁ ተረጋገጠ!

**ሐሳዊው ዘመቻ ተፋፍሞ ሲካኼድ፡፡**

እኒሁ የአድቬንቲስት ልኡካን: ወደእነርሱ ሃይማኖት በለወጧቸው: በእነዚያ ደካሞች አገልጋዮቻቸው: ምቹ መሣሪያነት: አለቃ ዘካርያስ: ከአጼ ምኒልክና ከንግሥት ዘውዲቱ ያገኟቸውን የአዋጅ ወረቀቶች: ቀደም አድርገው: በልዩ ልዩ ዘዴ: ከወራሾቻቸውና ከተጠሪዎቻቸው በመውሰድ: ከወኪሎቻቸው እጅ አስገብተዋቸው ስለነበረ: ስለማንነታቸው ለሚጠይቋቸው ኹሉ: ለባላገሮቹም ኾነ ለመንግሥት ባለሥልጣኖች: "እኛ እኮ ያለቃ ዘካርያስ ተከታዮች ነን!" እያሉ በማታለልና ያንን የአዋጅ ቃል: በማስረጃነት እያቀረቡ በማሳየት: በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መካከል እየተዘዋወሩ: እውነተኛው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት ሐዋርያና ኢትዮጵያዊ ሰማዕት የኾኑትን አለቃ ዘካርያስን: መልካም ስማቸውንና በጎ ምግባራቸውን: በርኵሰት ተንኰላቸው መበከል ቀጠሉ!

አጼ ኃይለ ሥላሴ: አለቃ ዘካርያስን: ማንነታቸውንና ምንነታቸውን: ማለትም: ሃይማኖታቸውንና ምግባራቸውን: በዝና ብቻ ሳይኾን: በግንባር ጭምር: ቀደም አድርገው: ከማንም የበለጠ: በቅርብ ያውቋቸዋል፡፡ እጅግ የሚያሳዝነው: እንደዚያ: የሚያውቋቸውንና ሊመሰክሩላቸው የሚችሉትን ታላቅ ሰው፥ በአገር ደረጃም: ጀግና አርበኛና ባለሙያ: ኋላ: ባዕዳኑ አድቬንቲስቶችና ተከታዮቻቸው: መጥተው: "የለም! እርሳቸው እኮ: የእኛ: የአድቬንቲስት ሃይማኖት ተከታይ ናቸው!" ብለው: ይህን የመሰለውን ግዙፍ ሐሰት: ያለኀፍረት: በድፍረት ሲያቀርቡላቸው: ምንም ጥያቄ ሳያነሡ: እንዴት ዝም ብለው ተቀበሏቸው? የሚያሰኘው: ተከታዩ ድርጊታቸው ነው፡፡

የእኒያ ደፋሮችና ኀፍረተ ቢሶች ጥያቄ: ያው እንደሚታየው: በአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ዘንድ: ተቀባይነትንና እውቅናን አግኝቶ: እነዚህ ባዕዳን የሃይማኖት ልኡካን: በጊዜው ሕግ መሠረት: "የባዕዳን ሃይማኖት ልዑካን ሊገቡበት አይቻልም!" በተባለው: "ዝግ በኾነው ክልል" ውስጥ በሚገኘው: በደብረ ታቦር ከተማ: በአለቃ ዘካርያስ ስም: ከመንግሥት: ቦታ ተቀብለው: ያን ቦታ: መደበኛ ሠፈራቸው አደረጉት፡፡ በዚያም: "ጉድመንሰን" በተባለ: ፈረንጅ አድቬንቲስት አማካይነት: ትምህርት ቤትና ሕክምና ቤት አቋቁመው እንዲሠሩ ተፈቅዶላቸው: አሁንም: በአለቃ ዘካርያስ ስም: በመላ በጌምድርና ጎንደር፥ ላስታና ወሎ ድረስ እንደልባቸው እየተዘዋወሩ እንዲሰብኩ መብቱ ተሰጧቸው: የሐሰት ዘመቻቸውን በስፋት ቀጠሉ፡፡ በዚህም አድራጎታቸው: ከራሳቸው ከአለቃ ዘካርያስ ቤተሰቦች መካከል: አንዳንዶቹን፥ ከተወላጆቻቸውና ከደቀ መዝሙሮቻቸው ጀምሮ: ከእስልምና ወደክርስትና ከመለሷቸው መካከል ደግሞ: ብዙዎቹን: ሃይማኖታቸውን እያስለወጡና እንደገና እያጠመቁ: ከኢትዮጵያዊነት አውጥተው: አድቬንቲስት አደረጓቸው፡፡

በተከታታዮቹም ዓመታት፡ በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢዋ፡ በአቃቂና በሻሸመኔ፡ “ኮየራ” በተባለው ሥፍራ፡ ትምህርት ቤቶችንና ሕክምና ቤቶችን እንደፈለጉ እያቋቋሙና ሃይማኖታቸውን እያስፋፉ፡ የቅዱሱ ኪዳን ወገን የኾነውን ኢትዮጵያዊ፡ የእነርሱ ሃይማኖት ተከታይ እንዲያደርጉ፡ ልቅ የኾነ ድጋፍ ተሰጣቸው:: በአዲስ አበባም፡ በቤተ መንግሥቱ አካባቢ፡ ከፍል ውኃው ጋር በተያያዘው ቦታ ላይ ሳይቀር፡ ሠርተው ከሚያካኺዱት ሕክምና ቤት ሌላ፡ በዚሁ ክልል፡ ቤተ ጸሎታቸውን ሊሠሩ የቻሉበትንም ፈቃድና ቦታ እስከማግኘት የደረሱበት እርዳታ ተደረገላቸው:: በአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛውን ሥልጣን ይዘው ከነበሩት የመኳንንት ልጆች መካከል፡ ብዙዎቹ በእነርሱ ትምህርት ቤት የተማሩ እንደነበሩም አይዘነጋም:: በየትምህርት ቤቶቻቸውና በየሕክምና ቤቶቻቸው ውስጥ፡ ይማሩና ይሠሩ በነበሩ፡ በተለይም፡ የተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች በኾኑ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ላይ፡ ከሕግ ውጪ፡ በማናለብኝነትና በትምክህት፥ ያለይሉኝታና ያለሥጋት፥ በይፋና በብዛት ያካኺዱት የነበረው፡ ሃይማኖት የማስለወጥ ተግባርና ዳግመኛ የማጥመቅ ሥርዓት፡ በዚያን ጊዜ፡ አድቬንቲስቶች፡ በቤተ መንግሥቱ ዘንድ የነበራቸው ቅርበት የቱን ያህል የሚያዝናናቸው፥ የሚያስመካቸውና የሚያስተማምናቸው እንደነበረ የሚያመለክት ነበር::

አዎን! አለቃ ዘካርያስ፡ በተለይ፡ “ነገላ” በተባለው ሥፍራ አቋቁመውት ባለፉትና ቋሚ ሐውልታቸው ኾኖ በሚገኘው፥ እስከዛሬም አገልግሎቱ ተስፋፍቶ በቀጠለው የሐዋርያት (አቦ) ቤተ ክርስቲያናቸው ምክንያት፡ ሕያው ማንነታቸውና ሌላው ግዙፉ የሥራ ፍሬያቸው፥ የሰማዕትነት ሙያቸውና አንጸባራቂ ዝናቸው፡ እንደፀሐይ ብርሃን ደምቆ የሚታይና የታወቀ ሲኾን፡ አድቬንቲስቶች፡ በአፄ ኃይለ ሥላሴና በመንግሥታቸው፡ እንዲያ ተማምነውና ተመክተው፡ ይህን ኹሉ እውነታ በመካድና በመተላለፍ፡ የአለቃ ዘካርያስ በኾነው በጎ ነገር ላይ ኹሉ፡ የፈጸሙት ዓይን ያወጣ ቅጥፈት፥ የድፍረት ሐሰትና የማናለብኝነት ድርጊት፡ ከእነርሱ በፊት፡ ግብፃውያን የኢትዮጵያ በኾነው መልካም ነገር ላይ ካደረሱት በደል የማያንስ፥ በይቅርታ ሊታለፍ የሚቻል እንኳ ቢኾን፤ ጠባሳው ሊፋቅ የማይቻል ኾኖ ሲታወስ ይኖራል::

## የአለቃ ዘካርያስ ልጆች አቤቱታ ሲሸነገል::

አድቬንቲስቶች፡ የግል ዓላማቸውን፡ ከግብ ለማድረስ ሲሉ፡ በአለቃ ዘካርያስ ስምና ሙያ፥ በማስረጃ ወረቀቶቻቸውም እየተጠቀሙ፡ የፈጸሙትና እየፈጸሙ ያሉት፡ እጅግ አሳዛኝ በደል ታውቆ፡ እውነቱ እንዲወጣ፥ ከሥጋዊዉም፥ ከመንፈሳዊዉም ሕግጋት ውጪ፡ እንደዚያ በሐሰትና በተንኮል ያጎደፉት የአባታቸው መልካም ስምና ሥራ ይታደስ ዘንድ፡ የተወሰደባቸውና የተነፈጋቸው መብታቸው እንዲመለስላቸው በመጠየቅ፡ በአባታቸው የተዋህዶ ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊነት ጸንተው የተገኙት፡ ታላቂቱ የአለቃ ዘካርያስ ሴት ልጅ፡ እማሆይ ወለተ እግዚአብሔር፡ ከልጃቸው ከእማሆይ ድንስር ገብረ እግዚአብሔርና ከልጅ ልጃቸው ከወይዘሮ ራሔል ዘካርያስ ጋር ኾነው፡ አቤቱታቸውን ለአፄ ኃይለ ሥላሴ አቀረቡ::

ከዚህም ጋር፡ በጥብቅ ተፈልጎ ወደቤተ መንግሥቱ እንዲመጣ ተደርጎ የነበረውም፡ አለቃ ዘካርያስ፡ እስላሞችን የረቱበት መጽሐፋቸው፡ "እንዲመለስልን" ሲሉ፡ አብረው ያቀረቡት ጥያቄ ነበር።

ዳሩ ግን፡ ዘመኑ፡ ሓሰት የነገሠበት ጊዜ ስለነበረ፡ ያ ጥያቄያቸው ጭምር፡ መላው አቤቱታቸው፡ የውሃ ሽታ ኾነ! ለሽንገላ ያህል፡ ለታላቂቱ ልጅ፡ አነስተኛ የጡረታ አበል ከመፈቀዱ በቀር፡ ያ ኹሉ የደካሞቹ ውጣ ውረድ፡ ከንቱ ኾኖ መቅረቱን፡ ዛሬ በሕይወት ያሉት፡ የመጨረሻዪቱ፡ የአለቃ ዘካርያስ፡ የልጅ ልጅ ልጅቱ ያዘክሩታል።

## የታመነ ተመልካችን ያጣ፡ ቤተ መንግሥት።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ከአድቬንቲስቶች ጋር የነበራቸው የወዳጅነት ግንኙነት፡ የቱን ያህል የተቀራረበና የተሣሠረ፥ እስከመጨረሻውም ጸንቶ የቀጠለ መኾኑን፡ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ፡ የግላቸው ወጥ ቤት ኾና እስከዕለተ ሞታቸው ድረስ ስታገለግላቸው የኖረችው ሴት፡ በአዲስ አበባ አካባቢ፡ የአድቬንቲስቶቹ ትምህርት ቤት ሥራ መሪ፡ የአቶ ሓንሰን ባለቤት፡ አሜሪካዊቷ ወይዘሮ ሓንሰን በመኾናቸው፡ ታውቆ ተረጋግጧል።

በዚህ ኹኔታ፡ በተለይ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ከዕድሜያቸው አረጋዊነት የተነሣ፡ በአካልም፥ በአእምሮም እየተዳከሙ በኼዱበት በመጨረሻው ዘመናቸውና ይልቁንም፡ ያከብሩዋቸው፥ ያደምጧቸውና የድፍረት ጥፋት ላለማድረግም፡ ይፈሩዋቸው የነበሩት ባለቤታቸው፡ እቴጌ መነን፥ መምህረ ንስሓቸው፡ እጨጌ ባስልዮስና እነራስ ካሣን የመሰሉ የዘመድ ጓደኞቻቸው በሌሉበት ጊዜ፡ ይህች አክራሪ የአድቬንቲስት ሴት፡ እንኳንስ በሚያስቡት፥ በሚናገሩትና በሚያደርጉት ይቅርና፡ በሕይወታቸው ላይ ሥልጣን እንደነበራት መገመት፡ ለማንም ተመልካች አያዳግትም።

በአገሪቱና በሕዝቡ ላይ፡ አደገኛ ፍጻሜን ሊያስከትል የበቃው፡ ያን የመሰለው አሳሳቢ ኹኔታ፡ በቤተ መንግሥቱ ውስጥና በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሕይወት አካባቢ፡ ጎልቶ በሚታይበት ጊዜ፡ ስማቸው ከላይ የተጠቀሰውን፡ የአጼውን፡ የቀደሙትን የቅርብ መካሪዎችና ጠበቂዎች "ተክተዋል" ሊባሉ ከሚችሉት ባለአደራ ባለሥልጣኖች መካከል፡ ለዚያ አሳሳቢ ኹኔታ፡ "መፍትሔ ያስገኛሉ" ተብለው ታምኖባቸው የነበሩት የትኞቹ ኖረዋል? እስቲ፡ ስማቸው፡ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን፡ አንድ በአንድ፡ እየመዘንን እንመልከታቸው!

አባታቸውን አጼ ኃይለ ሥላሴን እጅግ የሚፈሩትና የሚያከብሩት፡ ልዕልት ተናኘ ወርቅ? ለእርሳቸውማ፡ አብረን የደርግ እሥረኞች ሣለን፡ የፀረ ኢትዮጵያነትና የፈረንጅ አምላኪነት ዝንባሌ ያየሁባቸው፡ ፊታውራሪ ገብረ ሕይወት ወልደ ሓዋርያት የተባሉ ሰው፡ እንደራሴያቸውና አማካሪያቸው ነበሩ። ወይስ፡ ኢትዮጵያኛው፡ የግእዝ ቋንቋና ፊደል፡ በላቲኑ እንዲተካ፥ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት ደግሞ፡ በባዕዱ ኀብረተሰባዊ ርእዮተ ዓለም (Socialism ሶሺያሊዝም) እንዲለወጥ ይጥሩ የነበሩት፡ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ? ወይስ፡ በአስተዳደጋቸውና በአኗኗራቸው፥ በአስተሳሰባቸው ሳይቀር፡ የእንግሊዛዊነትን ጠባይ በገሃድ እያሳዩ፡ በዘውድ ተቀናቃኝነታቸው፡ ለርእሰ ብሔርነቱ ሥልጣን፡ ራሳቸውን ከማዘጋጀት ጋር፡ ወደመጨረሻው ዘመን፡ የቤተ ሕዝቡ (Parliament) የበላይ ተጠሪ የነበሩት፡ ራስ አሥራተ ካሣ?

ወይስ፡ ኋላ፡ በደርግ ጊዜ፡ አጼያቸውን፡ በይፋ በመክዳት፡ ማንነታቸውን የገለጹትና የራሳቸው ሥውር ዕቅድ የነበራቸው፡ የቤተ ክህነቱ የበላይ ተጠሪ፡ እጨጌ ቴዎፍሎስ? ወይስ፡ ፈረንሳዊት ሚስት አግብተው፡ መስሎቻቸውን ምሉካን (Ministres ሚኒስትሮች) እየመሩ፡ እንደኢትዮጵያዊ ሳይኾን፡ እንደፈረንጅ ይኖሩ የነበሩት፡ የቤተ ምልክናው የበላይ ተጠሪ፡ ጸሓፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ? ወይስ፡ ለረዥም ጊዜ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ልዩ ጸሓፊና ኋላም፡ ጸሓፌ ትእዛዝ ተብለው፡ በጽሕፈት ምሉክነት፡ የኢትዮጵያን መንግሥታዊ አመራር፡ ወደፈለጉበት አግጣጫ ለመለዋወጥ፡ ሥልጣን የነበራቸው፡ የእንግሊዞች ቃል አቀባይና የፀረ ማርያም ሃይማኖት ተከታዩ፡ አቶ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ? ወይስ፡ በአጼው ልዩ የውስጥ (Cabinet ካቢኔት) ጽሕፈት ቤት፡ የመንፈሳዊ ክፍል ኃላፊና አገልጋይ የነበሩት፡ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የተባሉት መነኵስ?

## የውድቀቱ መቃረቢያ፡
## አመልካች ድርጊት፡፡

በተለይ፡ እኚህ፡ ስማቸው፡ በመጨረሻ የተጠቀሰው መነኵሴ፡ በመንፈሳዊ ኃላፊነታቸው የሚሰጡት ምክር፡ እንኳን ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ቁም ነገር ያለው ሊኾን ይቅርና፡ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ እንኳ፡ ዘለዓለማዊ ጎጅነት ያለው በመኾኑ፡ የሚያስተማምን አልነበረም፡፡

ለዚህም፡ ማስረጃ ይኾን ዘንድ፡ ከድርጊቶቻቸው መካከል አንዱን ማቅረብ ይቻላል፡፡ እርሱም፡ በእኚሁ መነኵስ መሣሪያነት፡ በዚያው፡ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ፡ በማናለብኝነት ድፍረትና በይፋ የተፈጸመ፡ ሕገ ወጥ ተግባር ነው፡፡ ይኸው ሕገ ወጥ ተግባር፡ በሥጋም፡ በነፍስም፥ ማለትም፡ በምድርም፡ በሰማይም፡ ኹለት ግለሰቦችን ብቻ ሳይኾን፡ የኢትዮጵያን፡ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፥ ከዚያም አልፎ፡ ቤተ ሕዝቡን፡ በጠቅላላ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን ሳይቀር፡ ከሌሎቹ በደሎች ጋር ተደማምሮ፡ በፈጣሪዋ ፊት፡ በኃላፊነት አስጠይቆ፡ ከፍተኛ የኾነ የቅጣት ዋጋን፡ በደም ሳይቀር ያስከፈለ ነው፤ ይህም ክፍያ ሲፈጸም አይተናል፤ ደግሞም፡ የሚመለከተው ኹሉ፡ በንስሓ ካልተመለሰ በቀር፡ ገና ወደፊትም ሲከፈል እናያለን፡፡

"ሕገ ወጥ" የተባለው፡ ያ ተግባር፡ በሚከተለው አጭር ዐረፍተ ነገር ሊጠቃለል ይቻላል፡፡ ይህም፡ እኚሁ መነኵሴ፡ የጦር አዝማች (General) ነጋ ተገኝ የተባሉትን ኢትዮጵያዊ ወገናቸውንና አንዲት የውጭ አገር ዜጋ የኾነችን ሴት፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ "ገዳም"፡ በተክሊል ካጋቡ በኋላ፡ ቆይተው ደግሞ፡ ይህችኑ ምስኪን ባዕድ ሴት፡ በራሳቸው አፋቺነት፡ ከወለደችለትና ከምትወድደው ባሏ አለያይተው፡ እኚሁ ባል ተብየው፡ ከቤተ መንግሥት፡ ልዕልት ኂሩት ደስታ የተባሉትን የልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴን ልጅ እንዲያገቡ፡ ማለትም፡ በጋብቻ ላይ ጋብቻን እንዲፈጽሙ ከመፍቀዳቸው በላይ፡ እነዚሁኑ፡ አዲሶቹን ተጋቢዎች' በዚያው፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ "ገዳም"፡ በኹለተኛ ተክሊል ማጋባታቸው፡ በመለኮታዊው ምሥጢርና ሥርዓቱ ላይ ያስከተለው ታላቅ ኃጢአት ነው፡፡

ስለዚህ ድርጊት አፈጻጸም፡ በዚያን ጊዜ፡ ቅርበት ስላልነበረኝ፡ ዝርዝሩን፡ ይህን ያህል ጠልቄ ባላውቀውም፡ በተለይ፡ በቤተ ክህነቱ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ሕዝቡ የሥልጣን መናብርት ላይ ተቀምጠው ሊተመለከቱት ሰዎች፡ እንዴት ቀላል መስሎ ታይቷቸው፡ በዝምታ እንዳለፉት፡ ከትዝብት ጋር ይገርመኛል። ነገር ግን፡ የፈተናው እሳት፡ ኋላ እያጠራ ባስገኘው ውጤት እንደታየው፡ በዚህ ረገድ፡ በኹሉም ዘንድ የነበረው አቋም፡ ተመሳሳይ ስለነበረ፡ ድርጊቱ፡ እንደቀላል ነገር ታይቶ፡ ታልፏል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሕግ የፈረሰበት፥ እጅግ ከባድ ኃጢአት መኾኑ አልታየም ነበር። ያሳዝናል!

ያም፡ የፈረሰው መለኮታዊ ሕግ፡ *"ባልና ሚስት፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ወደፊት፡ ኹለት አይደሉም! እንግዴህ፡ እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!"* የሚለው የጋብቻ ሥርዓት ነው! በዚህ፡ አንድ መነኵስ ካህን መሪና አስተባባሪ በኾነበት ድርጊት፡ ይህ አምላካዊ ሕግ እንደፈረሰ እንመለከታለን። መለኮታዊው ቃል፡ በዚህ ረገድ የሚለው ደግሞ፡ *"ከእግዚአብሔር ሕግ፡ አንዲቷ ነጥብ ከምትወድቅ፡ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀልላል! ሚስቱን የሚፈታ ኹሉ፡ ሌላዪቱንም የሚያገባ ያመነዝራል።"* ነው።

እንግዴህ፡ በዚህ መለኮታዊ ቃል መሠረት፡ ይህን የእግዚአብሔርን ሕግ ያፈረሰ፡ በእውነተኛ ንስሓ ካልተመለሰ በቀር፡ *ሥራው ብቻ ሳይኾን፡* እርሱ ራሱ[፻፹] ጭምር፡ መፍረሱ እንደማይቀር፡ በሃይማኖት ተረጋግጦ ታውቋል።

በዚያ ድርጊት፡ የእግዚአብሔር ሕግ፡ በንቀትና በድፍረት መፍረሱ ብቻ ሳይኾን፡ የጋብቻ ሥርዓትና የመልካም ቤተሰብ አቋምም፡ ጨርሶ እንዲፈራርስ፥ የሴቶችም ክብርና መብት እየተናቀ እንዲደፈር፡ ዲያብሎስና ባዕዳን፡ በኢትዮጵያ ላይ ሲያካኺዱ የኖሩት፡ ምሥጢራዊ ዘመቻ ተጋለጠበት! የኢትዮጵያ ቤተ ምልክና (ቤተ መንግሥት)፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ሕዝብ የተባበሩ መኾናቸው ተረጋገጠበት! ስለዚህ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ የሚታየው፡ የጋብቻ፥ የቤተሰብና የአገር መፈራረስ፡ "መድረሱ አይቀርም" ተብሎ የተጠበቀ እንጂ፡ እንደእንግዳ ደራሽ፡ አዲስ ኾኖ፡ ሊያስደንቅ አይችልም።

ያ፡ ለመለኮታዊው ሕግ መፍረስ ቀንደኛ ተጠያቂ የኾነው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ የፍርዱን ቅጣት ተቀብሎ ሲፈርስ፡ የእግዚአብሔር ሕግ የፈረሰበት፡ ያ፡ የጦር አዝማቹና የልዕልቲቱ ጋብቻም፡ አብሮ ፈረሰ! ጋብቻው፡ እንዲያ ባጭር ጊዜ ውስጥ መፍረሱ፡ ጥንቱኑ እንዲቆም የተደረገው፡ በእውነተኛው የእግዚአብሔር መሠረት ላይ ሳይኾን፡ በሌላው ሰብአዊ ዓላማና ጥቅም ላይ ለመኾኑ፡ ፍጻሜው ራሱ አረጋግጦ አሳይቷል።

አድቬንቲስቶችን በሚመለከት፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ የተገለጸው ዝርዝር ኹኔታ፡ ለምሳሌና ለዓይነት ያህል ተጠቅሶ የቀረበ እንጂ፡ በዚህ ረገድ፡ ለካቶሊካውያንና ለሌሎቹ የፀረ ማርያም ድርጅቶች የሃይማኖት ልኡካን ይደረግላቸው የነበረው አስተያየት፥ ይበረከትላቸውም የነበረው የተትረፈረፈ ችሮታ፡ ተመሳሳይ እንደነበረ ሊታወቅ ይገባል።

## ግራ የሚያጋባና አደናጋሪ ምግባር

በአንድ ወገን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነትን የሚያዳክሙ፡ እነዚህና እነዚህን የመሰሉት፡ ጎጂ ተግባራት፡ በይፋ እየተካኼዱ እያሉ፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ይህችው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ዘንድ፡ ሞገስን ያገኘችና ድጋፍም ያላት መስላ የምትታይባቸው፡ አንዳንድ፡ አስደናቂና የጎሉ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ይታያል:: እነዚህም፡ የጳጳሳትን፥ የሊቃነ ጳጳሳትንና የርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳትን ሢመት፥ እንዲሁም፡ የአብያተ ክርስቲያናትን መታነፅ የመሳሰሉት ናቸው:: እዚህ ላይ፡ ልብ አድርጎ፡ ማስተዋል ነው::

ይህ ኹሉ የሚኾነው፡ ለእነዚህ የክህነት ማዕርጋትና የአገልግሎት ሕንፃዎች፡ ዋና ምንጮች ኾነው፡ አስፈላጊዎቹን የሃይማኖት እውቀቶችና መንፈሳውያን መሣሪያዎች፡ እያዘጋጁ በማበርከት ረገድ፡ የዚህችው ቤተ ክርስቲያን፡ መሠረታውያን አቋሞችና ምሰሶዎች የኾኑት፡ መምህራንና ትምህርት ቤቶች፡ ጸንቶ የኖረው ህልውናቸው፡ እጅግ በተራቀቀና ሥርዓት ባለው ዘዴ፡ እየተገዘገዘ፥ የውድቀት ጉዟቸውም፡ ይፋ በኾነ መልክ፡ ነገር ግን ሳይታወቅ፡ ቀስ በቀስ፡ እየተዳከመ፥ እየተጕሣቈለና እየፈራረሰ ኼዶ፡ በመጨረሻ እንዲወድም የማድረጉ ሥውር ዘመቻ በሚከናወንበት ጊዜ ነበር::

እንግዴህ፡ ይህ ኹኔታ፡ ለማንም፡ ግራ የሚያጋባ፥ እንቆቅልሽ የኾነና የማይጣጣም ምሥጢርን ያዘለ ኾኖ የሚቀርብ በመኾኑ፡ ማንኛውም ሰው፡ "ከዚህ ኹሉ የተመሣጠረ ድርጊት በስተጀርባ ያለው ኀቡዕ ዕቅድ፥ መንሥዔውና ዓላማው፡ ከቶ ምንድር ነበር?" ብሎ ቢጠይቅ አግባብ ይኾናል:: ነገር ግን፡ ለዚህ ጥያቄ፡ ምላሽ የሚኾነውን ቃል ለመስጠት፡ እኔም ኾንሁ፡ ሌላ ማንም ሰብአዊ ፍጡር፡ ችሎታውም፥ መብቱም፥ ሥልጣኑም ያለን አይመስለኝም:: ችሎታውም፥ መብቱም፥ ሥልጣኑም ያላት፡ *የእግዚአብሔር እውነት* ብቻ ናት:: የእርሷም መልስ፡ ተጨባጭ የኾነው፡ ራሱ እውነታው ነው:: እርሷም፡ በዚህ ረገድ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የመጨረሻ ዘመን፡ እንደሰንሰለት ተያይዘውና ተከታትለው፡ እስካሁን በደረሱትና አሁንም እየተካኼዱ ባሉት፡ አሳዛኝ ኹኔታዎች አማካይነት፡ መልእክትና ትርጉም ያለውን መልሷን፡ እነሆ፡ በገሃድ ሰጥታለች፤ እየሰጠችም ነው፤ ገና ወደፊትም ትሰጣለች! አዎን! አሳዛኝ የተባሉት፡ እነዚያ ኹኔታዎችም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴና ትውልዳቸው፡ ለዚያ መሠሪ ኀቡዕ ዕቅድ የከፈሉት አሠቃቂ ዋጋ ነው::

## ኢትዮጵያ፡ እስላሞችን ስትፋረድ!

በዚያን ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ሼህ ዘኸርያን፡ ከሌላ ሳይኾን፡ ከራሳቸው፡ ከእስላሞች መካከል፡ ለምን አስነሣ? መቼም፡ እግዚአብሔር፡ ኹሉንም ነገር፡ ያለምክንያት እንደማያደርገው፡ እስላሞችም ያምናሉ:: ሼህ ዘኸርያን፡ ለዚያ ተልእኮ ጠርቶ፡ ያንን የመሰለ፡ የማይበገር አንደበት የሰጣቸውና የሌላ መጽሐፍ ጥቅስን ሳይጨምሩ፡ በዚያው፡ በቁርዓኑ ቃል ብቻ፡ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ድልን ያጎናጸፋቸው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ መኾኑን፡ ቅን ልቡና ያላቸው ኹሉ ያምኑበታል::

በዚያን ጊዜ የነበሩትም ኾኑ፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ፡ ታሪካቸውን የተከታተሉት፥ ዛሬም፡ በኢትዮጵያ የሚገኙት እስላሞች ጭምር፡ ይህን እውነታ ደህና አድርገው እንደሚያውቁትና እንደሚያረጋግጡት አይጠረጠርም።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ "እግዚአብሔር" ብለን የምንጠራውና የምናመልከው፡ የፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ የረቂቁም፡ የግዙፉም ፈጣሪ፡ እነርሱ እስላሞችም፡ "አላህ" ብለው የሚጠሩትና የሚያመልኩት፡ ያው፡ እርሱው ከኾነ፡ ታዲያ፡ ይኸው፡ የኹላችን፡ አንዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ ሺህ ዘኸርያን፡ በዚያን ዘመን ያስነሣቸው፥ በኢትዮጵያ ውስጥና ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚኖሩ እስላሞች፡ ምን መልእክትን ሊያስተላልፍ ፈልጎ ኖርዋል? ዛሬስ፡ ይህ መልእክት፡ በይፋ ተጽፎ እንዲወጣ ያደረገው ስለምንድር ይኾን? ምናልባት እስላሞች፡ የሃይማኖታቸው መሥራችና መሪ፡ መሐመድ፡ ገና በመነሻ ዘመኑ፡ በራሱ አገር፡ ከተቃዋሚዎቹ፡ መከራና ስደት በደረሰበት ጊዜ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በእንግዳ ተቀባይነታቸው፡ ለወገኖቹ፡ የጥገኝነት መስተንግዶን በማበርከት፡ ላደረጉላቸው ቸርነት፡ ውለታ መላሽ በመኾን፡ "አበሾችን አትንኳቸው!" የሚለውን የአደራ ቃሉን በመተላለፍ፡ ተፃራሪ ድርጊትን ለመፈጸም አስበው ይኾን?

ይህን የመሰለው አስተሳሰብ ደግሞ፡ "አይኖርም!"፥ "ሊኖርም አይችልም!" እንዳይባል፡ በ፲፮ኛው ምዕት ዓመት፡ በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን፡ አሕመድ ግራኝና ተከታዮቹ፡ ያን፡ የእስልምና ሃይማኖት፡ መሥራችና መሪ ቃል በመተላለፍ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ በፈጸሙት ወረራና ግድያ፡ ታይቷል። ያም የእልቂት ዘመን፡ በመላው፡ የኢትዮጵያ ቅዱስ ኪዳን ሕዝብ ዘንድ፡ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ኾኖ፡ እነሆ፡ ዘወትር ሲታወስ ይኖራል።

## የመሐመድ የ"አደራ" ቃል።

የእስልምናው መሥራችና መሪ፡ መሐመድ፡ የሰጠው፡ ያ፡ ሃይማኖታዊ ቃል፡ ቋሚ እንጂ፡ በማንም ፍጡር፡ ወይም በምንም ጊዜ፡ ወይም በማናቸውም ቦታና ኹኔታ ወይም በምንም ዓይነት ትርጉም፡ የሚሻር፡ ወይም የሚለወጥ አለመኾኑን፡ እንኳንስ፡ ሃይማኖታቸውንና የመሪያቸውን ቃል አክብረው የሚጠብቁት እስላሞች ይቅሩና፡ የሌሎቹ ሃይማኖቶች ተከታዮችም፡ በትክክል ያውቁታል። ይህ፡ የእስላሞች የእምነት አቋም፡ በድርጊት የተፈጸመ፡ እውን መኾኑን፡ እስከዚች ቀን ድረስ ያለው፡ "ጊዜ" ራሱ አረጋግጦታል። ይኸውም፡ እስላሞች፡ "ጂሃድ" (እስልምናን ለማስፋፋት የሚታወጅ ጦርነት) እያሉ፡ ሃይማኖታቸውን፡ በመካከለኛው ምሥራቅና በአካባቢው ክፍለ ዓለም፡ በሠይፋቸው ሲያስፋፉ፡ ኢትዮጵያ ብቻ፡ ከዚህ ጂሃዳቸው፡ ነጻ ኾና ልትጠበቅ የቻለችው፡ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር፡ በዚህ የመሪያቸው ቃል ምክንያት ጭምር መኾኑ ሊታበል አይቻልም።

እስላሞች፡ ይህን ሲያደርጉ፡ ራሱ፡ መሪያቸው መሐመድ፡ በቃሉ እንዳረጋገጠላቸው ኹሉ፡ ኢትዮጵያ፡ *"ምአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነትና "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" በተባለችው፡ በኢትዮጵያዊት እናቱ ድንግል ማርያም ንግሥትነት፡ የእግዚአብሔር የዘውድ መንግሥቱ መዲናና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝቡ መሰባሰቢያ ኾና፡ ለአያሌ ሺህ ዓመታት በነጻነት የኖረች አገር ለመኾኗ፡ እውቅናን በመስጠት እንደነበረ አሌ አይባልም። ይህ፡ የእስላሞች ሃይማኖታዊ አቋም፡ የደርግ መንግሥት እስከተቋቋመበት፡ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ድረስ ጸንቶ ቀጥሏል ሊባል ይቻላል። እንግዴህ፡ የእስልምና መሥራቹ መሐመድ፡ ያን የመሰለውን፡ የአደራ ቃል፡ ለተከታዮቹ፡ በቃል ብቻ ሳይኾን፡ በጽሑፍ ጭምር ትቶ ያለፈው፡ ያን የመሰለውን እውቅና ለሰጣት፡ ለዚህችው ኢትዮጵያና ሕዝቧ መኾኑ ሊዘነጋ አይገባም።

የእስላም ወገኖች ኹሉ፡ ለኢትዮጵያ ያላቸው ባለውለተኛነት፡ ከሃይማኖት መሪያቸው የተለየ ሊኾን አይችልም፤ አይገባምም። ምክንያቱም፡ እስላሞች፡ ከመሐመድ ዘመን ጀምሮ፡ በዚህችው አገር ውስጥና በሕዝቧ መካከል በመኖር፡ የተደረገላቸው የቸርነት ሥራ፡ ከመጀመሪያዎቹ እስላሞች የተለየ ስላልኾነ ነው። በመካከሉና አልፎ አልፎ፡ በኢትዮጵያውያን በኩል፡ ከእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት ውጪ፡ የተደረገ ስሕተትና ጥፋት ቢኖርም እንኳ፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፡ በየቦታው፡ በሰፊው እንደታተተው፡ ለዚያ ስሕተትና ጥፋት፡ በመለኮታዊው ዳኝነት፡ በየዘመናቱ፡ ከፍተኛ የቅጣት ዋጋ እንደከፈሉበት፡ በራሳቸው፡ በእስላሞች ዜና መዋዕል ሳይቀር፡ ተመዝግቦ የሚነበብ ነው፤ ዛሬም፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እየተካኼደ ባለው፡ የእርስ በርስ ጦርነትና ረሃብ፥ ቸነፈር (በሽታ) እና ስደት፡ ይኸው ቅጣት እየወረደ፡ በገሃድ ሲፈጸም ይታያል።

እስላሞች፡ የሚያዳምጡትና የሚከተሉት፡ "ከአምላክ የበለጥን፡ አዋቂዎች ነን" የሚሉትን፡ የዓለማውያን ሥነ መንግሥት ፈሊጠኞችን (Politicians የፖለቲካ ሰዎችን) አሳብና ቃል ሳይኾን፡ የእግዚአብሔርን ሕግና የመሪያቸውን ቃል መኾኑ፡ በዓለም ሃይማኖተኞች ዘንድ እንደተመሰከረላቸው፡ ራሳቸውም ያውቁታል።

## የጊዜው የእስላሞች አዝማሚያ።

ይኹን እንጂ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ በተለይም፡ ከየካቲት ወር፡ ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. አንሥቶ፡ በኢትዮጵያ በሚኖሩ እስላሞች ዘንድ የሚታየው ኹኔታ፡ ያን የመሐመድን የአደራ ቃል እንደረሱ የሚያስመስላቸውን አዝማሚያ እንደያዙ ያመለክታል። ይኸውም፡ ኢትዮጵያን፡ በጂሃድ፡ ማለትም፡ በገሃድ ጦርነት ሳይኾን፡ በገንዘብ ኃይልና በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ፡ በጋብቻ ሳይቀር በሚፈጸም፡ የስልት መንገድ፥ እንዲሁም፡ በሥነ መንግሥት (political የፖለቲካ) ትግል፡ መንግሥታዊ ሥልጣን ይዘው፡ አገሪቱንና ሕዝቡን፡ እስላም ለማድረግ፡ የሚያካኺዱት ግልጽና ረቂቅ ዘመቻ ነው።

ይህም፡ Dr. (ዶክተር) አብዱል መጂድ ሁሴን የተባሉት፡ የሕዝብ ወኪል፡ የአሁኑ ሕገ መንግሥት በተመከረበት ብሔራዊ ሸንጎ ላይ ሲናገሩ፡ እንግዲህ፡ በኢትዮጵያ የሚታነፁት መስጊዶች ቁጥር፡ በአገሪቱ ላይ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ልክ ብቻ ሳይኾን፡ በእጥፍ መኾኑን የሚያሳዩ መኾናቸውን በድንፋታ በተናገሩት ቃልና በአሁኑ ጊዜ፡ ሼህ መሐመድ ሁሴን አልዐሙዲን የሚባሉት ከበርቴ፡ በመላ ኢትዮጵያ፡ በተለይም፡ ጥንተ ክርስቲያን በኾነው፡ በዐማራው ወገን ላይ አነጣጥረው በሚያካኺዱት፡ ወሰን በሌለውና እጅግ ልቅ በኾነው የገንዘብ መናኘት+ የሀብት ይዞታ ማስፋፋትና የጋብቻ ተግባር በግልጽ ይታያል::

ይህ ዝንባሌያቸውና ሙከራቸው፡ ባሁኑ ጊዜ፡ እንዲህ በገሃድ መከሠቱ፡ ሳያስደንቅ ይችላል:: ምክንያቱም፡ ቀደም ብሎ ከተገለጸውና ዛሬ ካለው ኹኔታ፡ በቀላሉ መገንዘብ እንደሚቻለው፡ "'ኢትዮጵያውያንን አትንኳቸው!' የሚለው፡ የመሐመድ ቃል የሚጸናው፡ ያች ኢትዮጵያ፡ እውነተኛ ማንነቷን፡ ማለትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷንና ሥርዓተ መንግሥቷን ጠብቃ እስከተገኘች ድረስ ብቻ በመኾኑ ነው፤ይህም፡ ኢትዮጵያና ሕዝቧ፡ ከዚያ ውጪ በሚኾኑበት ጊዜ፡ ማለትም፡ መሪያቸው መሐመድና ተከታዮቹ እስላሞች፡ በዚያ ጥንታዊ አቋሟ፡ አውቀዋትና አክብረዋት የኖሩት፡ ያች ኢትዮጵያ፡ በአሁኑ ጊዜ እንደሚታየው፡ ያን፡ የታወቀ ሃይማኖታዊ ሥርዓቷን ትታ፡ በየጊዜያቱ፡ ሃይማኖት-አልባ የኾኑትን፡ የኅብረተሰባዊነትን (socialism)፡ ወይም፡ የጋርዮሽን (communism)፡ ወይም የሕዝባዊነትን (democracy) ርእዮተ ዓለማት በመከተል፡ ራሷን፡ ለተለያዩ ባዕዳን ፍልስፍናዎች አስገዝታ በምትገኝበት ጊዜ፡ ያ፡ "የመሐመድ ቃል አይጸናም" ማለት ነው:: በዚህም ጊዜ፡ እስላሞች፡ ከዚያ፡ ከመሪያቸው የአደራ ቃል፡ "ነጻ ይኾናሉ!" የሚለው ፍትሐዊ ውሳኔ፡ የሚያስኬድ ይኾናል:: ይህ ኹኔታ፡ በኢትዮጵያ ተከሥቶ፡ በይፋ በሚካኼድበት፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች፡ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ የኾነውን ኹሉ፡ ከሌሎች ባዕዳን ጋር እየተሻሙ፡ በመቀራመቱና በማጥፋቱ ትግል ውስጥ፡ ቀደምት ተሣታፊዎች ኾነው ቢገኙ፡ "ለዚህ ድርጊታቸው፡ በቂ ምክንያት አላቸው!" ከማለት በቀር፡ በምንም ሊያስደንቅ አይችልም::

ይህን ቁም ነገር፡ በተለይ፡ ኢትዮጵያዊው የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ፡ በብርቱ ሊያጤነው የሚገባ፡ የሕይወት፡ ወይም የሞት፡ ማለትም፥ የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ነው:: ምክንያቱም፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፡ ለአያሌ ሺህ ዓመታት፡ ሕያው አድርገው ያቆዩትን፡ የነጻነት ህልውናቸውን ጠብቀው መቀጠል የሚችሉበት ዕድል የተንጠለጠለው፡ በዚህ ቁም ነገር ላይ በመኾኑ ነው:: አዎን፡ የጥንታዊቷ ኢትዮጵያና የልጆቿ ኢትዮጵያውያን፡.የወደፊት ዕድል የተንጠለጠለበት የሚዛን ምላስ ያረፈው፡ ኢትዮጵያ፡ ያን፡ በእስላሞችና በክርስቲያኖች+ በአይሁድና በአረማውያን፡ በሌሎችም የዓለም ሕዝቦች ዘንድ የታወቀውን ማንነቷን፡ በመጠበቋና ባለመጠበቋ ሚዛን ላይ መኾኑን፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ አበክሮ ሊገነዘበው ይገባል::

## ለእስላሞች፡
## ሃይማኖታዊ ማስጠንቀቂያ!!!

እስላሞችም ኾኑ ሌሎቹ፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሃይማኖተኞች ኹሉ፡ በኢትዮጵያ ላይ ሊያደርሱ ስለሚያቅዱትና ስለሚያካኺዱት፥ የፈጸሙትም ክፉ ነገር ቢኖር፡ ስለዚያ ጽርጊታቸው፡ እጅግ መጠንቀቅ እንዳለባቸው የሚያውቁ ይመስለኛል፤ ይህን እውነታ፡ ለሌሎች ለማሳመንና ለማረጋገጥ፡ ብዙ ምክንያቶች ሊቀርቡ ይቻላል። ከእነዚህ መካከል፡ አንድ ኹለቱን ብቻ እጠቅሳለሁ፦ የመጀመሪያው፡ ኢትዮጵያ፡ በአዳምና ሔዋን ኪዳን ልቦና መሠረትነት፡ በቀጥታ፡ ከፈጣሪዋ ከተቀበለችው ሃይማኖቷ አንሥቶ፡ እስከዚች ቀን ድረስ፡ የእግዚአብሔር አምልኮትና ሕያዋን ቅርሶቹ ተጠብቀውባት የኖረች አገር መኾኗን የሚያረጋግጠው አቋሟ ነው፤ ኹለተኛው ደግሞ፡ በተለይ እስላሞች፡ "በእስልምና ሃይማኖታችን ውስጥ፡ ማንም ባዕድ፡ ጣልቃ ሳይገባብን፡ መንግሥትም፥ ሕዝብም ኾነን፡ በዚሁ የሃይማኖት ሕጋችን እየተዳደርን መኖር አለብን" ብለው፡ ይህን ፍላጎታቸውን፡ በየአገራቸው፡ አስከብረው እንደሚኖሩ ኹሉ፡ "ኢትዮጵያም፡ ይህን ማንነቷን፡ በዚሁ መልክ ጠብቃና አስከብራ መኖር፡ መብቷ መኾኑን መቀበል ይገባል" የሚያሰኘው የጋራ ድንጋጌ ነው።

እንግዴህ፡ እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ኢትዮጵያም፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት፤ ጥንታዊ አቋሟን እንደያዘች፡ ተጠብቃ፡ ህልውናዋን እንድትቀጥል ለማድረግ፡ እነርሱ፡ ማለትም፡ ሌሎቹ ሃይማኖቶችና እስላሞች ጭምር ኃላፊነት አለባቸው ማለት ይኾናል። ከዚህ የተነሣም፡ እስላሞችም ኾኑ ሌሎቹ ሃይማኖቶች፡ ይህን ሃይማኖታዊ ግዳጃቸውን፡ በሚፃረር መልክ፡ ኢትዮጵያን የሚጎዳ፡ አንዳች ተግባርን፡ መፈጸሙ ቀርቶ፡ ማሰቡ እንኳ፡ ያው፡ እርሱኑ፡ እስላሞች፡ "አላህ" በሚለው አጠራራቸው፡ የሚያመልኩትን አንዱን አምላክ እግዚአብሔርን፡ ማሳዘንና መለኮታዊ ቊጣውን፡ በራሳቸው ላይ መጋበዝ መኾኑን፡ ለአንዲት አፍታ እንኳ ሊዘነጉት እንደማይገባ፡ እዚህ ላይ ደግሜና አበክሬ ላሳስባቸው እወድዳለሁ።

እግዚአብሔር የሠራውን ማፍረስ፡ እንኳንስ፡ ሃይማኖታውያን በኾኑት፡ በእስላሞች ዘንድ ቀርቶ፡ ከሰብአዊው የተፈጥሮ ባሕርያቸው፡ ማለትም፡ ከሕሊናቸው ዳኝነት የተነሣ፡ በሃይማኖተ ቢሶችም ዘንድ እንኳ ቢኾን፡ እጅግ ያሠቅቃል! የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ ለማፍረስ መሞከርም፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማፍረስ መቃጣት ነው።

ኢትዮጵያውያንም፡ ምናልባት፡ ከአሕመድ ግራኝ በባሰ ጽናት፡ የመጨረሻውን ጥፋት ሊያደርስ፡ ከ"እግዚአብሔር አልባው አገዛዝ" (communism ኮሚዩኒዝም) እና ከ"ሕዝባዊ አገዛዝ" (democracy ዲሞክራሲ) ቀጥሎ፡ አሁን በተራው ተመዝዞ እየተምዘገዘገ ከሚገኘው፡ ሠይፍ ለመዳን፡ ምርጫውና ፍላጎቱ ካላቸው፡ በዚህ መጽሐፍና "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!" በሚል ርእስ፡ ቀደም ብሎ ታትሞ በወጣው መጽሐፍ ወደተገለጸው፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታቸው፡ በንስሓ ይመለሱ ዘንድ፥ ራሳቸውንም፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ረድኤት ለማይለየው፡ ለዚያ፡ የኢትዮጵያዊነት ጸጋ ያበቁ ዘንድ እየተማፀንኩ፡ እኔም፡ የመጨረሻ ጩኸቴን አሰማለሁ።

እዚህ ላይ፡ "ኢትዮጵያ" የምላት፡ ለእርሷ ባላቸው የሃይማኖት ቃል ኪዳን፡ ታማኞች ልጆቿ ኹነው የተገኙትን፡ የቀድሞውን፡ መሓመድ አሊን፥ የኋለኛውን፡ ንጉሥ ሚካኤልንና የቀድሞውን፡ ሼህ ዘኸርያን፡ የኋለኛውን፡ አለቃ ዘካርያስን (ንዋየ ክርስቶስን) የመሰሉትን፡ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን የወለደችውን፥ እንዲሁም፡ ራሳቸው እስላሞችና ሌሎቹም ሃይማኖቶች የሚያውቋትን፡ ያችን፡ እውነተኛዪቱን ኢትዮጵያ እንጂ፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው መንበሮች ላይ የተቀመጡትን ባለሥልጣኖች አለመኾኑን ማስታወቅ እወድዳለሁ።

ራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያን ነን" ብለው፡ በየልቦናቸው የሚያምኑትን እስላሞች ኹሉ፡ ስማቸው፡ ከላይ የተጠቀሱትን የአባቶቻችንን፡ መልካም አርአያነት በመከተል፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነታቸው ያበቁ ዘንድ፡ ምኞቴና ጸሎቴ ብቻ ሳይኾን፡ በማያቋርጥ፡ ጥልቅ የፍቅር ስሜት፡ ለእያንዳንዳቸው፡ በነፍስ ወከፍ የማቀርበው፡ ልባዊ ልመናዬም ነው።

ይህ ልመናዬ፡ ለእስላሞች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ብቻ ሳይኾን፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸውን፡ በተለያዩ ምክንያቶች ለውጠው፡ ወደሌሎች ባዕዳን ሃይማኖቶች ለገቡት ኹሉ ጭምር የቀረበ መኾኑን፡ አበክሬ ስገልጽ፡ ደስ ይለኛል።

ዛሬ፡ እስላሞችን፡ ከዚያ፡ ከመሪያቸው የአደራ ቃል የተፋቱ ሊያደርጋቸው የሚችል ኹናቴ፡ በኢትዮጵያ በመፈጠሩ፡ በአገሪቱ ላይ የሚኖሩ ወገኖቻቸው፡ የኢትዮጵያ፡ የሃይማኖት ምልክቶችና ቅርሶች ሳይቀሩ፡ ደብዛቸው እንዲጠፋ እስከማድረግ በሚደርስ፡ ልዩ ልዩ የተራቀቀ ስልትና ግዙፍ መንገድ በመጠቀም፡ ምናልባት የመንግሥታዊ ሥልጣንን ይዘው፡ አገሪቱን ለማስለም፡ ባሁኑ ጊዜ፡ ከፍተኛ ጥረትና ትግል እያካኼዱ መኾናቸውን የሚያመለክቱ ድርጊቶች፡ በገሃድ እየታዩ መኾናቸው፡ ከላይ ተገልጿል። ይኹን እንጂ፡ ይህ ኹናቴ ከመፈጠሩ በፊትም ቢኾን፡ ቀደም ብሎ ወደተጠቀሰው፡ ወደከፋው አዝማሚያ ያዘነበሉ መኾናቸውን የሚያመለክቱ ተመሳሳይ ድርጊቶችና እነዚያም፡ በበለጠ እየተጠናከሩ በመኼድ ላይ መኾናቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች መኖራቸውን፡ ከብዙዎቹ አንዱን ብቻ በምሳሌነትና በምስክርነት፡ እዚህ ላይ፡ በማቅረብ፡ ማስረዳት ይቻላል።

## የ"አኵስም ነገር" እስከመቼ?

እንደሚታወቀው፡ አኵስም፡ ለኢትዮጵያ፡ የማንነቷ፡ ማለትም፡ ለሕያው ታሪኳ፥ ለሃይማኖቷና ለሥርዓቷ መታወቂያ ኾና የቆመች፡ ቅድስት ከተማዋ መኾኗ፡ እንኳንስ፡ በቅርብ ያሉት እስላሞች ይቅሩና፡ የሩቆቹ ክርስቲያኖች፥ አይሁድና አረማውያንም ጭምር ያውቁታል። በዚህ መልክ የሚያውቋትም፡ "ጻሩ እሳት! መኻሉ ገነት!" ተብላ፡ እንደሃይማኖታዊው ሥርዓት፡ መስቀልና ወንጌል ዞሮባት፡ "ርእሰ አድባራት" ተብላ የተደበረች፥ "ርእሰ ገዳማት" ተብላም የተገደመች፥ "ኢየሩሳሌም"፡ ለአይሁድና ለክርስቲያኖች፥ "መካ መዲና"ም፡ ለእስላሞች እንደኾኑት ኹሉ፡ እርሷም፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ "ኢየሩሳሌማቸው"፥ "መካ መዲናቸው" መኾኗን ተገንዝበው ነው።

ታዲያ፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩት እስላሞች፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ ይህን የመሰለ ሃይማኖታዊ አቋም ባላት፥ እውቅናውም በተሰጣት፡ በአኩስም ከተማ ክልል ውስጥ፡ መስጊድ ለመሥራት "ይፈቀድልን!" እያሉ፡ የኢትዮጵያ ተፃራሪዎች የኾኑ መንግሥታት፡ ሥልጣን በያዙ ቁጥር፡ "አመቺ ዕድል አገኘን!" በማለት፡ እንዴት በየጊዜው፡ አቤቱታ ሲያቀርቡ ይኖራሉ? በዚህ ረገድ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሳይቀር፡ ይህን የመሰለውን ጥያቄ፡ ለመንግሥት አቅርበው፡ በተለይ፡ በአኩስሞች ከፍተኛ ሃይማኖታዊ ተጋድሎ፡ ጉዳዩ በሰፊው ከተመረመረ በኋላ፡ የአኩስም ጽዮን መብቷ እንደተጠበቀ እንዲቀጥልና እስላሞቹ ግን፡ ከክልሉ ውጪ፡ በአቅራቢያው በምትገኘው፡ በዚያው፡ በአኩስም አውራጃ፥ የማራይ ወረዳ ከተማ በኾነችው፡ በውቅሮ፡ መስጊዳቸውን እንዲሠሩ ተፈቅዶላቸው፡ ከቦታው ጋር የማይመጣጠን ከፍተኛ መስጊድ ሠርተው እየተገለገሉበት ይገኛሉ።

እንግዴህ፡ በደርግ ዘመን የተደረገውንና ዛሬም የሚደረገውን ትተን፡ ፋሺስት ጣልያን፡ ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ፡ የኾነውን፡ እስቲ እንመልከት! በዚያን ጊዜ፡ "እንግዴህ ኢትዮጵያ፡ ኢትዮጵያነቷ አበቃላት!" በሚል እምነት፡ እስላሞች፡ ወደፋሺስቱ ገዢ ዘንድ ኼደው፡ በኢትዮጵያ ሲፈጸምባቸው የቆየውን በደል በመዘርዘር፡ "'ኢትዮጵያውያን አይደላችሁም!' ተብለን፡ ይኸው፡ በአኩስም ውስጥ መስጊድ ከመሥራት ተከልክለን እንኖራለን። አሁን ገናናው የጣልያንን መንግሥት፡ ሥልጣኑን ከያዘልን፡ ለመሥራት ይፈቀድልን!" ብለው አመለከቱ። እርሱም፡ ዳኝነት ማየት፡ ግዳጁ ኾነና፡ በአኩስም ነዋሪዎች የኾኑትን፡ እውነተኞቹን ኢትዮጵያውያን ጠርቶ፡ በክስ መልክ የቀረበለትን፡ የእስላሞቹን አቤቱታ፡ ካሰማቸው በኋላ፡ ለዚህ ክስ፡ መልስ የሚኾናቸውን ቃል እንዲሰጡት ጠየቃቸው።

ኢትዮጵያውያኑም፡ ስለአኩስም ምንነት፡ ከላይ የተጠቀሰውን ማብራሪያ ከሰጡት በኋላ፡ "ስለዚህ፡ 'መካና መዲና'፡ ለእነርሱ ለእስላሞች፡ እንደኾኑት ኹሉ፡ 'አኩስም'ም፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ ቅድስት ከተማችን ናት! እኛስ፡ እነርሱን፡ በእንግድነት ተቀብለን፡ ስናስተናግዳቸው ኖረናል፤ በአኩስም ከተማችንም እንዳይኖሩ፡ እስካሁንም አልከለከልናቸውም፤ እነርሱ ግን፡ እኛን፡ እግራችንን እንኳ፡ ከመካና መዲና ከተሞቻቸው ለማስገባት አይፈቅዱልንም!" ብለው መለሱለት። ፋሺስቱም ገዢ፡ እስላሞቹን፡ "ታዲያስ! ይህ፡ እውነት ነወይ?" አላቸው። እነርሱም፡ "አዎን!" ብለው መለሱለት። የኢትዮጵያ ደመኛና ቀንደኛ ጠላት የተባለው፡ ፋሺስቱ ዳኛ፡ "እንግዲያውስ ሂዱ! እናንተ፡ እግራቸውን ከከተማችሁ እንዲያስገቡ ስትፈቅዱላቸው፡ በዚያን ጊዜ፡ እነርሱ ደግሞ፡ መስጊዳችሁን፡ በከተማቸው እንድትሠሩ ይፈቅዱላችኋል!" ብሎ፡ ኹለቱንም ወገኖች አሰናበታቸው።

እንግዴህ፡ በፋሺስትነቱ፡ ሃይማኖተ ቢስ አረመኔ፡ በጣልያንነቱም፡ ካቶሊካዊ ጠላት የኾነው፡ ያ፡ ባዕድ ገዢ እንኳ፡ በጠላቶቹ፡ ኢትዮጵያውያን ላይ እንዲያ ሲፈርድ፡ የሃይማኖት ሥርዓት አክባሪዎች የኾኑት እስላሞች ግን፡ ይህን የኢትዮጵያውያንን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ተቀብለው፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ሲያስተናግዷቸው ከኖሩት ኢትዮጵያውያን ጋር፡ በባለውለተኛነትና በሰላም ለመኖር ፈቃደኞች አለመኾናቸው ያስገርማል፡ ያስተዛዝባል፡ ያሳዝናልም። ይህ አድራጎት፡ "ወርቅ ባበደረ፡ ጠጠር! እህል ባበደረ፡ አፈር!" አያሰኝም?

## ኢትዮጵያ
## የዛሬዎቹን የትግራይ ልጆቿን የምትፋረድበት፡
## ሌላው አስተዛዛቢ ሙከራ።

ይህን የመሰለው ድርጊት ሳያንስ፡ እንደገና ታሪክን፡ ያውም፡ ሕያው የኾነውን፡ የኢትዮጵያውያንን የህልውና ዜና መዋዕል ለመለወጥ፡ የሚደረገው ሌላው ሙከራ ደግሞ፡ በበለጠ ያሳዝናል። ይህም ኹኔታ፡ አጼ ዮሐንስና እርሳቸውን የመሰሉ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ሰማዕታት፡ በምዕራባውያን ደመኞቻችን ግልጽ ድጋፍ ተደራጅተው፡ በየተራ የመጡባቸውን፡ የግብፅንና የደርቡሽን እስላማውያን ወራሪዎች፡ በሕይወታቸው መሥዋዕትነት ተቋቁመው፥ እንቅስቃሴያቸውን ገትተውና የዓላማቸውን ደብዛ ሳይቀር፡ ከኢትዮጵያ ምድር ደምስሰው ማጥፋታቸው እየታወቀ፡ የእነርሱን ደም ጠጥታ፡ በነፃነትና በቅድስና በለመለመችው በትግራይ ክፍለ ሀገር፡ እስላሞች፡ በቅርቡ፡ ባካኼዱት፡ አህጉር አቀፍ ስብሰባ ላይ፡ በይፋ ተከሥቶ ታይቷል። ይኸውም፡ በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ የሚኖሩ እስላሞች ተባብረው ባቀነባበሩት በዚሁ ስብሰባቸው፡ በኢትዮጵያ፡ "አሕመድ ነጋሽ" የተባለ ንጉሥ ነግሦ እንደነበረ ለማስመሰል፡ ያሳዩት ጥረት ነው። ይህ ድርጊት፡ ቀደም ብሎ፡ በተለያየ መንገድና ዘዴ፡ በምሥጢርና በገሃድ ሲካኼድ ከቆየው ሙከራና አሳሽ ዘመቻ ጋር ተያይዞ ሲታይ፡ አገራችን ኢትዮጵያ፡ ዛሬ የምትገኝበትን ኹኔታ፡ በቀጥታና በግልጽ አረጋግጦ የሚያሳይ ክሥተት መኾኑን፡ በቀላሉ መመልከት ይቻላል።

"ዕድሜ መስታዋት ነው! ብዙ ነገር ያሳያል!" ተብሏልና፥ "መቆየትም፡ ይህን ለማየት?" ኾኗልና፡ በዘመናችን እንደምንመለከተው፡ የእግዚአብሔር እውነት ተሽራ፥ ሐሰት የኾነው፡ የሰዎች እውነት እንዲሠለጥን ለማድረግ፡ "ኢትዮጵያውያን ነን" በሚሉ፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ወገኖች ዘንድ ሳይቀር፡ በያግጣጫውና በየመልኩ፡ ብርቱ ሙከራ እየተካኼደ በመኾኑ፡ ዛሬ፡ በአገራችን በሚኖሩ እስላሞች በኩል ሲፈጸም የሚታየው ድርጊት፡ ከሌሎቹ የተለየ ኾኖ፡ በምንም ዓይነት ሚዛናዊ አስተያየት፡ ሊያስደንቅ ከቶ አይችልም። ከላይ እንደተወሳው፡ በውለታ አመላለስ ረገድ ብቻ፡ እርግጥ ያስተዛዝባል።

ቀደም ብሎ የተወሳውን የተሳሳተ የታሪክ ትችት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ በተመሠረተው አማናዊ ድርጊት ለማስተካከል፡ ከዚህ የሚከተለውን አጭር ሐተታ መመልከቱ ሊበቃ ይችላል። የእስልምና ሃይማኖት መሥራች የኾነው መሐመድ፡ በዚሁ ሃይማኖቱ የተነሣ፡ የገዛ ወገኖቹ በሚያሳድዱት ጊዜ፡ "ወደአበሻ አገር ሽሹ! በዚያ፡ ፍርዱ ቅን የኾነና ሕዝቡን በሰላም የሚያስተዳድር፡ 'አል ነጋሽ' የሚባል ንጉሥ አለ!" በሚል ቃል፡ ከቤተሰቡና ከተከታዮቹ መካከል የተመረጡትን አባሎች፡ በዘመኑ፡ የኢትዮጵያ መሪ ወደነበረው፡ ወደአጼ አርማሕ ሰደዳቸው። በዚያም፡ ከንጉሡ፡ ከአጼ አርማሕ ጋር፡ ቤተ ምልክናው፥ ቤተ ክህነቱና ባጠቃላይ፡ ቤተ ሕዝቡ ጭምር፡ ስደተኞቹን፡ በመልካም ዓይን ተቀብለው፡ በማስተናገድ፥ አሳዳጆች ጠላቶቻቸውም፡ እነርሱን፡ ከኢትዮጵያ አስወጥተው ለመውሰድ፡ በልዩ ልዩ መንገድ ያደረጉትን ጥረት፡ በሃይማኖታዊ ምግባር በማክሸፍ፡ መሐመድ፡ ባገሩ፡ በመካ፡ በድል አድራጊነት እስከተደላደለ ድረስ፡ በኢትዮጵያ፡ በጥገኝነት እንዲኖሩ አደረጉ።

በመጨረሻም፡ በራሳቸው በስደተኞቹ ፍላጎት፡ በሚያስደስት አሸኛኘት፡ ወደአገራቸው መልሰው ላኳቸው።

አጼ አርማሕ ባረፈ ጊዜ፡ መሓመድና ተከታዮቹ፡ ስለውለታው፡ ሙሉ የኃዘን ጸሎት እንዳደረጉለት፥ የኋላ ኋላም፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች፡ ያን፡ የአጼውን የቸርነት ሥራ በማዘከር፡ በየጊዜው፡ በጸሎት እንደሚያስታውሱት ይነገራል። ይህ እውነታ፡ በታሪክ የተረጋገጠ ሲኾን፡ ራሱም፡ መሓመድ፡ ለዚያ፡ ለአጼውና ለሕዝቡ በጎ ምግባር፡ ባለውለተኛነቱን ለማሳየት፡ "አበሾችን (ኢትዮጵያውያንን) እንዳትነኩ!" ባለው የኑዛዜ ቃሉ አጽንቶታል። መሓመድ፡ አጼ አርማሕን፡ "አል ነጋሽ" ያለው፡ "ነጋሢ" ወይም "ንጉሥ" የሚለው፡ ኢትዮጵያኛ የማዕርግ ቃል፡ በዚያ ዘመን የነበረው፡ የአጼው መጠሪያ ስም መስሎት፡ በስሕተት እንደተጠቀመበት ግልጽ ነው። እንዲያውም፡ በዓረብኛው ፊደል፡ "ገ" የሚል ሆሄና ድምፅ ስለሌለ፡ "ናጃሽ" ብለውታል። የዛሬዎቹ እስላሞች፡ ለዚያ ንጉሥ፡ "አሕመድ" የሚለውን ስም፡ ከየት አምጥተው እንደሰጡት ግን ያስደንቃል፤ ካለማወቅ የመነጨ፥ ወይም፡ በ፲፮ኛው ምዕት ዓመት፡ በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን በነበረው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ ላይ፡ የተወሰነውን መለኮታዊ ቅጣት እንዲፈጽም፡ ተልኮ ከነበረው፡ "አሕመድ ግራኝ" ከተባለው፡ የእስላም ወራሪ ስም ጋር በማያያዝ፡ ሐሰት የኾነውን ይህን ነገር፡ እውነት ለማስመሰል፥ ወይም፡ ለታሰበው የጠላትነት ዓላማ፡ ኾን ተብሎ የተፈለሰፈ ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው ከቶ አይቻልም።

በኢትዮጵያ የሚኖሩ የዛሬዎቹ እስላሞች፡ ከሃይማኖት መሪያቸው የተጻፈላቸውን፡ ይህን ኹሉ እውነት እያወቁ፡ የሃይማኖት መሥራቻቸውን ቃል በመተላለፍ፡ ዓለም የተቀበለውን፡ ይህን ሐቅ፡ ለማስተባበል ከሞከሩ፡ የበሉበትን ወጭት እንደመስበር፥ ወይም የሚያጎርሱ ጣቶችን፡ አውቆ እንደመንከስ ያስገምታቸዋል፤ የራሳቸውንም ሃይማኖት እንደመካድ ያስቆጥራቸዋል። በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፡ የሚፈራውን መለኮታዊ ቅጣት ለመፈጸም፡ ታዝዘው ከኾነም፡ ዓላማቸው ይሳካላቸው ይኾናል። ነገር ግን፡ ጊዜያዊ ተልእኳቸውን ካደረሱ በኋላ፡ ለመጨረሻ ጊዜ፡ ፍርዳቸውን፡ ከኢትዮጵያ አምላክ፡ በተራቸው የሚቀበሉ መኾናቸውን በቅድሚያ ሊያውቁት ያስፈልጋቸዋል።

ባሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ በቤተ ሕዝቡም፥ በቤተ ክህነቱም ኾነ በቤተ ምልክናው መንበሮች ላይ የተቀመጡት፡ የዚህ ትውልድ መሪዎች፡ ይህን፡ እጅግ አሳሳቢ የኾነውን ሃይማኖታዊ ጉዳይ በሚመለከት፡ የያዙት የክህደት አቋም፡ የታወቀ ስለኾነ፡ ከዚህ አመራራቸው፡ በንስሐ ካልተመለሱ በቀር፡ እነርሱም፡ ዕድላቸው፡ ከእነርሱ አስቀድመው ከነበሩት፡ የተለየ ሊኾን እንደማይችል፡ ሊገነዘቡት ይገባል።

ስለዚህ፡ የእግዚአብሔርን እውነት መሠረት በማድረግ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች፡ ያን፡ የሃይማኖት መሪያቸውን፡ የመሓመድን የአደራ ቃል እንዳይዘነጉት ለማስታወስ ስል፡ እኔም፡ ከዚህ በላይ፡ የሠፈረውን ሐተታ ያቀረብሁት፡ በዚህ ረገድ፡ የተቀበልኩት ሃይማኖታዊ ተልእኮዬ አስገድዶኝ መኾኑን ልገልጽ እወድዳለሁ።

## ለኢትዮጵያውያን: ሃይማኖታዊ ማስጠንቀቂያ!!!

በዚህ ኹሉ ኹኔታ: የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ የኾኑት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: የመጨረሻውን የቅጣት ፍርድ ለመቀበል የሚዘጋጁበት ጊዜ መድረሱን ሳይገነዘቡት የሚቀር አይመስለኝም:: ምክንያቱም: የኢትዮጵያ መለኮታዊት መንግሥት አካሎች በኾኑት: በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው በኩል: በቅዱሱ ኪዳን ላይ በኅብረት የተፈጸመው የክህደትና የዓመፅ ኃጢአት: እየተባባሰ ከመኼድ በቀር: በዚሁ ኃጢአት መነሻነት: እነሆ: ለሃያ ሰባት ዓመታት እየወረደ ያለውን መርገምና ያለማቋረጥ የቀጠለውን የመቅሠፍት ቅጣት: በአምላካዊው ምሕረት እንዲመለስ ለማድረግ የሚያስችለው፥ ያ: እስካሁን ከትውልዱ ሲጠበቅ የቆየው የንስሓ ምግባር: በምንም መልክ: ፍንጭ አለማሳየቱ ነው::

በቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊ ደም የታተመችው: የዚች የኢትዮጵያ መንግሥት መሪ: ኢየሱስ ክርስቶስ: የቅርቦቹን: የአዲስ ኪዳኑን የመከራ ዘመናት ለመጥቀስ ያህል: በጉዲት፥ በአሕመድ ግራኝና በፋሺስት ሙሶሎኒ መሣሪያነት: በዕድሜ በተራራቁ: የሕዝቧ ትውልዶች ላይ: ያን የመሰለ ቅጣትና ጥፋት እንዲወርድ የፈቀደው ለምን ይመስለናል? በእነዚያ ዘመናት የነበሩት ትውልዶች: እያንዳንዳቸው: ከፈጣሪያቸው ጋር ያደረጉትን የአምልኮ ቃል ኪዳን አፍርሰው: በጌታ ቃል: *"ትውልድ ዕሉት፥ ወዐማፂት፥ ወዘማዊት!": ማለትም: "ከሃዲ፥ ዓመፀኛና አመንዝራ ትውልድ!"* የተባለችውን ኾነው ስለተገኙ አልነበረምን? ዛሬስ: እኛ: ራሳችን: ምስክሮች ኾነን ለቆምንበት፥ በንስሓም ለመመለስ "እምቢ!" ላለ: ለዚህ: ትውልድ ሌላ: ምን ዕድል ይጠብቀዋል ተብሎ ይታሰባል? የዚህ ትውልድ ጽዋማ: ይኸው እየተጠናከረ: በጥድፊያ ሲራመድ የሚታየው: ተሰንግሎ: እየተምዘገዘገ ያለው: የሠይፈ ነበልባሉ ኃይል: በጥብጦ ሊሰጠው ያዘጋጀለትን: የኮሶ ድፍድፍ: ቁቅ እያለው እንዲጠጣ ከሚገደድበት ደረጃ ሊያደርሰው የተቃረበ መኾኑን: ኹሉም በግልጽ ይመለከተዋል:: ከዚህ ከሚያስፈራ: የቅጣት ሠይፍ መዳን የሚቻለው: በንስሓ ብቻ ስለኾነ: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ጸንተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ኹሉ: የሱባዔ ይዞታቸውን: በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት ምግባራት: በያሉበት ሊቀጥሉበት ይገባል::

## ኢትዮጵያ: ስለቤተ ክህነቷ ጥቃት ስትፋረድ!

አጼ ኃይለ ሥላሴ: ቀደም ብለው: በምዕራባውያን ባለገንዘቦችና የሃይማኖት አማካሪዎች የተፅዕኖ ኃይል፥ ኋላ ደግሞ: በምሥራቃውያን ባለጋሮቾች (communists) እና "እግዚአብሔር-አልባ ነን" በሚሉ ጠበብት የምክር ግፊት፥ ግን: ኹልጊዜም: የቅዱሱን ኪዳን ግዴታዎቻቸውን በመተላለፍ: የእግዚአብሔር ቁኾነው ይልቅ: ለሰብአዊው ቃል ኪዳን: ቅድሚያንና ብልጫን እየሰጡ: የባዕዳንን የሥነ መንግሥት ፍልስፍና እንደተቀበሉና በተግባር ላይ እንዳዋሉ: እስካሁን በተመለከትነው ተረድተናል::

ይኹን እንጂ፡ “የእግዚአብሔር ሹም” እና ዋና አገልጋዩ እንደመኾናቸው መጠን፡ በቃል ኪዳን የተሣሠሩትን፡ ቅዱሱን ኪዳን በመግፀን፡ ሥርዓቶቹ በሥራ ላይ ውለው፡ ፍሬያማ ይኾኑ ዘንድ፡ ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው ማቅረብ፡ ብቸኛ ግዴታቸውና የመጀመሪያ ተግባራቸው ሊኾን ይገባ ነበር።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ እንዲህ አድርገው፡ ለካቶሊክ ሃይማኖትና ለተከፋፈሉት አያሌ የክርስትና እምነት ድርጅቶች፡ ወደኢትዮጵያ መግቢያ የሚኾናቸውን፡ ጥርጊያ መንገድ ለመክፈት ሲሉ፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓት ይልቅ፡ ልቅ አኗኗርን የሚያበረታታውን፡ የምዕራባውያንን የሥነ መንግሥት ፍልስፍና ማጽደቃቸው፥ አከታትለውም፡ በደረጃና በፈረቃ፡ ለምሥራቁና ለምዕራቡ ልዕለ ኃያላን መንግሥታት ፈቃድና ፍላጎት፡ በጭፍን በመንበርከክ፥ ለቅዱሱ ኪዳን የገቡትንም ግዴታ ጨርሰው በመተው፡ ፍጹም እምነታቸውንና ሙሉ ትውክልታቸውን፡ በየተራ፡ በኹለቱ ኃያላን ወገኖች ላይ መጣላቸው፡ እነሆ፥ የኢትዮጵያንና የቃል ኪዳን ሕዝቧን፡ የመጨረሻ ዕድል፡ በአንድነት የሚወስን፡ ዓቢዩ ቁም ነገር ኾነ! እርሱም፡ ዛሬ እየተጐነጩት ያለው፡ በመከራ ኮሶ የተሞላው፡ መራራው ጽዋ ነው!

ይህ፡ ጽኑ የኾነ፡ የመጨረሻ እርምጃ፡ ማለትም፡ በእግዚአብሔር፡ አንዲት የኾነችውን አገር፥ ወይም አንድ የኾነውን ሕዝብ፡ በምዕራባውያን የፍልስፍና ፈሊጥ፡ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት ብሎ፡ ከኹለት የመክፈሉ ውሳኔ፡ በኢትዮጵያ፡ ገቢራዊ መኾኑ፡ የእግዚአብሔር የዘውድ መንግሥት አገር በኾነችው፡ በኢትዮጵያ አንድነት ተመሥርቶና የቅዱሱ ኪዳን መንግሥታዊ አካላት በኾኑት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ሦስትነት ጸንቶ የኖረውን ሃይማኖታዊ ሥርዓት፡ ከሥሩ መንግሎ ለመጣል፡ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ዕቅድና የተካኼደ ከባድ ሙከራ እንደነበረ፡ ያለውልውል ያረጋግጣል።

በዚያ ውሳኔ መሠረት፡ ቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት፡ በሥውር የመለየቱንና በዚያ ቦታ፡ አዲስ መጤዎቹን፡ የባዕዳን ሥነ መንግሥታውያን ርእዮተ ዓለማት፡ በዘዴ የመተካቱን ይህን ተግባር ለመቀጠል ሲባል፡ በርከት ያሉ፡ የተራቀቁ ዕቅዶች፡ በጥንቃቄ እየተዘጋጁ፡ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደረገ። ለዚህም ተግባር መከናወን፡ ፍጹም አመቺ ኹኔታን ለመፍጠርና ኺደቱን በበለጠ ለማፋጠን ይቻል ዘንድ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የትምህርት ምልክናውን (ministere ሚኒስቴር) ሥልጣን፡ ማለትም፡ የትምህርት ምሉክነቱን (ministre ሚኒስትርነቱን)፡ ራሳቸው ይዘው፡ አመራሩን፡ በግል አካኺደውታል። በዚህ አሠራር፡ ከተፈጸሙትና በይፋ ከታወቁት ተግባራት መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

፩. ጸንቶ ከኖረው፡ ከቅዱሱ ኪዳን የመንግሥትና የትምህርት ሥርዓቶች፡ የምዕራባውያን ወደኾኑት፡ የተደረገው፡ አጠቃላዩ ሥር ነቀል ለውጥ፡ በሦስት መንገዶች ተካኺዶ ተከናውኗል።

የመጀመሪያው መንገድ፡ ቤተ ክህነት፡ ማለትም፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ የአገሪቱን መንግሥት በማካኼድና ሕዝቡን በማስተማር ረገድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት፡ ይዛው ከኖረችው፡ ከሲሰው የኃላፊነት ድርሻዋና የሥልጣን ተካፋይነቷ፡ በይፋና በገቢር እንድትገለል በማድረግ፤

ኹለተኛውም መንገድ: ጃፓንና በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ: ተመሳሳይ አገሮች እንዳደረጉት ኹሉ: ለቤተ ክህነትም: ተገቢው ድጋፍና አስፈላጊው እርዳታ ተበርክቶላት: ያላት: በቂ የሰው ኃይልና የተከማቸ የእውቀት ሀብት፥ በሕዝብም ዘንድ የመደመጥ ጸጋ: በዘመናዊው መልክ: በበለጠ ዱብሮ: ብቅዓትን ካገኘ በኋላ: ይህንኑ: በቀላሉ: ለኢትዮጵያ መሻሻልና ዕድገት ማዋል ሲቻል: ነገር ግን: በዚህ ፋንታ: ወይም ከዚህ ይልቅ: ባለመታደል: ያ ኹሉ ኃይል፥ ሀብትና ጸጋ: ኸን ተብሎ: እየተበላሸና እየፈራረሰ እንዲኼድ፥ በመጨረሻም: ከመጥፋት እንዲደርስ: በዝምታ በመመልከት!

ሦስተኛው መንገድ ደግሞ: ወጣቱ የኢትዮጵያ ትውልድ: የባዕዳንን: ርእዮተ ዓለማትና ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች: በቀላሉ ለመቀበልና ለማመን ይችል ዘንድ: አእምሮውን: በምዕራባውያኑ ሥርዓተ ትምህርት: ፈጽሞ አከላሽቶ፥ አለስልሶና ኮትኩቶ ለማመቻቸት: የቤተ ክህነት: የሃይማኖት መምህራንን: ከነትምህርት ገበታቸው: ቀስ በቀስ: ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሳይቀር በማስወገድ!

፪. ቤተ ክህነት: ማለትም: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን: በዚህ መልክና ይዞታ: የቅዱሱ ኪዳን ኃላፊነቶቿን፥ ሥልጣኗንና መብቶቿን ስለተገፈፈች፥ ከዚህ የተነሣም: ጉልበት አንሷትና ለመራመድ አቅቷት: ተሽመድምዳና ለብቻዋ ተጥላ ወድቃ፥ ለሙስናና ከጠላቶቿ እግር ሥር: በምጽዋት ልመና እስከመውደቅ በሚያደርሳት ጕሥቍልና: ለማናቸውም ዓይነት አሳዛኝ ፍጻሜ ስለተጋለጠች፥ ይልቁንም: ከላይ እንደተብራራው: ባላጋራዎቿን ለመቋቋም ትችል ዘንድ: ተገቢውና አስፈላጊው ተመጣጣኝ ዝግጅት ስላልተደረገላት: እነሆ: የምዕራቡና የምሥራቁ ርእዮተ ዓለማት: ከተፅዕኖ ኃይላቸውና ከተለያዩ ሃይማኖቶቻቸው ጋር: በዚች የቅዱሱ ኪዳን አገርና ሕዝቧ ላይ: በታወቀና በተፈቀደ አሠራር: ያልተገደበና ያልተወሰነ: የሰለባ ወረራቸውንና ዘመቻቸውን ሊያካኺዱ ቻሉ!

ይህ: ከቤተ ክህነት ዓቅም በላይ የኾነው: ያገር ውስጥ ደምሳሽ እርምጃ: ከባሕር ማዶ: ይደርሰው በነበረው ሰፊ ድጋፍና የተባበረ ጥረት: በከፍተኛ ይዞታ ተጠናክሮ: ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በቃ! ድጋፉና ጥረቱም የተገኘው: በልዩ ልዩ የኃያላን መንግሥታት: የስለላ መሥሪያ ቤቶች፥ በማስታወቂያ ወኪሎች፥ በሃይማኖት ሰባክያን ሠፈሮችና የዓለም ቤተ ንዋይን (World Bank)፥ የተባበሩት መንግሥታትንና ቅርንጫፎቻቸውን በመሰሉት: አህጉር አቀፍ ድርጅቶች፥ በሌሎች የክፍለ ዓለምና የክፍለ አህጉር አካላት፥ በባዕዳን መንግሥታት እንደራሴ ጽሕፈት ቤቶች፥ በታላላቅ የገንዘብና የንግድ ማኅበሮች፥ እንዲሁም: በትምህርት ተቋማት አማካይነትና መሣሪያነት: እነዚህ ኹሉ: እያንዳንዳቸው: በብዛት: ካበረከቱት: የነጻ ትምህርት እርዳታቸው ጋር ተደማምሮ: በተናጠልና በጋራ፥ በገፍ: ይቀርብ ከነበረውና እየቀረበ ካለው የእርዳታ ክምችት ነው::

፫. ኢትዮጵያን: እንዲህ: ኹሉን ያጣችና ዕርቃኗን የቀረች፥ የራሷ የኾኑትን ጉዳዮችም እንኳ አስተናግዳ ማከናወን እንደማትችል: እንደደካማና ችጋረኛ አገር በመመልከት፥ ይህም ማለት: ቅዱሱ ኪዳን: የተሠረዘ ሕግና የተሻረ ሥርዓት እንደኾነ በማስመሰል፥ ወይም: እንደሌለ በመቍጠር፥ ወይም: እንደማይጠቅም አሮጌ ዕቃ ወዲያ በመወርወር: የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ: ከምሥራቁና ከምዕራቡ: ኹለት ማዕዘናት: ለመጡበት ኃይላት: በፍጹም ኹለንተናው:እንዲንበረከክ ተገደደ::

የተንበረከከውም፡ መጀመሪያ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ገና ከአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ አንሥቶ፡ ለምዕራቡ ጌትነት፥ ኋላ፡ ወደመጨረሻው ዘመናቸው ደግሞ፡ ጥርጊያው፡ እንዲያ፡ በተዘጋጀለት መንገድ፡ ሰተት ብሎ ለገባው ለምሥራቁ ተፅዕኖ ነበር፡፡ ይህ፡ እጅግ ያየለና የሰፈነ ኹኔታ፡ በግለሰብም ኾነ፡ በብሔራዊ ደረጃ፡ በአጠቃላይ፡ በኹሉም አካባቢ ሠርጎ በመግባቱ፡ ይኸው ኹኔታ፡ በኹለቱም ደረጃዎች ያሉት ግለሰቦችና አገሪቱ፡ ለአጠቃላዩ ህልውናቸው የሚደገፉበት፥ ማንነታቸውም፡ ወደዚሁ፡ ወደመጣው ገጸ ባሕርይ መለወጡን፡ ለመላው ዓለም ያሳውቁበት እስከመኾን ደረሰ!

## ኢትዮጵያ፡ ስለበጌምድርና ጎጃም፡ ስትፋረድ!

በለውጡ ዋዜማ፡ እኔ፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ስለነበርሁ፡ በዚህ ረገድ፡ ይካኼድ ስለነበረው ምሥጢራዊ ግዝገዛ፡ ከማውቃቸው ድርጊቶች መካከል፡ አንዳንዶቹን ለማስረጃነት ላቀርባቸው እወድዳለሁ፡፡

በጌምድርና ጎጃም፡ ለኢትዮጵያ፡ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር፥ የትምህርትና የእውቀት፥ የጥበብና የኪነት መሠረትና ምንጭ በመኾን፡ በተለይ ለፍትሕ፥ ለመንፈሳዊውና ለክህነታዊዉ አገልግሎት፡ አዕማድና የአከርካሪ አጥንት የኾኑት ካህናት፥ መምህራንና ሊቃውንት፡ ያለማቋረጥ የሚፈልቁባቸው ክፍላተ ሀገር መኾናቸው፡ በይፋ የታወቀ ነው፡፡ ነገር ግን፡ እነዚህ፡ ኹለት ክፍላተ ሀገር፡ በቤተ ክህነት አስተዳደራቸው በኩል፡ ከሌሎቹ፡ ከቀሩቱ ክፍላተ ሀገር ኹሉ ተለይተውና ተነጥለው፡ ከዚያ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ ምንም ዓይነት የድጋፍ አስተያየት የማይደረግላቸውና የገቢ ምንጭ የሌላቸው ነበሩ፡፡ ለዚህ አሳዛኝ ኹኔታቸው፡ "መነሻ ነው" ተብሎ፡ ይሰጥ የነበረው ምክንያት፡ እነዚህ ኹለት ክፍላተ ሀገር፡ ወራሪው ፋሺስት ጣልያን፡ ከኢትዮጵያ ምድር ከተባረረበት፡ ከ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ወዲህ፡ ስለመሬት ግብር፡ አዲስ ሥርዓት ወጥቶ፡ "የእያንዳንዱ ሰው ይዞታ፡ እየተለካ፡ በዚያ ልክ፡ ግብሩን፥ አሥራቱን፡ ለመንግሥት፡ በገንዘብ ይክፈል? ወይስ በጥንቱ ሥርዓት፡ (በአገልግሎትና በምርት፡ ለየባለመብቱ በመክፈል) መቀጠል ይሻላችኋል?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ፡ ጉዳዩ፡ የአገርን፡ መሠረታዊ የአስተዳደር አቋም የሚነካ ስለኾነ፡ በዝርዝር ተጠንቶና እነርሱም በትክክል ተረድተውት፡ በሥራ ላይ ሊውል የሚገባው፡ "ከዚያ በኋላ ቢኾን ይሻላል" የሚል መልስ በመስጠታቸው፡ እንግዲያው፡ "እስከዚያው፡ በጥንቱ ሥርዓት ቀጥሉ!" በመባላቸው እንደኾነ ይነገራል፡፡

ኹለቱን ክፍላተ ሀገር በሚመለከት የነበረው ውስብስብ ችግር የተፈጠረው፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸውና ወደፊትም እንደሚብራራው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ የአስተዳደር አቋምና የአሠራር ሥርዓት በመቃወሱ በመኾኑ፡ ራሱን፡ ከዚህ አቋምና ሥርዓት ገንጥሎ፡ የባዕዳንን አዲስ አቋምና ሥርዓት ሊመሠርት፡ በዚያን ጊዜ፡ ቆርጦ የተነሣው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ ለችግሩ፡ ተገቢ የኾነውን መፍትሔ ፈልጎ ማግኘት፥ ያንንም፡ በሥራ ላይ አውሎ ለፍሬ ማብቃት ይቻለውም፥ ይገባውም ነበር፡፡

ዳሩ ግን: ያን ግዳጁን በመፈጸም ፋንታ: እንዲወገድ የተፈለገ: አንድ ያረጀ ቤት: እየፈራረሰ መኼዱ እየታየ: እስኪወድቅ ድረስ: ዝም ተብሎ እንደሚጠበቅ ኹሉ: ለተፈለገው የኢትዮጵያ ውድቀት: መነሻው: የእነዚህ ኹለት ክፍላተ ሀገር መሠረታዊ አቋም መፈራረስ በመኾኑ: ለእርሱ: በሥጋዊ ዓይኖቹ ይከታተለው እንደነበረው: መሠረታቸው እየተናደ፥ ምንጫቸውም: እየደረቀ መኼዱን: ራሱ: እንደተውኔት: በምትሐት እያየ፥ ከአስተዋይ ተመልካቾች የሚቀርብለትንም ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ ገሸሽ እያደረገ: ዝም ብሎ መመልከቱን ቀጠለ! ይልቁንም: የካህናቱ፥ የመምህራኑና የሊቃውንቱ ተጠሪዎች የኾኑት አረጋውያን: አዲስ አበባ ድረስ ለአቤቱታ እየተመላለሱና አድማጭ በማጣት እየተጉላሉ ሲያመለክቱ ሣሉ: ለእኒያ ባለጉዳዮች: ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንኳ: ደንታ የሌለው መኾኑን በገሃድ እያሳየ: የመጨረሻውን የቤተ ክህነትን ጠቅላላ ውድቀት ይጠባበቅ ነበር::

## በዝምታ የሚፈጸም:
## የጳጳሳት ኀላፊነት::

ይህ ኹሉ ሲኾን: ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳሳት መንፈሳዊ አገዛዝ ነጻ በመውጣት: በ፲፱፻፵ዎቹ ዓመታተ ምሕረትና በተለይም: የሊቀ ጳጳሳትነቱን ሙሉ ሥልጣን: ኢትዮጵያ ከተረከበችበት: ከ፲፱፻፶፩ ዓመተ ምሕረት ወዲህ: በኹለቱ ክፍላተ ሀገር: ለቤተ ክህነት ዋና ተጠሪነት የተሾሙት ጳጳሳት: ከመንግሥት እንዲያገኙ የተመደበላቸውን: የየራሳቸውን የግል ደመወዝና አበል: በየወሩ ከመቀበል በቀር: እያንዳንዳቸው: በየሀገረ ስብከታቸው ስላለው ጽኑ ችግር: ምን እንዳደረጉና እንዳላደረጉ: ከላይ እንደተጠቀሰው: ባለማቋረጥ: ወደአዲስ አበባ የሚጐርፈው የደጀጠኚው ብዛትና ድካም ይመሰክራል::

ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የኾነው: የቤተ ክህነቱ ተጠሪዎች: ከእጨጌው ጀምሮ: "ሲኖዶስ" የሚባለው: የጳጳሳት ጉባዔ: እንደዛሬዎቹ ኹሉ: ታዛዥነታቸው: ያው: ለሾማቸው የሰዎች መንግሥት በመኾኑ: ምንም የሚሉትና ምንም የሚያደርጉት ነገር አልነበረም:: በመንግሥቱ ድርጊት የተስማሙ ይመስል: እነርሱም: ዝም ብለው ይመለከቱ ነበር:: ተናግረውም ከኾነ: በተግባር የማይገለጽ ንግግር: እንደዝምታና ፋይዳ እንደሌለው የሚቆጠር ነው:: ፋይዳ ይኖረው የነበረው: ለጉዳዩ: አጥጋቢ የኾነ መልስ ወይም ለችግሩ: መፍትሔን የሚያስገኝ አንዳች ውጤት ተገኝቶበት ቢኾን ነበር::

ነገር ግን: ያ: ሊኾን ስላልቻለ: እጨጌውና ጳጳሳቱ: ለአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት: ሊሉትና ከዚያ ጋር አያይዘው: ሊያደርጉት ይገባ የነበረው: እንዲህ የሚለው ቃልና ድርጊት ይመስለኛል:- "የአገርን ውድቀት የሚያስከትለውን፥ ይህን በመሰለ ረቂቅ መንገድ ተወጥኖና በግዙፍ መልኩም: እንዲህ ጎልቶ: በኢትዮጵያ ላይ የሚካኼደውን የባዕዳን ዘመቻ: እኛ መንፈሳውያኑ: ባለብን ኀላፊነት: እንደእናንተ: እንደሥጋውያኑ ዝም ብለን ተቀምጠን አንመለከትም! በሤራውም፥ በጥፋቱም ተባባሪዎች አንኾንም! ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስና አገራችን ኢትዮጵያ የኾነችው: ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም: ስለዚህ ጉዳይ: ለሚያቀርቡልን ጥያቄ: ተገቢውን ምላሽ መስጠት አለብን!"

ጳጳሳቱ፡ ይህን ቃል፡ በመጀመሪያ፡ ለቤተ ምልክናው ባለሥልጣኖች፥ በመጨረሻም፡ ለአጼው ተናግረው፡ ወይም በጽሑፈት አመልክተው፡ ችግሩ፡ ሊወገድ፡ ወይም ሊሻሻል ካልተቻለ፡ ነገሩን፡ ለመላው ቤተ ሕዝብ አስታውቀው፡ ቤተ ሕዝቡ የሚለውን መስማት፥ ከዚያም፡ ይህን ማድረግ ካልቻሉ፡ ሥልጣናቸውን፡ ለአጼው መንግሥት አስረክበው፡ ወደየገዳማቸው መመለስ ይገባቸው ነበር፤ በ፲፱፻፵፫ ዓ. ም.፡ በብፁዕ እጨጌ ባስልዮስ እጅ፡ የጵጵስናውን ሹመት ተቀብለው የነበሩት፡ ብፁዕ አባ ታዴዎስ እንዳደረጉት ማለት ነው፡፡ ይህም አልኾነላቸውም፡፡

## የጽሑፈት ቤት እንኳ አለመኖር፡፡

በጌምድርንና ጎጃምን በሚመለከት፡ ሌላው የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ፡ እኔ፡ የቤተ ክህነቱን ሥራ፡ በኃላፊነት እስከተረከብኩበት፡ እስከግንቦት ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ድረስ፡ የቀሩት፡ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር በሙሉ፡ እስከወረዳ ድረስ፡ የሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት ሲኖራቸው፡ እነዚህ ክፍላተ ሀገር ብቻ፡ በጎንደርና በደብረ ማርቆስ ከተሞቻቸው፡ በየግል ቤታቸው እንዲኖሩ ከተሾሙት፡ ከሊቃነ ጳጳሳቱ በቀር፡ የወረዳ ቀርቶ፡ በክፍላተ ሀገር ደረጃ እንኳ፡ የየራሳቸው የኾነ፡ የቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤትና ሠራተኞች ያልነበሩዋቸው መኾኑ ነው፡፡ ለነገሩማ፡ ሰዎቹ ራሳቸው፡ የሚበሉት ሳይኖር፡ እንዴት መሥሪያ ቤት ሊኖር ይችላል?

ስለዚህ፡ ለዚህ አገልግሎት የሚመደብ የተለየ ገንዘብ ባይኖርም፡ ወደፊት፡ የሰበካ ጉባዔ ተቋቁሞ፡ ራሳቸውን የሚችሉበት መንገድ እስኪዘጋጅ ድረስ፡ ጠቅላይ ቤተ ክህነት፡ ካለው አጠቃላይ የገቢ አርእስት ላይ፡ ተቀናንሶ በሚገኝ አነስተኛ ወጪ፡ "ለኹለቱም ክፍላተ ሀገር፡ ለእያንዳንዳቸው፡ የየራሳቸው ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት፡ ሊኖራቸው ይገባል!" በማለት፡ ጽሕፈት ቤቶቹ፡ በዝቅተኛ መጠን፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፱፻፷፬-፷፭ ዓ. ም. እንዲቋቋሙላቸው ተደረገ፡፡

ከላይ፡ ቀደም ብሎ በተገለጸው ይዘትና ሂደት፡ በረቂቁ የባዕዳን መጋዝ ስትገዘገዝ የቆየችው፡ ያች፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ፈራርሳ የምትወድቅበትን ጊዜ፡ ዝም ብሎ፡ በናፍቆትና በንቃት ይጠባበቅ የነበረው፡ ያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ በመጨረሻ፡ ያ፡ መለኮታዊው የቅጣት ቀን ደረሰበትና፡ በቆፈረው ጉድጓድ ራሱ ገብቶበት፡ ተንኰታኰተ! የእኚያ፡ የኹለት ክፍላተ ሀገር ጥቂቶችም፡ የእግዚአብሔር ዳኝነት የፈጸመችውን ተአምራዊ ኃይል፡ "ጉድ!" እያሉ ተመለከቱ! "ጌታ ሆይ! ለካ፡ አለህና!" ብለውም አመሰገኑት፡፡

## የማይጣጣም ድርጊት፡፡

እጅግ የሚያስገርመው፡ ደርግ፡ ያንን፡ "በእግዚአብሔር አምናለሁ" ይል የነበረውን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ደረማምሶ፡ "እግዚአብሔር የለም" የሚል አገዛዙን መተካቱ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" በሚል ማዕርግ ተቀብቶ፡ የአሸናፊውን የይሁዳ አንበሳ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ዘውድ በተጠሪነት የተቀዳጀውና በዙፋኑ የተቀመጠው የ"አጼ"ው መንግሥት፡ ለእነዚያ ኹለት ክፍላተ ሀገር ያልፈጸመውን ተገቢ ግዳጅን፡ ፈጽሞ መገኘቱ ጭምር ነው እንጂ፡፡

ይኸውም: ፋሺስት ጣልያን: ከኢትዮጵያ ተባርሮ ወደሥልጣን ከተመለሰበት ዘመን ጀምሮ: የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የነፈጋቸውን አበል: ያ: ሃይማኖተ ቢስ የኾነው ደርግ: በመደበኛ መልክ: በያመቱ: ከመንግሥቱ ግምጃ ቤት: እንዲከፈላቸው ማድረጉ ነው።

በመንፈስና በእውነት መመለክንና መገልገልን የሚወድደው እግዚአብሔር: "አምላከ ነዳያን": ማለትም: "የድኾች አምላክ" ነውና: ስለእኒህ ጥቁምቹና እነርሱን ስለመሰሉት ድኾቹ ሲል: በኢትዮጵያ የመሠረታት መንግሥቱ: መንፈሳዊ ህልውናዋን: በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: የሰበካ ጉባዔ አማካይነት: እንድትቀጥል: እነሆ ፈቃዱ ኾነ!

## ኢትዮጵያ:
## ስለቤተ ክህነቷ ግብርና ቀረጥ ከፋይነት
## ስትፋረድ!

ቤተ ክህነት: የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው በኢትዮጵያ አቋም ውስጥ: ከቀሩቱ: ከኹለቱ: ማለትም: ከቤተ ሕዝቡና ከቤተ ምልክናው ጋር: በማናቸውም ይዞታ፥ አገልግሎትና ጸጋ ኹሉ: ሲሶ ድርሻ ያላት: ባለመብት መኾኗ: አግባብነት ባላቸው: በዚህ መጽሐፍ ምዕራፎች ተገልጿል። ይኹን እንጂ: ይህን: ከፈጣሪዋ የተሰጣትን: ባሕርያዊ መብት እንድታጣ የሚያደርጓት: ደባዎች: በምሥጢር ብቻ ሳይኾን: በይፋም ሲካኼዱባት ኖረዋል፤ አሁንም እየተካኼዱባት መኾናቸው: በገሃድ እየታየ ነው።

## የባለ"ሲሶዋ መንግሥት"
## የሰሞን መሬት ገቢ።

እያንዳንዱ ባለመብት: በመሬቱ ተተክሎ: ማለትም: መሬቱን ይዞ: ባለመሬቱን ቤተ ክርስቲያን: ደብርም ኾነ ገዳም፥ ወይም ገጠር: በግንባር የሚያገለግልበት፥ ወይም: ካህን ቀጥሮ የሚያስገለግልበት ካልኾነ በቀር: በስም ብቻ: "ሲሶ መንግሥት አላት" እየተባለች ስትወቀስ የኖረችው: የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: ራሷ የምትጠቀምበትና የምታዝዝበት: አንድም ርስት ያልነበራት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። መሬቱ: ለእያንዳንዱ ባለመብት: ርስት ኾኖ: ያ ግለሰብ: ይዞታውን: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሳልኾነ ግለሰብ ሳይቀር ሊያከራየው፥ በዕዳ ሊያሲዘው፥ ሊያወርሰውና ሊሸጠው፥ በሌላም መንገድ ሊጠቀምበት እንዲችል ተደርጎ የተኖረ መኾኑ: በኹሉ ዘንድ ይታወቃል። ይህም መሬት: እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በሚተከልበት ጊዜ: ከግል ተካዩ ወይም ከመንግሥት: ለመገልገያ ተብሎ: ለዚያው ቤተ መቅደስ የተሰጠ ሲኾን: በመሬቱ ላይ አገልጋይ የሚኾነው ካህን ይተከልበትና ያ ካህን ወይም ተወላጁ: ያን: መንቀያ መትከያ የኾነ: የቤተ ክርስቲያን መሬት: ርስት አድርጎ ይይዘዋል።

ከዚህ በቀር፡ ማናቸውም ባለመሬት፡ የያዘው ርስት፡ ለመንግሥት፡ በጉልበቱ፥ በሙያው ወይም በሕይወቱ፡ ማለትም በዘመቻ፥ በመሳሰለው ኹሉ፡ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጥበት ኾኖ ሣለ፡ አንዳንዱ፡ ምናልባት፡ ይህን ከመሰለው አገልግሎት ለመዳን፥ ወይም ከልቡ፡ ለነፍሱ የሚበጀውን ለማድረግ ሲል፡ "ይህ መሬቴ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበት እንዲኾን ይፈቀድልኝ" ብሎ ለአጼው ሲያመለክትና ሲፈቀድለት፡ ወደቤተ መቅደሱ መገልገያነት ይዛወራል።

በዚህ መልክ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተመደቡትና ወደዚያ አገልግሎት የገቡት መሬቶች፡ ባጠቃላይ የሰሞን መሬት ይባላሉ። በኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት መሠረት፡ ቤተ ክህነት፡ አገልግሎቷን፡ በበለጠ አሟልታና አስፋፍታ ለማበርከት "ያስችላታል!" ተብሎ ይታመንበት የነበረውን፡ ይህን መብቷን የማስከበሩ ግዳጅ፡ የቤተ ምልክናው (የመንግሥት) ድርሻ ሲኾን፡ ይህ ግዳጅ ባግባቡ ሳይፈጸም በመቅረቱ፡ ዛሬ ካለችበት ጕሥቍልና ለመድረስ በቅታለች።

በዚህ ኹኔታ ተያይዞ፡ በእኔ የአገልግሎት ጊዜ የደረሰው፡ በአሥራት መልክ፡ ለቤተ ክህነት ይሰበሰብ የነበረው፡ የሰሞን መሬት ጠቅላላ የዓመት ገቢ፡ መሠረታዊ ግምቱ፡ ይህን የመሰለው ገቢ ከሌላቸው፡ ከበጌምድርና ከጎጃም በቀር፡ ፩ አእላፍ ፪፻ሺ (አንድ አእላፍ ኹለት መቶ ሺ)፡ ማለትም፡ በፈረንጆች አኀዝ፡ 1, 200, 000 (አንድ million ሚልዮን ኹለት መቶ ሺ) ብር ነበር። ከመንግሥቱ ጠቅላላ ገቢ ውስጥ፡ "ሲሶውን ትካፈላለች" እየተባለ ይለፈፍባት የነበረችው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ታገኘው የነበረው፡ የገቢዋ መሠረታዊ ግምት፡ እንግዴህ ይህ ነበር። ከዚሁ፡ የግምት ገቢም ውስጥ፡ በፈቃድ ይገባ የነበረው፡ ከ፰፻ሺ (ስምንት መቶ ሽህ) ብር አይበልጥም ነበር፤ ሌላው፡ የመንግሥቱ የማስፈጸም ሥልጣን የማይገኝ በመኾኑ፡ ሳይገባ ይቀር ነበር።

እንግዴህ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አዝማሚያ እንደታወቀ፡ እግዚአብሔር፡ በጥበቡ ወጥኖ ያስፈጸመው፡ የሰበካ ጉባዔ መቋቋም በግድ አስፈላጊ ኾኖ፡ እውን እስከኾነበት እስከ፲፱፻፷፭ ዓ. ም ድረስ፡ በ፳ሺ (ሃያ ሽህ) ያህል አብያተ ክርስቲያን ለሚያገለግሉ ፪፻ሺ (ኹለት መቶ ሽህ ካህናት) ያህል ይከፈል የነበረውን የደመወዝና የሥራ ማስኬጃ ወጪ ይሸፍን የነበረው፡ ይኸው፡ ፰፻ሺ (ስምንት መቶ ሽህ) ብር ነበር። ይህ፡ የቤተ ክህነት ጠቅላላ ገቢ፡ ቤተ ክህነት ሳትገባባቸው፡ በየራሳቸው እንዲተዳደሩ፡ በልዩ ትእዛዝና ደንብ ይተዳደሩ የነበሩትን፡ የቁልቢ ገብርኤልን፥ የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያምንና የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴን አብያተ ክርስቲያን የመሰሉ፡ ከፍተኛ የስእለትና የሙዳየ ምጽዋት ምንጭ ያላቸውን፡ የየገዳማቱንና የየአድባራቱን የየግል ገቢ፥ እንዲሁም ቤተ ክህነት ያለባትን የወጪ ግዳጅ ለመሸፈን ሲባል፡ እርሷ በምታዝበት፡ በአዲስ አበባ፡ መንበረ እጨጌ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ባለው፡ በብቸኛው የከተማ ቦታዋ ላይ ካሠራቻቸው ሕንፃዎች፡ የሚገኘውን የኪራይ ገቢ፥ ለጳጳሳቱም፡ ከመንግሥት ይከፈላቸው የነበረውን ደመወዝና አበል አያጠቃልልም።